
የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን
እና
የመፍትሔ አቅጣጫዎች



ሰኔ 2010 ዓ.ም.
በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል
ጊዜያዊ የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት
ትምህርት ሚኒስቴር

ማውጫ

ርእሰ	ገጽ
ክፍል አንድ፣ ጠቅላላ	1
1.1 *መግቢያ*	1
1.2 *መሠረታዊ የቃላት ፍቺ*	2
1.3 **የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ጥናት ሂደት**	2
ክፍል ሁለት፣ በትምህርትና ሥልጠና እስካሁን ያሳካናቸው አንኳር ጉዳዮች	4
ክፍል ሶስት፣ የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን	9
1. አጠቃላይ ትምህርት	10
1.1 **የትምህርት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት**	10
1.2 **የትምህርት ብቃትና ጥራት**	22
1.3 **ሚናቸውን በሚገባ ተገንዝበው ድርሻቸውን ያልተወጡ የአጠቃላይ ትምህርት የባለድርሻ አካላት**	33
2. ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና	35
2.1 **ፍትሐዊነትና ተደራሽነት ያላረጋገጠ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና**	35
2.2 **የውጤት ተኮር ሥልጠና ጥራትና አግባብነት**	37
3. ከፍተኛ ትምህርት	45
3.1 **ለሴቶችና ልዩ ፍላጐት ላላቸው ወገኖች ትኩረት ያልሰጠ የከፍተኛ ትምህርት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት**	45
3.2 **የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት**	48
4. **የትምህርት አመራርና አደረጃጀት**	55
4.1 **ከወቅቱ ጋር ያልተሳሰረ የትምህርት ፍልስፍና/ዓላማ**	55
4.2 **የሕጻናትን እድገት ከሥራ አላም ጋር ያላገናዘበ የትምህርት መዋቅር**	56
4.3 **በቀጣይነት ራሱን እያበቃ የማይሄድና ለሌሎች አቅም መሆን ያልቻለ የትምህርት አመራርና አስተዳደር**	56
4.4 **በችግር የተወሳሰበ የትምህርት ሀብት**	57
4.5 **ከአለም መድረክ ወደኃላ የሳበን የትምህርት መረጃ ሥርአት**	57
4.6 **ፖሊሲውን ሙሉ በሙሉ ያልተገበረ የትምህርት መስጫ ቋንቋ አፈጻጸም**	57
ማጠቃለያ	58
ክፍል አራት፣ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ማሻሻያ ሃሳቦች	59
1. **የትምህርት ፍልስፍና**	59
2. **የትምህርት መዋቅር**	58
3. **የመምህራን ዝግጅትና ምልመላ**	60
4. **አጠቃላይ ትምህርት**	61
5. **የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና**	62
6. **ከፍተኛ ትምህርት**	64
7. **የትምህርትና ሥልጠና ቋንቋ**	66
8. **የትምህርት ፋይናንስ**	66
9. **ሥርአተ-ትምህርት**	66
10. **የትምህርት አስተዳደርና መዋቅር**	68
ማጠቃሻ መጻሕፍት	71
አባሪ-አንድ፣ የፍኖተ-ካርታ ጥናት ተሣታፊዎች ዝርዝር	74

ክፍል አንድ

አጠቃላይ

1.1 መግቢያ

አንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገትን በማምጣት የሕዝቦቿን ኑሮ ማሳደግ የምትችለው በሚኖራት የሰው ኃይል እምቅ አቅም ነው። ዛሬ በሣይንስና ቴክኖሎጂ በልጽገው በአገራቸው ልማትን በማምጣት የሕዝባቸውን ተጠቃሚነት ያጐለበቱ አገሮች ልምድ የሚያሳየን ይህንኑ ሐቅ ነው። በተለይ በቅርብ አመታት ከነበሩበት የድህነት አረንቋ ወጥተው ከፍተኛ የሣይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ላይ የደረሱ የደቡብ ኮሪያ፣ የቻይና፣ የሲንጋፖር፣ የቬትናም፣ የማሌዢያ፣ ወዘተ. አገሮችን ተሞክሮን እንደ አብነት መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ አገሮች ለትምህርትና ሥልጠና በሰጡት ትኩረት የሰው ኃይል ሀብታቸውን በከፍተኛ ደረጃ በማልማት ከፍተኛ እድገት በማስመዝገብ የሕዝባቸውን ኑሮ ማሻሻል ችለዋል። ከዚህ የምንረዳው ትምህርትና ሥልጠና ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማፍራት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ነው።

በአገራችንም መንግሥት በ1986 ዓ.ም. የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በመቅረጽ ባለፉት 24 አመታት ሰብአዊ ሀብትን በማልማት ሀገራችንን በአጭር ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው፤ ሩቅ ባልሆነ ጊዜም ከበለፀጉት አገሮች ተርታ ለማሳለፍ መሠረታዊ መሆኑን በመረዳት ለትምህርትና ሥልጠና ልዩ ትኩረት ሰጥቷል። በዚህም መሠረት በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው የተቀመጠውን አላማና ግብ ለማሳካት ባለፉት አመታት የትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ አግባብነትና ጥራት ለማጐልበት ሰፊ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። ፖሊሰውን መሠረት ያደረጉ የትምህርት ስታንደርዶች፣ ስትራቴጂዎች፣ የትምህርት ልማት መርሃ ግብሮች (ESDP I-V)፣ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዶች (GTP I&II) ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫዎች ጋር በማስተሳሰርና በማዘጋጀት ተግባራዊ እየተደረጉ ናቸው። በዚህም መሠረት በሁሉም ዘርፎች የትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን በማስፋፋት የትምህርት ተደራሽነትና ፍትሐዊነት በማጐልበት በኩል በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ አመርቂ ውጤቶችም ተመዝግበዋል። በተለያዩ ዘርፎች ባለሙያዎችን በማፍራት አገራችን አሁን ለደረሰችበት የእድገት ደረጃ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ። ምንም እንኳን ከመነሻችን ሲታይ የተመዘገቡት ውጤቶች ከፍተኛ ቢሆኑም አሁንም ለሁሉም ሕጻናትና ወጣቶች ትምህርትና ሥልጠናን ማድረስ አልቻልንም፤ በመሆኑም ተጠቃሚ ያልሆኑ ዜጐች አሉ። የትምህርትና ሥልጠና ጥራትና አግባብነትን በተመለከተ በሁሉም የትምህርትና ሥልጠና ዘርፎች በተለይ የተማሪዎችን የመማር ውጤት ከማሻሻል አኳያ በፖሊሲው የተቀመጠውን የመማር ውጤት በማረጋገጥ በኩል ችግሮቹ የገዘፉ ናቸው። ይህም አገሪቱ የምትፈልገውን ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማፍራት በኩል አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል። በመሆኑም እነዚህን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት ይቻል ዘንድ የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እየተሠራ ይገኛል።

ለፍኖተ-ካርታው ግብአት የሚሆን ጥናት እንዲጠና ተደርጓል። ይህ የመወያያ ሰነድ ለፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ግብአትነት ከተጠናው ጥናት በተጨማሪ ከዚህ በፊት በተለያዩ ጊዜያት በትምህርትና ሥልጠና ሥርዓታችን ዙሪያ

በየዘርፉ ማለትም በአጠቃላይ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት በተካሄዱ ግምገማዎች፣ ጥናቶች፣ አመታዊ የትምህርት ስታትስቲክ መረጃዎች፣ አለም አቀፍ የትምህርና ሥልጠና ክትትል ሪፖርቶችን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሰነዶችን መሠረት አድርጓል። በእነዚህ ሰነዶች የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችንና ተግዳሮቶቻችን ተለይተዋል፤ መፍትሔዎች ተጠቁመዋል። በእነዚህ ችግሮችና የመፍትሔ ሃሳቦች ላይ መወያየት ለቀጣይ ዝግጅት መሠረት የሚጥል በመሆኑ ይህ የውይይት ሰነድ ተዘጋጅቷል። ሰነዱም በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍሎ ቀርቧል። ክፍል አንድ፣ መግቢያና የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ጥናት ሂደትን ይዟል። ክፍል ሁለት በትምህርትና ሥልጠና እስካሁን ያሳካናቸው አንኳር ጉዳዮች ይገልፃል። ክፍል ሶስት የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን ያብራራል። ክፍል አራት ደግሞ ለችግሮቹና ተግዳሮቶቹ የመፍትሔ ሃሳቦች የሚጠቁሙና በአጭሚ ቡድኑ የቀረቡ የፖሊሲ ማሻሻያ ምክረ-ሃሳቦች ናቸው።

1.2 መሠረታዊ የቃላት ፍቺ

ሀ. ፍኖተ-ካርታ (Road Map) ማለት አንድን ግብ ውጤታማ ለማድረግ የምንከተለው አቅጣጫ ወይም መንገድ ነው። አሁን እያዘጋጀነው ያለው የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ የአገራችን የመካከለኛ ገቢ ራእይ ለማሳካት የሚያስፈልገውን ብቁ የሰው ኃይል በብቃትና በብዛት እንዴት በማፍራት የአገራችንን ሁለንተናዊ ልማት እና የዲሞክራሲ ግንባታ ሥራዎች መደገፍ እንዲቻል ከአለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በማስተሳሰር የሚዘጋጅ ዝርዝር እቅድ ነው።

ለ. የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ማለት ጠቅለል ያለና የትምህርት ፍልስፍና ያለው በረጅም ጊዜ ልናሳካቸው የሚገቡ ግቦችንና አላማዎች እንዲሁም እነዚህን ግቦችና አላማዎች የሚፈፀሙበትን ስልቶች የሚያመላክት የመንግሥት ሰነድ ነው።

1.3 የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ጥናት ሂደት

አንድ ሥራ ውጤታማ እንዲሆን ከሚያስችሉ ጉዳዮች ዋናውና ቀዳሚውን ድርሻ የሚወስደው እቅድ ነው። በተደራጀና ሙሉዕ በሆነ እቅድ የሚሠራ ሥራ ውጤታማ ይሆናል። በመሆኑም የሰው ሀብት ልማትን ውጤታማ ማድረግ የሚቻለው ዛሬ አለም የደረሰበትን እድገት ደረጃ ከአገር እድገት ጋር ባገናዘ መልኩ የተናበበ ፖሊሲ በማዘጋጀት እና ይህን መሠረት ባደረገ በተሟላ እቅድ ሲመራ ነው። ከዚህ አኳያ ዛሬ በሣይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ያመጡ አገሮች የሰው ሀብታቸውን ከአገራቸው ልማት እንዲሁም አለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ጋር በማስተሳሰርና በማዘጋጀት በመተግበራቸው ውጤታማ ሊሆኑ ችለዋል። የውጤታማነታቸው ሚስጢር የሚያስፈልጋቸውን የሰው ሀይል በፖሊሲ አቅጣጫ በማስቀመጥ፣ ፖሊሲውን ለመተግበር የሚያስችሉ የረጅምና የአጭር ጊዜ እቅዶችን በማውጣት በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ሀብት ማልማት መቻላቸው ነው። እነዚህ አለም አቀፍ ተሞክሮዎች ለአገራች የትምህርትና ሥልጠና እድገት ፋይዳ ያለው መሆኑን በመገንዘብ በ2007 ዓ.ም. ለትምህርትና

ሥልጠና ሴክተሩ ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት የሚሆን የጽንሰ-ሃሳብ ጽሑፍ (Concept Paper) በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል እንዲዘጋጅ ተደረገ። በጽንሰ-ሃሳቡ ላይ የትምህርት ሴክተሩ የማኔጅመንት ካውንስል በተከታታይ ውይይቶችን በማድረግና ጽንሰ-ሃሳቡን በማዳበር እና የመነሻ ሃሳብ በማዘጋጀት ወደ ሀብት ማፈላለግ ሥራ ተገባ። ሥራውን ለመከታተል እንዲቻል ከየዘርፉ የተውጣጣ አንድ የስትራንግ ኮሚቴ እንዲሁም ቴክኒካል ኮሚቴ ተቋቁሞ ክትትል ሲደረግ ቆይቷል። ለዚህ ሥራ የሚሆን ሀብት ከመደበኛ በጀት እና ከአጋር አካላት በማፈላለግ በትምህርት ሚኒስቴር የበላይ አመራር ክትትል እየተደረገበት በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል ሥራው እየተሠራ ይገኛል።

ይህን ሥራ ሊሠሩ የሚችሉት ባለሙያዎችን ለመለየት እንዲቻል መነሻ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ በቀረቡት አማራጮች ላይ ውይይት በማድረግ ምርጫ ተካሂዷል። መሠረታዊ ሃሳቦቹም አለም አቀፍ ባለሙያዎችን ቀጥሮ ማሠራት ወይም የአገሪቱን ምሁራን በመጠቀም እንዲጠና ማድረግ የሚሉ ነበሩ። ከሁለቱ አማራጮች የአገሪቷን ምሁራን በመጠቀም ጥናቱን ማጥናት የተሻለ እንደሚሆን በጋራ በመወሰን ጥናቱ እንዲጠና ተደርጓል። በዚህም መሠረት ሦስት ደረጃዎች ያሉት የአማካሪዎች ቡድን እንዲለዩ በማድረግ ወደ ሥራ ተገብቷል። <u>የመጀመሪያው ቡድን</u> ስድስት አባላት ያሉት የዋና ተመራማሪዎች አባላት የያዘ ሲሆን ዋና ተግባራቸው በስድስት የተለዩ ዋና ጉዳዮች ማለትም <u>ቅድመ መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት፤ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና፤ የከፍተኛ ትምህርት፣ የመምህራን ልማት፣ የትምህርትና ሥልጠና አመራርና ፖሊሲ ጉዳዮች</u> የሚሉ ሲሆኑ በእነዚህ የተለዩ ጉዳዮች ላይ የጥናትና ምርምር ማካሄድና በሚገኘው ውጤት ለፍኖተ-ካርታ ሥራው የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ጭብጦች መለየትና ማዘጋጀት ናቸው። <u>ሁለተኛው ቡድን</u> በዋና አጥኚዎች የሚመሩ እነሱን ጨምሮ በተለዩት ዋና ዋና ጉዳዮች ሥር ስድስት፣ ስድስት ባለሙያዎች በጥቅሉ 36 ባለሙያዎችን የያዘ የአጥኚዎች ቡድን ነው። የባለሙያዎቹ ዋና ዋና ተግባራት በተቀረፀው የጥናት ዘዴዎች አማካኝነት በተመረጡ ክልሎችና የትምህርት ተቋማት በመገኘት መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር የተገኘውን ውጤት ሪፖርት በማዘጋጀት ለዋናው ተመራማሪ ማስረከብ ነው። ከእነዚህ በተጨማሪም አጥኚዎችን በመስክ መረጃ በማሰባሰብ የሚረዱ 73 ረዳት አጥኚዎችም እንዲቀጠሩ ተደርጓል። <u>ሦስተኛው ቡድን</u> ደግሞ አራት አለም አቀፋዊ ባለሙያዎችን የያዘ ሲሆን ከዋና አማካሪዎች በተካሄደው ጥናት የሚገኙትን ጭብጦች መሠረት በማድግ ከዋናው አጥኚዎች ጋር በመሆን ፍኖተ-ካርታውን ለሕትመት ዝግጁ ማድረግ ሲሆን ይህ የአለም አቀፍ ባለሙዎች መረጣ እየካሄደ ሲሆን ሥራው ወደፊት የሚተገበር ይሆናል። እነዚህን ሂደቶች መሠረት በማድረግ በአጥኚዎች አማካኝነት ለፍኖተ-ካርታው ግብአት የሚሆን ጥናት መሠረታዊ ሣይንሳዊ የጥናት ሂደቶችን ጠብቆ ሲካሄድ ቆይቷል።

የጥናቱን አጠቃይ ሂደት በተመለከተ በመጀመሪያ በትምህርት ዘርፍ የተጠኑ ልዩ ልዩ ጥናቶችና ሪፖርቶች በመዳሰስ ለሥራው መነሻ የሚሆን ጽሑፍ (Inception Report) እንዲሁም ዝርዝር የጥናቱ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ አመራሩ ውይይት አድርጉበታል። በአመራሩ የተሰጡ አስተያየቶች እንዲካተቱ በማድረግ የመጨረሻ ቅርጽ በማስያዝ ሰነዱን መሠረት በማድረግ ጥናቱ እንዲጠና ተደርጓል። ለጥናቱ የሚያስፈልጉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ማለትም የጽሑፍ መጠይቅ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ የቡድን ውይይት የሚረዱ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች ረቂቅ በአጥኚ ቡድኑ

ተዘጋጅቶ፣ በተለያዩ መድረኮች በአመራሩና በባለሙያዎች አስተያየት ተሰጥቶባቸው ተሻሽለው ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል። በተዘጋጁት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች መሠረትም የፌድራልና የክልል ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ የዩኒቨርስቲ ኘሬዝዳንቶች፣ የዞንና የወረዳ የትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ የትምህርትና ሥልጠና ባለሙያዎች፣ ዲኖች፣ ርእሰ መምህራን፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ የንግድ ምክር ቤት አባላት፣ የልማት አጋሮች፣ ወዘተ. በአጠቃላይ 15,000 በላይ ሰዎች ለጥናቱ መረጃ በመስጠት ተሣትፈዋል።

በመሰክ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ በስድስት ዋና ጭብጦች ረቂቅ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል። በተዘጋጁት ሰነዶች ላይ የተለያዩ ስድስት ወርክሾፖችን በማዘጋጀት በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካለት ጥናቱ እንዲዳብር ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪም ለጥናቱ ግብአት እንዲሆን የአለም አቀፍ ተሞክሮ መዳሰሱ ተገቢ በመሆኑ ካለው ውሰን ሃብት አኳያ ብዙ ሕዝብ ኖሯቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ መካከለኛ ገቢ የተቀላቀቁ ሀገሮች እንዲሁም የፍኖተ-ካርታ ልምድ ያላቸውን መምረጡ ለጥናቱ ተገቢ በመሆኑ ቬትናም እና ማሌዢያ እንዲመረጡ ተደርጓል። በዚህም መሠረት ዋና አጥኚ ቡድኖቹ እንዲሳተፉ በማድረግ ተሞክሮ ተቀምሮ ሪፖርት ቀርቧል። የማሌዢያ የፍኖተ-ካርታ ብሉ ኘሪንት ሞዴል አጥኚው ቡድኑ ለትምህርት ሚኒስቴር አስረክቧል። አጥኚ ቡድኑ ከመሰክ የተሰበሰበውን መረጃ፣ ከሁለቱ ሀገሮች የተገኙትን ተሞክሮዎች እንዲሁም በወርክሾፖቹ የተሰባሰቡትን አስተያየቶች በማጠቃለል በስድስቱ ዋና ዋና ጉዳዮች ምክረ-ሃሳቦችን የያዙ 694 ገጾች ያሉት ዋና እንዲሁም 100 ገጾች ያሉት የተጠቃለለ የጥናት ሪፖርቶችን በማደራጀት ለሚኒስትር መ/ቤቱ አስረክቧል። ከዚህ በተጨማሪም ረቂቅ ጥናቱን ለትምህርት ሚኒስቴር የበላይ አመራር ገለጻ አድርጓል። ጥናቱም በቀጣይ በሚዘጋጁ መድረኮች አስተያየት ተሰጥቶበት የመጨረሻውን ቅርጽ እንዲይዝ በማድረግ የሚታተም ይሆናል።

ክፍል ሁለት

በትምህርትና ሥልጠና እስካሁን ያሳካናቸው አንኳር ጉዳዮች

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት የተጀመረው በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ መሆኑ ይታወቃል። በወቅቱ የነበረው የትምህርት ዓላማ በጅምር ደረጃ የነበረውን ፊውዳላዊ ቢሮክራሲ የሚያገለግልና በተለይ በአስተርጓሚነት የሚሰራ የሰለጠነ ሰው ኃይል ማፈራት ነበር። ሥርዓተ ትምህርቱም ከውጭ የተቀዳ ሲሆን መምህራኑም እንዲሁ የውጭ ዜጎች ነበሩ። ዘግየት ብሎ ሥርዓተ ትምህርቶቹ በሀገር ውስጥ እንዲቀረጹ ቢደረግም ከውጭ ተጽእኖ ሙሉ በሙሉ ተላቀው የሀገሪቱን ችግር የሚፈታ ተደራሽነት፣ ተገቢነት፣ ፍትሐዊነትና ጥራት ያለው የትምህርት ሥርዓት ሊዘረጋ አልተቻለም። የነበረው የትምህርት ተደራሽነት ውሰን ሲሆን፤ ትምህርት ቤቶችም በዋና ዋና ከተማ ብቻ ነበር የሚገኙት። የትምህርት እድል ሴቶች፣ ልዩ ፍላጎት ያላቸውና አርብቶ አደር ዜጎች ጨርሶ የእድሉ ተቋዳሽ አልነበሩም። ከትምህርት ተገቢነትና ጥራት አኳያ ሲታይም በወቅቱ ከ85% በላይ የነበረውና በግብርና የሚተዳደረውን ሕዝብ ግብርናውን በማዘመን የኑሮ ደረጃውን አላሻሻለም። በመሆኑም የነበረው የትምህርት ሥርዓት የሀገሪቱን ትምህርት ከተደራሽነት፣ ከፍትሐዊነት፣ ከተገቢነትና ከጥራት ችግሮች ሊያላቀቅ አልቻለም። ይህንን ችግር

ለመቅረፍ ካስቻሉን ከ1983 ዓ.ም በኋላ ከተገኙት የሥላም፣ የልማትና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ውጤቶች ውስጥ አንዱ የ1986 ዓ.ም. የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መቀረጽ ነው።

የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው በ1986 ዓ.ም በተደራጀ ሁኔታ ተቀርጾ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል። ፖሊሲውም አምስት አጠቃላይና አሥራ አምስት ዝርዝር ዓላማዎች በማስቀመጥ የትምህርቱን አቅጣጫ በግልጽ አስቀምጧል።[1] ዋናው ዓላማ ትምህርትን በማስፋፋት ብቁ ዜጐችን ማፍራት ነው። ከዚህም ባሻገር ሥርዓተ ትምህርትን፣ የትምህርት መዋቅርን፣ የትምህርት ምዘናና የፈተና ሥርዓትን፣ የመማሪያ ማስተማሪያ ቋንቋን፣ የትምህርት፣ የሥልጠናና የምርምር ተዛምዶን፣ የትምህርት ግብዓቶችን፣ የትምህርት ሥርዓት አደረጃጀትንና ማኔጅመንትን፣ ለትምህርት የሚመደብ በጀትንና ልዩ ትኩረት የሚሹና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራትን በማመላከት ጥርት ያለ አቅጣጫና አሳታፊ ሥርዓት እንዲዘረጋ አስችሏል።

የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው በተዘጋጀበት ወቅት ከፖለቲካዊ ፋይዳቸው አኳያ ሶስት ጊዜ በማይሰጡ ጉዳዮች ላይ ልዩና ቅድሚያ ትኩረት ሰጥቷል። የመጀመሪያው ጉዳይ ከምንከተለው ፌደራላዊ ስርዓት አኳያ ለአንድ ክፍለ ዘመን የነበረውን የተማከለ የትምህርት አመራር ባልተማከለ አቅጣጫ እንዲመራ ማድረግ ነበር። ሁለተኛው ደግሞ የትምህርት አቅርቦት፣ ፍትሀዊነት፣ ተደራሽነት፣ ጥራትና አግባብነት ችግሮችን በዘላቂነት መፍታትና በትምህርት ሰራ ላይ ጉልህ ድርሻ ያላቸውን የመምህራንን ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት ልዩ የሙያ ዕድገት መሰላል በማጥናት ተግባራዊ ማድግ ሲሆን፤ ሶስተኛው ጉዳይ ደግሞ ሥርዓተ ትምህርቱን ከሀገራቱ ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ መቃኘትና ወደ ኢንዱስትሪ መር የኢኮኖሚያ መዋቅር ሽግግር ለምናደርገው ግስጋሴ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ መቃኘት የሚሉ ናቸው። ከእነዚህ የቅድሚያ ትኩረት ጉዳዮች ባሻገር የትምህርትና ስልጠና ስርዓቱ አንድ የኢኮኖሚና ፖለቲካ ማህበረሰብ መገንቢያ ዋና መሳሪያነቱን ያሳካ ዘንድ የሀያ ዓመት የማስተግበሪያ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶለት ከመተግበሩም በላይ በየጊዜው የተከሰቱ ችግሮችን በመፈተሸና ማስተካከያ በማድረግ ተግባራዊ በመደረጉ አሁን ለደረስንበት ማህበራዊ ዕድገትና ልማት ከፍተኛ ድርሻውን በማበርከት ላይ ይገኛል።

ፖሊሲው ተነድፎ በተግባር ላይ ከዋለ በኋላ በሂደት የተመዘገበውን ውጤት እና ለውጥ በጥናት እንዲፈተሹና የሌሎችን ተመሳሳይ ሁኔታ ያላቸውን ሀገሮች ተሞክሮ በመፈተሽ ተግባራዊ በማድረግ እመርታዊ ለውጦች ማስመዝገብ ችለናል። ከእነዚህም ለውጦች መካከል የትምህርት ተሳትፎን፣ ፍትሃዊነትና ጥራትን በማስጠበቅ በኩል የትምህርት አመራሩንና አደረጃጀቱን በወሳኝነት በህዝብ ተሳትፎ እንዲመራ ስርዓት በመዘርጋት እንዲለወጥ ተደርጓል። በሌላም በኩል ደግሞ ከህገመንግስታችን መርሆች አኳያ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ሊላበሷቸው የሚገቡ እሴቶች ተለይተውና ተገቢ ፖለቲካዊ አቅጣጫ ተቀምጦ የስነዜጋና ስነምግባር ትምህርት እንዲሰጥ ከመደረጉም በላይ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ እንዲቀረጽና በየደረጃው ተግባራዊ እንዲደረግ ተደርጓል። ትምህርት

[1] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት። (መጋቢት፣ 1986)። አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ፣ ገጽ 4-6።

የልማት፣ የሰላምና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ማሣለጫ ሆኖ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣትና የማህበረሰቡን አኗኗር ደረጃ ለማሻሻል እንዲቻል በሦስቱ አቅሞች የተቀናጀ ጥረት በርካታ ተደማሪና በጉልህ የሚታዩ ውጤቶች ህዝብና ሀገር ተጠቃሚ ሆነዋል።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በቀደሙት ስርዓቶች የሀገራችን ትምህርት የተደራሽነት መሰረታዊ ችግር የነበረበት በመሆኑ በመላ ሀገሪቱ ከሃያ አራት አመት በፊት 4 ሺህ በሚሆኑ የመጀመሪያ ደረጃና 278 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በአጠቃላይ ከ2 ሚሊዩን ያልበለጡ ተማሪዎች ብቻ ይማሩ ነበር። ይህ ተሳትፎ በዓለም ላይ በዝቅተኛ የትምህርት ተሳትፎ ከሚገኙ ሀገሮች እንድንሰለፍ ያደረገን ነበር። ይህ ዝቅተኛ ተሳትፎም ቢሆን ከአካባቢዎች አኳያ በከተሞችና ዙሪያ ያሉ ዜጎችን ያማከለ፣ ከፆታም አኳያ ሚዛናዊነት የጎደለው፣ ከዚያም አልፎ በልማት ወደ ኋላ የቀሩ ብሔር ብሔረሰቦችን የአርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ተሳትፎ በእጅጉ አነስተኛ ነበር።

ባለፉት ሃያ አራት ዓመታት ጉዟችን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ለማዳረስ በመቻሉ በአሁኑ ወቅት የትምህርት ተቋማት ቁጥር ከ39 ሺህ በላይ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችና 3,300 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከ28 ሚሊዩን በላይ ተማሪዎችን ማስተናገድ ተችሏል። በዚህም ታሪካችንን በልማታዊ አቅጣጫ መርተን መሰረታዊ ለውጥን ማምጣታችን ለሌላው ዓለም ምሳሌ መሆን የምንችልበት ደረጃ ላይ አድርሶናል። የአንደኛ ደረጃ ጥቅል ተሳትፎን ከ1114% በላይ እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኩልም በውስን አካባቢዎች ብቻ ተወስኖ የነበረውን ስርጭት በማስፋፋት ተሳትፎውን 47.1% ለማድረስ ተችሏል። ለዩኒቨርስቲ ትምህርት ማዘጋጃ በሆነው የመሰናዶ ትምህርት ፕሮግራም ከግማሽ ሚሊዩን በላይ ተማሪዎችን በመማር ላይ ሲሆኑ በየዓመቱ ለከፍተኛ ትምህርት ተገቢውን ማለፊያ እያስመዘገቡ ወደ ዩኒቨርስቲ የሚገቡ የተማሪዎችን ቁጥር ከመቶ ሀምሳ ሺህ በላይ ማድረስ ተችሏል። ይህን ውጤት ማስመዝገብ የተቻለው ግልጽ የሆኑ ፖሊሲዎችና ስትራቴዎቻችንን መሠረት ያደረጉ በየአምስት አመቱ የትምህርት ሴክተር ልማት ዕቅዶችን በማዘጋጀት ተግባራዊ በመደረጋቸው ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ትምህርትን በማስፋፋት ለዜጎች ተደራሽ ለማድረግ በተነደፈው ስትራቴጂ መሰረት በአግባቡ በመተግበሩ የተገኘ ውጤት ነው። መላው ህብረተሰብም ልጆቹን በአግባቡ መግቦ አልብሶ እንዲሁም አቅርቦና የትምህርት መሣሪያ እያሟላ ወደ ትምህርት ገበታ ባይልክና በትምህርት ተቋማት ግንባታ ሂደት ላይ የራሱን ከፍተኛ ድርሻ ባይጫወት ኖሮ ለዚህ ውጤት መድረስ አይቻልም ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ህብረተሰቡ ለት/ቤቶች ግብዓት በማሟላት ሳቢና ማራኪ እንዲሆኑ፣ መምህራን በመቅጠርና በትምህርት ተቋማት ግንባታ ላይ ጉልህ ድርሻ መጫወት ችሏል። ሰፊ ጥረት ተደርጓል። እንዲሁም መንግስት አጋር ድርጅቶችን በማስተባበርና በማሳተፍ የተገኘውን ሀብት በአግባቡ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በሚያስችል መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል።

ሌላው የትምህርትና ስልጠናን በአግባቡ ለዜጎች ለማድረስ ርብርብ የተደረገበት ፕሮግራም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ነው። በአሁኑ ወቅት በመካሄድ ላይ ባለው ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር

መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ሽግግር ውስጥ በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሀይል ከማቅረብ አኳያ ዘርፉ ድልድይ በመሆን የተሰጠውን ሚና በአግባቡ በመጫወት ላይ ይገኛል። ከሃያ አራት አመታት በፊት በጥቂት የከተማ አካባቢዎች ተወስኖ የነበሩት 16 ያህል ቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ዛሬ መንግሥታችን በወሰደው ቁርጠኛ እርምጃ በየወረዳው 1546 ተቋማት ማድረስ ተችሏል። የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ስራ ፈጣሪ ዜጋ በማፍራትም ሆነ ለልማቱ የሚያስፈልገውን በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ ባለሞያ በማቅረብ ውጤታማ ስራዎች እንዲከናወኑ ያስቻሉ ናቸው።

በአሁኑ ወቅት በመካሄድ ላይ ባለው ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መርህ መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ሽግግር ውስጥ በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሀይል ከማቅረብ አኳያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ በአለም ደረጃ ሻል ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎች ተቀምሮ ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ስትራቴጂ በማውጣት ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። በዚህም የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ሀገራዊ ስታንዳርድ በማውጣት ስራ ፈጣሪ ዜጋ በማፍራትም ሆነ ለልማቱ የሚያስፈልገውን መካከለኛ የሰለጠነ ባለሙያ በማቅረብ ውጤታማ ስራዎች እንዲከናወኑ ያስቻሉ ናቸው። በተጨባጭም በአሁኑ ሰዓት በሀገራችን በማደግ ላይ ላለው የኢንዲስትሪ/ ማንፋክቸሪንግ ዘርፍ፤ የመሰረት ልማት ዝርጋታ /መንገድ፣ የኤሌትሪክ ሀይል አቅርቦት፣ ቴሌ፣ መብራት፣ ወዘተ/፤ የፍትህ ስርዓት ግንባታ /ዳኛ፣ ፖሊስ፣ አቃቤ ህግ፣ አስተዳዳሪ ወዘተ/፤ ለማህበራዊ ዘርፍ /ጤና፣ ንፁህ ውሀ አቅርቦት አስተዳደራዊ አገልግሎቶች ወዘተ/ በመሳሰሉት ላይ በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሀይል የሚጠይቁ ዘርፎች ናቸው። ይህንንም የሰው ሀይል ከማቅረብ አኳያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ጎልህ ሚና ተጫውቷል።

የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችም የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ተቋማቱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የሚመረቱባቸው፤ የህብረተሰቡን ችግር የሚፈቱ ምርምሮች የሚካሄዱባቸውና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚደረግባቸው ማዕከላት ወደ መሆን እየተሸጋገሩ ይገኛሉ። ወደ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የተሸጋገሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ሲሆን አሁን በደረስንበት ወቅት ከ75 ሺህ በላይ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ማሸጋገር ተችሏል። የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ፕሮግራምን ተግባራዊ ካደረግንበት ዓመት ጀምሮ በርካታ የስራ ፈጣሪ ባለሙያዎችን፤ የጥቃቅንና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ችግር ፈቺ የቴክኖሎጂ ውጤት ማቅረብ የሚችሉ ወጣቶችን በመፍራት ላይ ናቸው። ይህም የሀገራችንን ህዳሴ ለማሳካት የሚያስችለንን እርሾ በመፍጠር በኩል ተቋማቱ ገንቢ ሚና እየተጫወቱ መሆናቸውንና መንግስት ያስቀመጠውን ስትራቴጂ አቅጣጫ ትክክለኛነት የሚያሳይ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በየዓመቱ በሚካሄደው የፈጠራ ውድድርም በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ያሉ ተቋማት በሚያቀርቧቸው አዳዲስ ፈጠራዎች ዕውቅና በማግኘት ላይ መሆናቸው እንዲሁም በዘርፉ ሙያ ቀስመው የሚወጡ ወጣቶች በጥቃቅንና አነስተኛ በመደራጀት ስራ ፈጥረው ሀብት ማፍራታቸው የፕሮግራሙን ስኬታማነት ያረጋግጣል። በመሆኑም በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሰልጥነው የሚወጡ ወጣቶች በሁለንተናዊ መልኩ የክህሎት ባለቤት በመሆን በአንድ በኩል በተለያዩ የልማት ዘርፎች ተቀጥረው መስራት በሌላ በኩል ደግሞ የራሳቸው ስራ ፈጣሪ በመሆን ወደ ስራ በመሰማራት ስኬታማ መሆን ችለዋል።

በቀጣይ ቴክኖሎጂን መቅዳት፣ ማላመድና መፍጠር የሚችሉ እንዲሁም በሰለጠኑበት ዘርፍ የብቃት ማረጋገጫ ምዘና ወስደው ብቁና ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉ በርካታ ወጣቶችን በማፍራት ለሀዳሴው ጉዞ መሳካት ወሳኝ በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል የሚገባው ነው።

በሀገራችን የተጀመረው ልማትና ዕድገት ፈጣንና ተከታታይነቱን ጠብቆ እንዲሄድ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሀይል ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የከፍተኛ ትምህርት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። በመሆኑም በጥቂት ተቋማትና የትምህርት ፕሮግራሞች ተወስኖ የነበረውን አስተሳሰብና አሰራርን በመስበር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተደራሽ ከማድረግ ጎን ለጎን የተልዕኮቸውን ተገቢነት በስትራቴጂ እንዲቃኝ ተደርጓል። የትምህርት ስርዓታችን ወስጥ ከተወሰዱ ወሳኝ ፖለቲካዊ እርምጃዎች አንዱ ግልጽ በሆነ የህግ ማዕቀፍ ዩኒቨርስቲዎችን ማስፋፋት ነበር። በዚሁ መሰረት በፖሊሲ ቀረጻ ወቅት ሁለት የነበሩትን የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ወደ 46 ማደግ ችሏል። ከዚህም በተጨማሪ ወደ 130 የሚደርሱ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሥራ ላይ ናቸው። በዚህም አኳኋን ባለፉት ሀያ አራት ዓመታት በየምዕራፍ ቀጣይነት ባለው መልኩ በሀገራችን ልዩ ልዩ አቅጣጫዎች ፍትሀዊነትን አማክለው የተስፋፉት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስፋትና የቅበላ አቅም ሲታይ ወደ አንድ ሚሊዩን ማድረስ ተችሏል።

የዩኒቨርስቲዎች መስፋፋትና የመቀበል አቅማቸውን ማሳደግ እንደተጠበቀ ትኩረታቸውም ለወደፊት መዳረሻችን ወደ ሆነው የኢንዱስትራላይዜሽን ግብ መሰረት መጣያ እንዲሆኑ ተደርጓል። በዚህም መሰረት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቅበላና ስልጠና ስርዓቱ ሰባ በመቶ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፎች ቀሪው ሰላሳ በመቶ ደግሞ በማህበራዊ ሳይንስና በሌሎች መስኮች ላይ እንዲሆን ተደርጓል። እነኝህን ከሀገራዊ ግባችን አኳያ ተቃኝተው በመተግበር ላይ ያሉ የከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራሞች ውጤታማ እንዲሆኑ በርከት ያሉና ብቃት ያላቸውን ምሩቃን ለማፍራት የሚያስችሉ ወሣኝ የጥራት ማስጠበቂያ ፕሮግራሞች ተቀርጸው ተግባራዊ ሆነዋል። ከእነዚህም መካከል በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ለማስተማሩና ለምርምር ተልዕኮ የሚያስፈለጉትን መምህራን ለማፍራት ከፍተኛ የሆነ የመንግስት በጀት እየተመደበ በውጭ ሀገርና ሀገር ውስጥ የሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ እንዲሰለጥኑ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። ከዚህ በተጨማሪም ዩኒቨርስቲዎች ተገቢ ግብዓት እንዲሟላላቸው ከመደረጉም በላይ የመገናኛ ኢንፎርሜሽን ትስስር መረብ ውስጥ ገብተው ለተልዕኮ ማሳለጫነት እንዲጠቀሙበት ሁለገብ ጥረት ተደርጓል። በሌላ በኩል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከማህበረሰቡ የተነጠሉ እንዳይሆኑ የምርምርና የቴክኖሎጂ መፍለቂያ ማዕከላት ሆነው የሀገራችንን አጠቃላይ ሁለንተናዊ ልማት እንዲያሳልጡ ተልዕኳቸው ግልጽ ሆኖ ተነድፎና አቅጣጫ ተቀምጦ በመሄዱ ከጥቂት ዓመታት በፊት እንደደሴት የመቆጠር ባህልን በመለወጥ በአሁኑ ሰዓት በፖለቲካ አመራርነት፣ በማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚው ዘርፍ፣ ለግሉም ሆነ ለመንግስት ሴክተሩ ያሉ ለውጦችን የሚያንቀሳቅሰውን ሰብዓዊ ሀብት በማምረት በኩል ጉልህ ሚና በመጫወት ላይ ናቸው። ይህም ውጤት/ ስኬት ሊመዘገብ የቻለው መንግስት በፖሊሲ ማዕቀፉ ከፍተኛ ትምህርት ለአጠቃላይ የሀዳሴ ጉዟችንን የሚያስቀጥል ትውልድን የማዘጋጀት ፖለቲካዊ ፋይዳ አስቀድሞ ለይቶ መንቀሳቀሱና በተግባርም ከፍተኛ በጀት በመመደቡ ነው።

በአጠቃላይ እስከአሁን በትምህርት ስርዓታችን የተገኙ ውጤቶች የሀገራችን ህዝቦች በተለይም መምህራን፤ ወላጆችና ተማሪዎች ባደረጉት ያልተቀጠበ ጥረት ነው። ለዘመናት ትምህርት እንደሰማይ ርቋቸው የነበሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ዛሬ የትምህርት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል። የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲያችን ተግባራዊ በሆነባቸው 24 ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የሰለጠነ የሰው ሀብት በማፍራት አሁን በማደግ ላይ ያለውን ሀገራዊ ሁኔታ በማሳለጥ ጉልህ ድርሻ አድርጓል። በገጠር ቀበሌዎች ውስጥ በአርሶ አደር ማሳ ቴክኖሎጂን ተቀብሎ ምርትና ምርታማነት እያሳደገ ያለው አርሶ አደርና አርብ አደር፣ የግብርና ኤክስቴሽን ባለሙያ፣ የጤና ኤክስቴሽን ባለሙያ፣ ከቅድመ መደበኛ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ያሉ መምህራን፣ ከፌደራል እስከ ቀበሌ አመራር፣ የፀጥታ መዋቅሩን የሚመሩት እና በሌሎች የልማት፣ የሰላምና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዘርፎች የተሰማሩ ባለሙያዎችና አመራሮች የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ውጤቶች ናቸው። በተጨማሪም በግል ሴክተሩ በሚካሄደው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተቋማት ዋናውን አሰፈጻሚና ፈጻሚ ኃይል እያዘጋጀ ያቀረበውና የለውጡ ዋና አሳላጭ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲያችን ውጤት ነው። በአሁኑ ወቅት በተለያዩ መስኮች ተሠማርቶ የአገሪቱን ልማት እየደገፈ ያለው ኃይል የዚህ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ውጤት ነው። ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሱ የትምህርትና ሥልጠና ውጤቶችን ያስመዘገብን ቢሆንም በፖሊሲው መሠረት ባለመፈፀም፣ በየደረጃው በፖሊሲው ላይ ግልጽነት ባለመፍጠራችንና በአግባቡ መተግበር ባለመቻላችን እስካሁን ያልፈታናቸው የትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ ጥራትና አግባብነት ችግሮችና ተግዳሮቶች ችግሮች አሉ። እነዚህን ችግሮችና ተግዳሮቶች በተመለከተ በዝርዝር በሚቀጥለው ክፍል እንመለከታለን።

ክፍል ሦስት

የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን

የትምህርትና ሥልጠና ዋና አላማ ጥራት ያለው ትምህርትና ሥልጠና በማቅረብ አገራችን በዝቅተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ የሚያስፈልጋትን ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማፍራት፣ ቴክኖሎጂን በማላመድ፣ በማመንጨትና በማሸጋገር የአገራችንን ሕዳሴ እውን ማድረግ ነው። ይህን ዓላማ እውን ለማድረግ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በመቅረጽና ተግባራዊ በማድረግ ባለፉት ሃያ አራት አመታት በርካታ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። እነዚህ የተሠሩት ሥራዎች ግን ወደ መካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ ሊያደርሱን የሚችሉ አይደሉም። ለዚህም የተለያዩ የትምህርትና ሥልጠና ችግሮች ይጠቀሳሉ። በእነዚህ ችግሮች ላይ በግልጽ ለመወያየት እንዲቻል ችግሮቹ በሦስቱም ዘርፎች ማለትም በአጠቃላይ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተለይተው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. አጠቃላይ ትምህርት

1.1. የትምህርት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት


1.1.1 የቅድመ መደበኛ ትምህርት

ትኩረት የተነፈገውና በአግባቡም ያልተተገበረ የቅድመ መደበኛ ትምህርት። ቅድመ መደበኛ ትምህርት እድሚያቸው ከ4-6 የሆኑ የነገውን አገር ተረካቢ ዜጋ ሕጻናትን በአካልና በአእምሮ በማዳበር አጠቃላይ ሰብእና የምንቀርጽበትና ለቀጣዩ መደበኛ ትምህርት መሠረት የምናስይዝበት ኘሮግራም ነው። በፖሊሲው እንደተቀመጠው "በአፀደ ሕፃናትና በተመሳሳይ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት ሕፃናትን ለተስተካከለ የአካልና የአእምሮ፣ የስሜትና የማህበራዊ ግንኙነት እድገትና ለመደበኛ ትምህርት የማያመቻች" ነው።[2] በፖሊሲው ይህ ይቀመጥ እንጂ በኘሮግራሙ የተሳታፊ ሕጻናት ቁጥር በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። ከ2005 – 2009 ዓ.ም. የጥቅል ተሣትፎውን[3] መጠን ስናይ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም እድገቱ መማር ከሚገባቸው ሕጻናት አኳያ ሲታይ በጣም አዝጋሚና አሳሳቢ ነው። ይህንንም ከሚከተሉት ግራፎች መመልከት ይቻላል።

ግራፍ 1፣ ከ2005-2009 ዓ.ም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ በ%



ግራፍ 2፣ ከ2006-2009 ዓ.ም የቅድመ መደበኛ ትምህርት የጥቅል ተሳትፎ እድገት ጭማሬ በ%




ከላይ ከቀረቡት ግራፎች መረዳት እንደሚቻለው የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ በ2005 ዓ.ም. ከነበረበት 26.1% ወደ 45.9% አድጓል። በአምስት አመት ጊዜ ውስጥ በ2006 ዓ.ም. 7.9% (ወንድ 8.3%፣ ሴት 7.5%) በከፍተኛ ደረጃ፤ በአንፃሩ በ2009 ዓ.ም. 1.5% (ሴት 1.4%፣ 1.3%) በመሆን የእድገቱ ምጣኔ በጣም ዝቅተኛ ነበር። በክልሎች መካከል ያለው የአፈጻጸም ልዩነት እጅግ የከፋና ፍትሐዊነቱ በጣም የሰፋ መሆኑ፣

[2] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት። (መጋቢት፣ 1986)። አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ ገጽ 8።

[3] ጥቅል ተሣትፎ ማለት በክፍል ደረጃው/ደረጃዎቹ ተመዝግበው ትምህርት የጀመሩ አጠቃላይ ተማሪዎች ብዛት፤ እድሜቸው ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ከደረሱ (ከ4-6 እድሜ) ሕጻናት የሕዝብ ብዛት ጋር ሲነፃፀር

<u>እጅግ የከፉና ፍትሐዊነቱ ቦጣም የሰፋ በክልሎች መካከል የአፈጻጸም ልዩነት፣</u> የክልሎችን ተሣትፎ ስናይ በ2009 ዓ.ም. መደበኛ ኘሮግራም አፈጻጸማችን ምን ያህል ዝቅተኛ እንደሆነ ከሚከተለው ግራፍ መረዳት ይቻላል።

ግራፍ 3፣ የ2009 ዓ.ም የክልሎች የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ በ%



	ትግራይ	አፋር	አማራ	ኦሮሚያ	ኢትዮ-ሶማሌ	ቤንሻንጉል-ጉሙዝ	ደቡብ	ጋምቤላ	ሐረሪ	አዲስ አበባ	ድሬዳዋ	አገር አቀፍ
ድምር	93.2	11.7	45.1	31.9	7.4	40.1	72.2	25.9	90.2	92.4	53.8	45.9
ሴት	92.9	11.7	44.6	30.5	7	37.8	69.6	25	88.4	91.4	53.2	44.5
ወንድ	93.5	11.8	45.6	33.3	7.8	42.4	74.9	26.8	91.9	93.4	54.5	47.1

ከላይ ከቀረበው ግራፍ እንደምንረዳው የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሣትፏችን[4] እንደአገር በጣም ዝቅተኛ ማለትም 45.9% **ብቻ ነው። ከክልሎች አንፃር ትግራይ** (93.2%)፣ **አዲስ አበባ** (92.4%) **እንዲሁም ሐረሪ** (90.2%) **በጣም ጥሩ አፈጻጸም አላቸው። ከአገር አቀፍ አማካይ በላይ ነገር ግን ከአለም አቀፍ ከአማካይ በታች የሆኑ ደቡብ** (72.2%) **እና ድሬዳዋ** (53.8%) **ናቸው። በሌላ በኩል ኦሮሚያ** (31.9%)፣ **ቤንሻንጉል-ጉሙዝ** (42.4%)፣ **አማራ** (45.1%) **ዝቅተኛና ከአገር አቀፍ አማካይ በታች የተሳትፎ መጠን ያላቸው ናቸው። በአንፃሩ ኢትዮጵያ ሱማሌ** (7.4%)፣ **አፋር** (11.7%) **እና ጋምቤላ** (25.9%) **አፈጻጸማቸው በጣም ዝቅተኛ ነው።[5]**


<u>ከአለም አቀፍ (ዩኔስኮ ስታንዳርድ) እና ከሰሃራ በታች ካለ አገሮች በጣም ዝቅተኛ ተሣትፎ፣</u> አጠቃላይ የቅድመ መደበኛ ትምህርትን ስናይ እድሚያቸው ለዚህ ደረጃ ከደረሱት 7,769,989 **ሕጻናት ውስጥ** 4,203,564 **የሚሆኑት የዚህ ኘሮግራም ተጠቃሚ አይደሉም።[6] የኘሮግራሙ አፈጻጸማችን ከሌሎች አገሮች እንዲሁም ዩኔስኮ ካስቀመጠው ስታንዳርድ አኳያ ምን ያህል ወደ ኋላ የቀረ መሆኑን ከሚከተለው ግራፍ መረዳት ይቻላል።**

[4] <u>ጥቅል ተሣትፎ</u> ማለት በክፍል ደረጃው/ደረጃዎቹ ተመዝግበው ትምህርት የጀመሩ አጠቃላይ ተማሪዎች ብዛት፣ እድሜቸው ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ከደረሱ (ከ4-6 እድሜ) ሕጻናት የሕዝብ ብዛት ጋር ሲነፃፀር

[5] Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016/17).

[6] Ibid.

ግራፍ 4፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተሣትፎአችን ከሌሎች አገሮችና ከዩኒስኮ ስታንዳርድ ጋር ሲነፃፀር



በአለም አቀፍ ደረጃ በዚህ ኘሮግራም አገሮች ቢያንስ፣ ቢያንስ 80% አፈጻጸም እንዲኖራቸው እንደስታንዳርድ የተቀመጠ ቢሆንም እኛ ግን በሁለተኛው እ.ት.ዕ. መጨረሻ ላይ ይህ ግብ ለማድረስ አቅደናል። የሌሎች አገሮችን ልምድ ስናይ በቅርቡ ይፋ በተደረገው የ2017/2018 Global Monitoring Report (GRM) መሠረት ከአፍሪካ አገሮች ውስጥ ማላዊ 82%፤ ኬኒያ 76% ማድረስ ችለዋል። የእኛ አፈጻጸምና እየተጓዘንበት ያለው አካሄድ ግን ወደ 80% ግብ የሚያደርሰን አይደለም።[7]

ለኘሮግራሙ አፈጻጸም ዋና ዋና ችግሮች መንግሥት በቅድመ መደበኛ ትምህርት የነበረው ተሳትፎ ውስን መሆን፣ ኘሮግራሙ በውስን አካባቢዎች የታጠረ እንጂ ሁሉንም በፍትሐዊነት ያዳረሰ አይደለም። በመንግሥት ት/ቤቶች ቢያንስ የአንድ አመት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ለመስጠት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጀመሩ የ"O" ክፍሎች በአብዛኞዎቹ ትምህርት ቤቶች ለሥራው ባለቤት ያልተሰጠው፣ በእምነት ወደ ሥራው ያልተገባበት፣ የሰለጠነ መምህር የማይመደብበት፣ ሕጻናቱን መሰብሰብ እንጂ በሥርአት እንዲመራ አልተደረገም። ስለኘሮግራሙ የአካባቢው የትምህርት አመራር ቀርቶ የትምህርት ቤት አመራርና ማህበረሰብ በግቢው ውስጥ ስለሚካሄደው ኘሮግራም በውል አያውቅም። ከዚህም ሌላ በአካባቢው ሥራ የሌላቸው ወጣቶች በበጎ ፈቃድ ያለምንም ሥልጠና ለይስሙላ የሚሣተፉበት ከፍተኛ ችግር ያለበት ኘሮግራም ነው። በአንዳንድ ቦታዎች የሚመደቡት መምህራን ለደረጃው የሚመጥን የሕጻናት እንክብካቤና ሥነ-ልቦና እውቀት እንዲሁም የማስተማር ሥነ-ዘዴ እውቀትና ክህሎት የሌላቸው ናቸው። ከዚህም ሌላ ለሕጻናቱ የሚሆን ቦታ ተከልሎ በጨዋታ መልክ መማር ሲገባቸው እንደመደበኛ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በክፍለ ጊዜ በመከፋፈል እንዲማሩ እንዲሁም ከእድሜ እኩዮቻቸው ጋር ሳይሆን ከትላልቆቹ ጋር እንዲጫወቱ መደረጉ ከሕጻናቱ የእድሜ፣ ሥነ ልቦና፣ የፔዳጎጂክስ ሣይንስ ውጪ የሆነ ነው። በመንግሥት በኩል መምህራንን ማሰልጠን እንዲሁም ሥርዓተ-ትምህርት ማዘጋጀት የሚጠበቅ ቢሆንም በደረጃው የተጠናከረ የመምህራን ሥልጠና በብቃትና በብዛት እየተተገበረ አይደለም። የተጠናከረ የምገባ ኘሮግራም አለመኖርም በድህነት ምክንያት


[7] UNESCO. (2017)(. GLOBAL EDUCATION MONITORING REPORT 2017/2018. https://en.unesco.org/gem-report/

ወላጆች ወደ ትምህርት ቤት ልጆቻቸውን አለመላክ እንዲሁም አንዳንዶቹም ከጀመሩ በኋላ ማቋረጥ ጉልቶ ይታያል። ሥርዓተ-ትምህርቱም ቢሆን ስታንደርዱን የጠበቀ አይደለም። የግል ዘርፉን ተሳትፎ ስናይ በአፀደ ሕጻናት ኘሮግራም የሚከናወንና ሥርጭቱም በከተሞች አካባቢ የተወሰነ ሲሆን የሚሰጠውም ትምህርት ከሕጻናቱ የእድሜ ደረጃ በላይ የሆነና ለገበያ ተብሎ ከሌሎች አገሮች የተቀዳ ነው። በአጠቃላይ የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ሕጻናት ለመደበኛ ትምህርት ዝግጁ ባለመሆን ሊገጥማቸው ይችል ለነበረው የማቋረጥ ችግር ተጋላጭነታቸው በአንጻራዊነት በመቀነስ፤ ከክፍል-ክፍል እንዲሸጋገሩ በማድረግ፣ ትምህርቱን በዝግጁነት የመቀበልና የስምንት ዓመቱን ትምህርት ሳያቀራርጡ የማጠናቀቅ እድላቸውን በማስፋት፣ የትምህርት ብክነትን በመቀነስ የትምህርት ጥራትን በማጐልበት በኩል ባለው አስተዋጽኦ ልክ ትኩረት አልተሰጠውም። በየደረጃው ያለው ከፍተኛ አመራርም በዚህ ልክ ተረድቶት ኘሮግራሙን ሲመራና ለሚከሰቱትም ችግሮች መፍትሔ ሲሰጥ አይታይም።

1.1.2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (1ኛ - 8ኛ ክፍል) ኘሮግራም

ፍትሐዊነትን ሙሉ በሙሉ ያላረጋገጠ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት፡ "የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በስምንት ዓመት የሚጠናቀቅ ሆኖ፣ በመሠረታዊና አጠቃላይ ትምህርት ለሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ የሚያዘጋጅና በሂደት የሚዳብር መሠረታዊ ችሎታ ያላቸውን ዜጐች የሚያፈራ እንደሚሆን" በፖሊሲው ላይ ተቀምጧል።[8] በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (1ኛ-8ኛ ክፍል) እድሜያቸው ከ7-14 ለሆኑ ሕጻናት ሁለንተናዊ ሰብእናቸውን የምንቀርጽበት የትምህርት እርከን ነው። ባለፉት ሁለት አሥር አመታት በተደረገው ርብርብ በርካታ ሕጻናትን ማስተማር ተችሏል። ከ2005 – 2009 ባሉት አመታት ያለውን የጥቅል ተሳትፎና በየአመቱ የእድገት ምጣኔ ከሚከተሉት ሁለት ግራፎች መገንዘብ ይቻላል።

ግራፍ 5፣ ከ2005-2009 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ (1ኛ-8ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ በ%



ግራፍ 6፣ ከ2006-2009 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ (1ኛ-8ኛ ክፍል) የተሳትፎ እድገት ጭማሬ በ%



[8] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት። (መጋቢት፣ 1986)። አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ ገጽ 8።

በግራፎቹ እንደተመለከተው ጥቅል ተሣትፎው በ2005 ዓ.ም. ከነበረበት 95.5% በ2009 ዓ.ም. ወደ 111.4% አድጓል። ይህ የሚያመለክተው ጥቅል ተሳትፎው ከአመት አመት እየቀነሰ በመምጣት ሕጻናት በትክክለኛ እድሚያቸው ማለትም ከ7-14 አመት ወደ ትምህርት ቤት በመምጣት መማር ሲገባቸው አሁንም ብዙ ሕጻናት ወደ ት/ቤት እንዳልመጡ ያሳያል። የእድገት ምጣኔውም ከአመት ወደ አመት ከፍ ዝቅ የሚል ሲሆን በ2006 ዓ.ም. በወንዶች 6.9%፣ በሴቶች 4.8%፣ በድምሩ 5.8% ከፍተኛ እድገት የተመዘገበት ነው። በአንፃሩ 2009 ዓ.ም. ዝቅተኛ እድገት የተመዘገበት ሲሆን በወንዶች 3.3%፣ በሴቶች 2.2%፣ በድምሩ 2.7% ተመዝግቧል። በ2009 ዓ.ም. ወንድ 11,029,506፣ ሴት 9,753,572 ድምር 20,783,078 በማስተማር ጥቅል ተሣትፎ 111.4% እንዲሁም ንጥር ተሣትፎ[9] 99.9% በማድረስ የተቻለ መሆኑን የ2009 አመታዊ የትምህርት ስታትስቲክስ መረጃ ያመለክታል።[10] በክልል ደረጃ ያለውን የጥቅልና የንጥር ተሣትፎ መጠን ከሚከተለው ሠንጠረዥ መረዳት ይቻላል።

ሠንጠረዥ 1፣ የ2009 ዓ.ም. የክልሎች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (1ኛ - 8ኛ ክፍል) ጥቅልና ንጥር ተሣትፎ በ%

ክልል	ጥቅል ተሣትፎ			ንጥር ተሣትፎ		
	ወንድ	ሴት	ድምር	ወንድ	ሴት	ድምር
ትግራይ	120.2	113	116.7	110.9	108.4	109.7
አፋር	69.2	62.4	66	51.6	48.4	50.1
አማራ	114.3	109.7	112.1	104.9	102.5	103.7
ኦሮሚያ	113.3	98.9	106.2	102.9	91	97
ኢትዮጵያ ሱማሌ	102	79.5	91.3	80.6	63.2	72.3
ቤንሻንጉል-ጉሙዝ	127.9	107.4	117.8	101.4	90.5	96.1
ደቡብ	131	116.8	123.9	114.6	103.5	109.1
ጋምቤላ	156.5	143.5	150.3	118.3	108.8	113.8
ሐረሪ	119.4	101.5	110.7	104.1	90.8	97.6
አዲስ አበባ	127.1	150.2	138.8	100.9	110.5	105.8
ድሬዳዋ	113.9	103.2	108.6	91.1	83.2	87.2
አገር አቀፍ	117	105.7	111.4	104.1	95.5	99.9

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተጠቀሰው የመጀመሪያ ደረጃ (1ኛ - 8ኛ ክፍል) ትምህርት በጥቅልም ይሁን በንጥር ተሣትፎ ጥሩ አፈጻጸም እንደሆነ መረጃው ያመለክታል። በጥቅል ተሣትፎ ከኢትዮጵያ ሱማሌና አፋር ክልሎች በስተቀር ሁሉም ክልሎች አፈጻጸማቸው ከ100% በላይ ነው። ይህም የሚያመለክተው ሁለት ጉዳዮችን ይሆናል። የመጀመሪያው ከትምህርት ቤት ውጪ የነበሩና ወደ ትምህርት ቤት የተመለሱ ብዙ ሕጻናት እንዳሉ ያሳያል። ሁለተኛው ደግሞ ትምህርት ቤት የተመዘገቡ እንዲሁም እድሚያቸው ከ7-14 ሆኖ ለዚህ የትምህርት ደረጃ የደረሱ ሕጻናት ብዛት አለመጣጣምን ነው። ምክንያቱም የንጥር ቀበላ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በየትኛውም ደረጃ ከ100%

[9] ንጥር ተሣትፎ ማለት በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተመዝግበው ትምህርት ከጀመሩ ሕጻናት ውስጥ እድሚያቸው ከ7-14 የሆኑ ሕጻናት ብዛት፤ እድሚቸው ከ7-14 ሕጻናት የሕዝብ ብዛት ጋር ሲነፃፀር

[10] Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016/17).

መብለጥ የለበትም። ከላይ በሠንጠረዡ የምናየው የአብዛኛዎቹ ክልሎች የንጥር ተሣትፎ መጠን ከ100% መብለጥ ለትምህርት የተመዘገቡና የሕዝብ ብዛቱ አለመጣጣም የሚያሳይ ነው።

ከ5ኛ-8ኛ ክፍል የጥቅል ተሣትፎ መጠንን ስናይ እድገቱ በጣም አዝጋሚ ነው። ባለፉት አምስት አመታት (ከ2005-2009) ያለውን ተሣትፎ ምን እንደሚመስል ከሚከተለው ግራፍ መረዳት ይቻላል።

ግራፍ 7፣ ከ2005-2009 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሣይክል (5ኛ-8ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ በ%




	2005	2006	2007	2008	2009
ሴት	62.2	63.4	64.8	68.9	71.4
ወንድ	63.4	64.7	67.8	73.3	77.3
ድምር	62.8	64.1	66.3	71.1	74.4

ከላይ ከቀረበው ግራፍ እንደምረዳው ጥቅል ተሣትፎ ከ2005 ጀምሮ ከ2% ባልበለጠ የእድገት ምጣኔ በአዝጋሚ በሆነ ሁኔታ እያደገ መጥቶ በ2008 ዓ.ም. ከሌሎቹ አመቶች ጋር ሲነፃፀር በአንፃራዊነት የሴቶች በ4.1%፣ በወንዶች 5.5%፣ በድምሩ 4.8% ከፍተኛ የእድገት ጭማሪ የታየበት ነው። የወንዶችና የሴቶችን የጥቅል ተሣትፎ ምጣኔን ስናይ የወንዶቹ ከሴቶቹ እድገቱ በተሻለ ፐርሰንት እየጨመረ የመጣ ነው። በሌላ መልኩ በ2009 ዓ.ም. መረጃ መሠረት ንጥር ተሣትፎው ደግሞ 59.7% መሆኑ በጣም አሳሳቢ ነው። ምክንያቱም ከንጥር ተሣትፎ አኳያ ሲታይ 40.3% ያክሉ በዚህ የእድሜ ክልል ያሉ ሕጻናት ትምህርት አላገኙም። በተመሳሳይ ጥቅል ተሣትፎው በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መጨረሻ እንደርስበታለን ብለን ከጣልነው የ95% ጋር ሲነፃፀር በ20.6% ልዩነት ያሳያል። ይህ ደግሞ በቀሪው ጊዜ በየአመቱ የ10.3% ጭማሪ ካላሳየ ግቡንም አናሳካም። ከዚህ በተጨማሪም ትምህርት ማግኘት ሲገባቸው የብዙ ሕጻናትን የመማር መብት ተጋፍተናል ማለት ነው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሣትፎን ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አለው።


1.1.3 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት /9ኛ ክፍል - 10ኛ ክፍል/ ኘሮግራም

በጣም አዘጋጪ እድገት እያሳየ ያለ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የአገራችን ኢኮኖሚ የሚፈልገውን በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል የምናዘጋጅበት ነው። ይህ ዘርፍ የመካከለኛ ገቢ ራዕያችን በአጭር ጊዜ ለማሳካት ቴክኖሎጂ የሚጠቀም፣ በእውቀት፣ በክህሎት፣ በአስተሳሰብ፣ በችሎታና በተወዳዳሪነት ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚና የፖሊቲካ ማህበረሰብ ለመገንባት ከፍተኛ ድርሻ ያለው ነው። አንድ አገር አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም ማደረስን ካላሳካች የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ መድረስ አስቸጋሪ ይሆንባታል። ከ2005 – 2009 ዓ.ም. የሁለተኛ ደረጃ ጥቅል ተሣትፎ እና የእድገት ምጣኔ ሲታይ በጣም አዘጋጪ እንደሆነ የሚከተሉት ሁለት ግራፎች ያሳያሉ።

ግራፍ 8፣ ከ2005-2009 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-10ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ በ%




ግራፍ 9፣ ከ2006-2009 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-10ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ እድገት ጭማሬ በ%



ከላይ የቀረቡት ሁለት ግራፎች የምንረዳው የሁለተኛ ደረጃ ጥቅል ተሣትፎ ከ2005 ከነበረበት 38.4% በ2009 ዓ.ም. 47.1% ያደገበት ምጣኔ በጣም አዘጋጪ ነው። በየአመቱ በ2008 ዓ.ም. በ5.2% ከማደጉ በስተቀር በሌሎቹ አመቶች በ2005፣ በ2007፣ በ2009 ያደገበት ምጣኔ እንደቅደም ተከተሉ በ0.9%፣ 0.5%፣ 2.1%%ት መሆኑ እጅግ አሳሳቢ ነው። የክልሎች የ2009 ዓ.ም. የጥቅል እንዲሁም የንጥር ተሣትፎ የት ደረጃ ላይ እንደምንገኝ በሚከተሉት ሁለት ግራፎች ማየት እንችላለን።

ግራፍ 10፣ የ2009 ዓ.ም. የክልሎች የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-10ኛ ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ በ%




	ትግራይ	አፋር	አማራ	ኦሮሚያ	ኢትዮ-ሶማሌ	ደቡብ	ቤንሻንጉል-ጉሙዝ	ጋምቤላ	ሐረሪ	አዲስ አበባ	ድሬዳዋ	አገር አቀፍ
ወንድ	71.4	18.3	50.3	41.3	17.3	58.8	61.2	114.8	57.9	107.7	55.4	48.9
ሴት	76.1	12.9	56.4	33.6	11.4	47.8	46.4	96.0	51.4	122.9	47.3	45.2
ድምር	73.7	15.9	53.3	37.5	14.7	53.4	53.9	105.9	54.7	115.6	51.3	47.1

ከላይ ከቀረበው የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ጥቅል ተሣትፎ የ2009 ዓ.ም. መረጃ መሠረት ተሳትፏችን በጣም ዝቅተኛ ነው። በዘመኑ በዚህ የትምህርት እርከን ወንድ 1,074,674፣ ሴት 964,461 ድምር 2,039,135 ተማሪዎች ነበሩ። እንደሀገር አፈጻጸማችን 47.1% ጥቅል ተሳትፎ ሲሆን በክልሎች መካከል ሰፊ የተሣትፎ ልዩነት ይታያል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ የተሣትፎ መጠን 115.6% ሲኖረው በመቀጠል ጋምቤላ 105.9%፣ ትግራይ 73.7%፣ ሐረሪ 54.7%፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ 53.9%፣ ደቡብ 53.4%፣ አማራ 53.3%፣ ድሬዳዋ 51.3%፣ ኦሮሚያ 37.5%፣ አፋር 15.9% እንዲሁም ኢትዮጵያ ሱማሌ 14.7% እንደቅደም ተከተላቸው የጥቅል ተሳትፎ መጠን አላቸው።[11] በተለይ የታዳጊ ክልሎች ተሳትፎ እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነው። የጋምቤላ አፈጻጸም የተሻለ አፈጻጸም ያለው ቢመስልም የነባር ብሔረሰቦችን ተሣትፎ በግልጽ የሚያሳይ ባለመሆኑ እንዲሁም የሌሎች ታዳጊ ክልሎች ነባር ብሔረሰቦች ከኢትዮጵያ ሱማሌ ክልል በስተቀር የደረጃውን ትምህርት ተሳታፊ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባናል።

በአጠቃላይ ከጥቅል ተሳትፎ አኳያ አፈጻጸማችን **አገራችን ከምትፈልገው በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል አኳያ ሲታይ በጣም ዝቅተኛና አሳሳቢ ጉዳይ ነው።** በአብዛኛዎቹ አገሮች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አራት አመት ሲሆን እኛ የምንሰጠውም ትምህርት ግን የሁለት አመት ትምህርት ነው። የእኛ ወጣቶች **በአብዛኛው በሊጋ እድሚያቸው ማለትም በ16 አመታቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሲለሚያጠናቅቁ ለሥራ ዝግጁ የሚሆኑበት እድሜ አይደለም።** ለዚህ የሚጠቀሱ ምክንያቶች ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቀለል ባለ መልኩ ከታችኛው ክፍል በትውውቅና እጅን ከማፍታታት አኳያ ሲለማይጀመር፤ የሥራ ፈጠራ ጽንሰ ሃሳብ ከታችኛው የክፍል ደረጃዎች ተጣጥሞ ሲለማይቀርብ፤ ወጣቶች 10ኛ ክፍልን ሲጨርሱ ባሉበት ቦታ በቂና ተገቢ ሥልጠና በመሰጠት ወደ ሥራ ሲለማይሰማሩ ችግሩ የገዘፈ ነው። በሌላ በኩል **የሁለተኛ ደረጃ ንጥር ተሳትፏችን ከጥቅል ተሳትፏችን ጋር ሲነጻጸር አፈጻጸማችን እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው።** ይህንንም ከሚከተለው ግራፍ መረዳት ይቻላል።

[11] Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016/17).

ግራፍ 11፣ የ2009 ዓ.ም. የክልሎች የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-10ኛ ክፍል) ንጥር ተሣትፎ በ%




	ትግራይ	አፋር	አማራ	ኦሮሚያ	ኢትዮ-ሶማሌ	ደቡብ	ቤንሻንጉል-ጉሙዝ	ጋምቤላ	ሐረሪ	አዲስ አበባ	ድሬዳዋ	አገር አቀፍ
ወንድ	38.61	7.91	25.16	21.02	8.34	30.86	23.29	36.73	31.36	60.23	26.03	24.93
ሴት	41.44	6.30	29.69	18.37	5.86	26.20	23.36	30.48	29.69	66.14	25.35	24.36
ድምር	40.01	7.20	27.40	19.70	7.25	28.54	23.33	33.76	30.52	63.38	25.69	24.65

የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (9ኛ-10ኛ ክፍል) እድሚያቸው ከ15-16 የሆናቸውን ወጣቶች የሚይዝ በመሆኑ ንጥር ቅበላው የሚሰላው በዚህ እድሜ ክልል 9ኛና 10ኛ ክፍል የተመዘገቡ እድሚያቸው ለዚህ የትምህርት ደረጃ የደረሱ ወጣቶችን ብዛት ተነጻጽሮ የሚሰላ ነው። ከዚህ አኳያ የአገራችንን አፈጻጸም ስናየው እጅግ በጣም ዝቅተኛ ማለትም 24.65% ነው። ከአዲስ አበባ (63.38%) በስተቀር ሌሎች ክልሎች ንጥር ተሳትፏቸው አሳሳቢ ነው። በከፋ ሁኔታ የታዳጊ ክልሎች ማለትም አፋር (7.20%) እንዲሁም ኢትዮጵያ ሱማሌ (7.25%) ልዩ ትኩረት የሚሹ ናቸው።[12]

ከአለም አቀፍ እና ከሰሃራ በታች ካሉ አገሮች በጣም ዝቅተኛ ተሣትፎ፣ **በአጠቃላይ የአገራችን የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ንጥር ተሣትፎ ከሌሎች አገሮች ጋር በንጽጽር ሲታይ ያለችበትን ደረጃ በጣም ዝቅተኛ ነው።**

ግራፍ 12፣ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-10ኛ ክፍል) ንጥር ተሣትፎአችን ከሌሎች አገሮችና ከአለም አማካይ ጋር ሲነፃፀር



[12] Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016/17).

ከላይ የተጠቀሰው ግራፍ አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-10ኛ ክፍል) ንጥር ተሣትፎአችን ከሌሎች አገሮችና ከአለም አማካይ ጋር ሲነፃፀር የሚያመለክት ነው። የአለም ባንክ የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ እርከን ላይ የሚገኙ አገሮች ኢኮኖሚያቸውን መሸከም የሚችል የሰው ሀብት ከማፍራት አንጻር ዝቅተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎአቸው ቢያንስ 72% መድረስ እንደሚገባው አስቀምጧል።[13] በቅርቡ በወጣው GMR ሪፖርት ደግሞ የአገሮች አማካይ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ንጥር ተሣትፎ 84% ሲሆን የአደጉ አገሮች 99%፣ ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው 92%፣ ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው 81%፣ ከሰሃራ በታች ያሉ አገሮች 64%፣ ከአፍሪካ አገሮች ጋና 91%፣ ማላዊ 83% እንደደረሱ መረጃው ያመላክታል።[14] ከዚህ አኳያ የአገራችንን የሁለተኛ ደረጃ (9-10) ጥቅል ተሣትፎ በሁለተኛ የእ.ት.ዕ መጨረሻ 74% ለማድረስ ብናቅድም በ2009 ዓ.ም. መረጃ መሠረት መድረስ የቻልነው ጥቅል ተሣትፎ 47.1%፣ ንጥር ተሣትፎ 24.6% ነው። ይህ አፈጻጸማችን ወደ አለምነው ግብ የሚያደርሰን አይደለም። ከዚህ በተጨማሪም በዩኒስኮ ሪፖርት መሠረት እ.ኤ.አ በ2015 በአለም ላይ ወደ 62 ሚሊዮን ወጣቶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (lower secondary) ማግኘት ሲገባቸው ያላገኙ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ 26 ሚሊዮን የሚሆኑት ከሳህራ በታች በሚገኙ አገሮች ውስጥ የሚኖሩ ወጣቶች ናቸው። በኢትዮጵያም በዘመኑ 4,577,000 ወጣቶች የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማግኘት ሲገባቸው ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ናቸው።[15]

በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ላስቀመጥነው ግብ አለመሳካት በዋናነት የሚጠቀሱ ምክንያቶች የመጀመሪያ ደረጃ ከመስፋፋቱና የትምህርት ተሣትፎው እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ አሁን ያለን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማስፋፋት ሥራ ከመጀመሪያ ደረጃ የሚመጣውን ሰፊ የተማሪ ኃይል ሊሸከም የሚችል አይደለም። ወደቀጣዩ ክፍልም የተሸጋገሩት ተማሪዎች ቢሆን ከተቋማቱ ርቀት አንጻር ተደራሽ ባለመሆናቸው ወላጆች ልጆቻቸውን በተለይ ሴት ልጆቻቸውን በኢኮኖሚና በርቀቱ ምክንያት ባላቸው ስጋት ስለማይልኩ ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ይገደዳሉ። ከዚህ በተጨማሪ ከመጀመሪያ ደረጃ የሚመጣውን ሰፊ የተማሪ ኃይል ሊሸከም የሚችል በእቅድ ላይ ተመሥርቶ አለመሥራት፣ ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ ስምንተኛ ክፍል እስከሚደርሱ ድረስ ተከታታይነት ባለው ሂደት ተማሪዎችን በማብቃት ወደ ቀጣዩ ክፍል እንዲሸጋገሩ አለማድረግ፣ ትምህርት ቤት የገባውም ቢሆን በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርት የማቋረጡ ሁኔታ የትምህርት ሥርዓቱን እየተፈታተኑት ያሉ ችግሮች ናቸው።

1.1.3.1 ምንም እንኳን በእቅዳችን የሄደ ቢሆንም ዝቅተኛ የመሰናዶ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት /11ኛ ክፍል - 12ኛ ክፍል/ ፕሮግራም


የመሰናዶ 2ኛ ደረጃ (11ኛ-12ኛ ክፍል) ትምህርት የከፍተኛ ትምህርት አካል ሲሆን በ2009 ዓ.ም. ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩት ተማሪዎች ቁጥር ወንድ 283,494፣ ሴት 236,548 ድምር 520,042 ናቸው። እንደአገር ጥቅል ተሳትፏችን 12.5%፤ የንጥር ተሣትፏችን ደግሞ 7.4% ነው። ከአለም አቀፍ ስታንዳርድ (45% ጥቅል ተሣትፎ)

[13] The World Bank. (2013). Secondary Education in Ethiopia. (p. 44).
[14] UNESCO.(2017). GLOBAL EDUCATION MONITORING REPORT 2017/2018. https://en.unesco.org/gem-report/
[15] Ibid.

እንዲሁም አገራችን ካለመችው ራዕይና የሰው ኃይል ፍላጎት አኳያ የተሳትፎ መጠናችን በጣም ዝቅተኛ ነው። በዚህም ኘሮግራም ከላይ በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተጠቀሱት ችግሮች እንደተጠበቁ ሆኖ የሁለተኛ ደረጃ መሰናዶ ተደራሽነት የበለጠ የከፋ ነው። በተማሪዎች መኖሪያና በት/ቤቶች መካከል ያለውን ርቀት በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ለማቋረጥ የሚገደዱ ተማሪዎች በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

በአጠቃላይ ከ1ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል ያለው የተማሪዎች ብዛት ስናይ በ1ኛ ክፍል በጣም ብዙ ተማሪ የሚመዘገብ ሲሆን ክፍሉ እየጨመረ ሲሄድ የተማሪዎች ቁጥር እየቀነሰ ይሄዳል። ይህን በተመለከተ የ2009 ዓ.ም. እየተማሩ ከነበሩ ተማሪዎች መረዳት ይቻላል።

ግራፍ 13፣ የ2009 ዓ.ም. ከ1ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል የተማሪዎች ብዛት የሚያሳይ




ከላይ በግራፉ እንደተመለከተው በ1ኛ ክፍል የነበሩ ተማሪዎች ብዛት 4,047,482 በየክፍል ደረጃው እየቀነሰ መጥቶ 12ኛ ክፍል የተማሪዎች ብዛት 254,703 ደርሷል። ይህ የሚያመለክተው በትምህርት ሥርዓታችን ወደ ትምህርት ቤት የገቡ ሕጻናት ከፍ ብሎ በተገለጹት ምክንያቶች በማቋረጣቸው በየክፍሉ ቁጥራቸው እየቀነሰ መምጣቱን ነው። በመሆኑም ሁሉም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ወላጅ፣ ተማሪ፣ መምህር፣ የትምህርት አመራሩ ችግሮቹን በተለይ የተማሪዎች የሚቀሩበትን ምክንያት እየለዩ መፍትሔ መሰጠት ይገባቸዋል።

1.1.4 ባለቤት አባል ተግባር ተኮር የጉልማሶች ትምህርት ኘሮግራም

የተግባር ተኮር የጉልማሶች ትምህርት ጉልማሳው ከመሠረታዊ ትምህርት ባሻገር በአገራችን ልማት እንቅስቃሴ ላይ ንቁና ወሳኝ ተሣትፎ እንዲያደርግ የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርትና ሥልጠና በመስጠት ምርታማነቱን፣ ጤናውን፣ ኑሮውንና ማህበራዊ ተሳትፎውን ትርጉም ባለው ሁኔታ እንዲያሻሽል ማድረግ ያስፈልጋል። በ2004 ዓ.ም የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ መሰረት በኢትዮጵያ ወደ 20.4 ሚሊዮን የሚጠጉ ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት የማይችሉ ጎልማሶች እንደነበሩ ታውቋል። ከእነዚህ ውስጥ እስከ አሁን ማስተማር የቻልነው 12 ሚሊዮን ጉልማሶችን ብቻ ነው።[16] ይህም ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት የሚችሉ ጉልማሶችን ወደ 65% ያደርሰዋል።[17] በአንፃሩ እስካሁን 8.4 ሚሊዮን ጉልማሶች ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት እንደማይችሉ ያሳያል። አፈጻጸማችንን ከሌሎች ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ማየት እንችላለን።

ግራፍ 14፣ ማንበብ፣ መፃፍና ማስላት የሚችሉ ጉልማሶች የተሣትፎ መጠናችን ከሌሎች አገሮችና ከአለም አማካይ ጋር ሲነፃፀር



በግራፉ ላይ የተጠቀሱት መረጃዎች ከኢትዮጵያ በስተቀር ሌሎቹ ከGRM[18] ሪፖርት የተገኙ ናቸው። በሪፖርቱ እ.ኤ.አ. በአለም ላይ ማንበብ፣ መፃፍና ማስላት የሚችሉ ጉልማሶች 86.2% ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ከሰሃራ በታች ያሉ 64.6%፣ ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ የላቸው 76.4%፣ ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች 94.4% እንደሆኑ መረጃው ያመለክታል። ከዚህ አንፃር የእኛ አፈጻጸም ስናነጻጽረው መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ የዜጎች የማንበብና የመጻፍ ምጣኔ 76.4% መድረስ ይኖርበታል። ጉልማሶችን ማስተማር የበለጠ ምርታማ እንዲሆኑ ከማስቻሉም በላይ ልጆቻውን በማስተማር በትምህርታቸው በመዝለቅ ውጤታማ እንዲሆኑ እንዲሁም በልጆቻቸው የባህሪ ግንባታ ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችሉ ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪም ጉልማሶችን እስከ ሁለተኛ

[16] Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016/17).
[17] ትምህርት ሚኒስቴር። (ነሐሴ/2009)። የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የ2009 ዓ.ም. የትምህርት ንቅናቄ ሰነድ።
[18] UNESCO.(2017). GLOBAL EDUCATION MONITORING REPORT 2017/2018. https://en.unesco.org/gem-report/

ደረጃ ትምህርት ማስተማር ድህነትን ከግማሽ በላይ እንደሚቀንስ ጥናቶች ያመለክታሉ።[19] ልጆቻቸውንም እስከ ከፍተኛ ትምህርት የማስተማር ሁኔታቸውም በዚህ ደረጃ ካልተማሩት ጐልማሶች ወይም ወላጆች ጋር ሲነጻጸር ትርጉም ባለው መጠን ተሳትፏቸው ከፍተኛ ነው።[20] ምንም እንኳን ጐልማሶችን ማስተማር ሁለንተናዊ ጠቀሜታ እንዳለው ቢታወቅም በአገራችን በፕሮግራሙ አፈጻጸምና አመራር ላይ በርካታ ችግሮች ይስተዋላሉ። ከእነዚህ ችግሮች መካከል የሚሰጠው ሥልጠና ከጐልማሳው ሕይወት ማለትም ግብርና፣ ጤና፣ የሕይወት ክህሎት፣ ወዘተ. ጋር የተቀራኘ አለመሆን፣ የጐልማሳውን ፍላጐት መነሻ ያላደረጉ ሥልጠናዎች መሰጠት፣ ማንበብና መጻፍ ላይ ማተኮር፣ ተገቢው አደረጃጀት የሌለው መሆኑ፣ ተአማኒና ወቅታዊ መረጃ አለመኖር[21]፣ ግብአቶች አለመሟላት፣ ፕሮግራሙን ለመምራት በየደረጃው የተቋቋሙት የቦርድና የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አለመግባት፤ መርህግብሩን ለትምህርቱ ሴክተር ብቻ መተው ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው።[22] የተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርት የሰው ሀብት ልማት አንዱ አካልና የማያቋርጥ ከመሠረታዊ የማንበብና መጻፍ ክህሎት እስከ የሕይወት ክህሎት የሚሰጠና ኢኮኖሚውን በከፍተኛ ደረጃ ሊደግፍ የሚችል ፕሮግራም ቢሆንም የተሰጠው ትኩረት በጣም አናሣ ከመሆኑም ባሻገር መካከለኛ ኢኮኖሚ ደረጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመግባት ወሳኝ መሆኑን በየደረጃው ያለው አመራር በደንብ የተገነዘበው አይደለም።


1.2 የትምህርት ብቃትና ጥራት

1.2.1 እጅግ አሳሳቢ የሆነ ብክነት የሚታይበት የትምህርት ውስጣዊ ብቃት

ውስጣዊ ብቃትን (Internal Efficiency) በተመለከተ በዚህ ስር በዋነኛነት የሚካተቱት ትምህርትን ተከታትሎ የማጠናቀቅ ምጣኔ ማደግ እና የመጠነ ማቋረጥና መጠነ መድገም መቀነስ ናቸው። ከዚህ አኳያ በመጀመሪያ ደረጃ በትምህርት የተሣትፎ መጠን የተሻለ ውጤት እንደተመዘገበ ከፍ ብሎ ተጠቅሷል። ምንም እንኳን ብዙ ሕጻናት ወደ ትምህርት ቤት በማስገባት እንዲማሩ በማድረግ ጥሩ ሥራ የተሠራ ይሁን እንጂ ፕሮግራሙ በብዙ ችግሮች የተተበተበ ነው። በመጀመሪያ 1ኛ ክፍል ከገቡት ሕጻናት ውስጥ 18.1% ማለትም በ2009 ዓ.ም. አዲስ ከተመዘገቡ 3,730,535 ሕጻናት ውስጥ 675,227 አቋርጠዋል። ይህም የሕጻናቱን የመማር መብት በማክበር በቀጣይ ለሚኖረው አገራዊ የልማት ተሣትፎ እንዲጨናገፍ ከማድረጋችን ባሻገር ከፍተኛ የሀብት ብክነትን እንዲከሰትም አድርገናል።[23] ወደ ትምህርት ቤት መጥተው እስከ 5ኛ ክፍል የሚዘልቁ ተማሪዎች ምጣኔ 53.5% ብቻ ነው። ይህ ማለት ደግሞ 1ኛ ክፍል ከተመዘገቡ 1,000 ሕጻናት ውስጥ በዘላቂነት 5ኛ ክፍል የደረሱት 535 ሲሆኑ ቀሪዎቹ 465 የደገሙና ያቋረጡ ናቸው። የማጠናቀቅ ምጣኔ በተመለከተ አፈጻጸማችን ምን ያህል ችግር እንዳለበት ከሚከተለው ግራፍ በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

[19] UNESCO. (June, 2017). Reducing Global Poverty through Universal Primary and Secondary Education,Policy Paper 32/Sheet 44, p.11.
[20] The Wold Bank. (2017). Sharing Higher Education's Promise beyond the Few in Sub-Saharan Africa, p. 30.
[21] Ministry of Education. (2017.) Ethiopian Education Development Roadmap: An integrated Executive Summary (Draft).
[22] ትምህርት ሚኒስቴር፣ (ነሐሴ፤ 2008)። የማሻቀልቀል ምዕራፍ ተዘግቶ የእድገት ምዕራፍ በተከፈተበት የሃያ አምስት ዓመታት ጉዞ ውስጥ የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ሚናና ለቀጣይ ተልዕኮ ሊኖረው የሚገባው ቁመና። አዲስ አበባ፡ ትመማድ።
[23] Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016/17).

ግራፍ 15፣ የመጀመሪያ ደረጃ የማጠናቀቂያ ምጣኔአችን ከሌሎች አገሮችና ከአለም አማካይ ጋር ሲነፃፀር



በGMR[24] ሪፖርት መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የማጠናቀቅ ምጣኔ ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች 95%፣ ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው 83% እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ አማካኙ ደግሞ 83% ሲሆን የአገራችን አፈጻጸም ግን 54.10% ነው። ይህ ማለት እድሚያቸው ለሰምንተኛ ክፍል የደረሱ ሁሉም 1,428,590 ተማሪዎች[25] ማጠናቀቅ ሲገባቸው 655,723 (45.90%) የሚሆኑት አለማጠናቀቃቸው የሀብት ብክነት ከማሰከተሉም በሻገር በአገራችን ሁለንተናዊ እድገት ላይ የሚኖረው ተጽእኖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል የሚያቋርጡ ሕጻናት ከድህነት እንዲሁም ከትምህርት ቤት ርቀት ጋር ተያይዞ ባሉ ምክንያቶች ሲሆን ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያሉት ሕጻናት ግን ባህሪው ለየት ይላል። ከ5ኛ አስከ 8ኛ ክፍል የእድሜ ክልል ያሉ ህጻናት (11-14) የሚያጋጥማቸው የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖዎች ማለትም የጉልበት ስራ፣ ጋብቻ፣ የኢኮኖሚ አቅም ማነስ፤ ወዘተ. ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው ለማቋረጥና ከት/ቤት ውጭ ለመሆን ይገደዳሉ። ይህ ደግሞ በ2ኛ ደረጃ፤ በቴክኒክና ሙያ እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ዘርፎች በመካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሀብት ልማት ፍላጎታችን መሳካት እንቅፋት እየሆነ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ብዙ ሕጻናት የትምህርት ቤት ደጃፍ ያልረገጡ አሉ። በዩኒሰኮ ሪፖርት መሠረት እ.ኤ.አ በ2015 በአለም ላይ ወደ 264 ሚሊዮን የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማግኘት የሚገባቸው ሕጻናትና ወጣቶች ከትምህርት ቤት ውጪ ነበሩ። ከእነዚህ ውስጥ 61 ሚሊዮን የሚሆኑት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መከታተል የነበረባቸው ሕጻናት ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ ሲሆኑ 33 ሚሊዮን የሚሆኑት ከሳህራ በታች በሚገኙ አገሮች ውስጥ ያሉ ሕጻናት ናቸው። እ.ኤ.አ. በ2015 በአለም ላይ እድሚያቸው ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ደርሶ ወደ ትምህርት ቤት በመምጣት መማር ሲገባቸው ከትምህርት ቤት ውጪ የሆኑ ሕጻናት አንድ ሶስተኛውን ቁጥር የያዙት ናይጄሪያ (8.7 ሚሊዮን)፣ ፓኪስታን (5.6

[24] UNESCO. (2017). GLOBAL EDUCATION MONITORING REPORT 2017/2018. https://en.unesco.org/gem-report/
[25] Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016/17). GE 2009_Annex.

ሚሊዮን)፣ ሕንድ (2.9 ሚሊዮን)፣ ሱዳን (2.7 ሚሊዮን)፣ ኢንዶነዢያ (2.6 ሚሊዮን) እንዲሁም ኢትዮጵያ (2.2 ሚሊዮን) ናቸው።[26] በኢትዮጵያ በዘመኑ 2,194,000 ሕጻናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማግኘት ሲገባቸው ወደ ትምህርት ቤት አልመጡም።[27] በተለይ ልዩ ፍላጐት ያላቸው፣ የነባር ብሔረሰቦች፣ በገጠር የሚገኙና የሴት ሕጻናት ወደ ትምህርት ቤት አለመምጣት ችግር የከፋ ነው።

ከላይ ለተጠቀሱት ችግሮች ዋና ዋና መንስኤዎቹ ራሱንም ሆነ ልጆቹን መመገብ ያልቻለ ወላጅ ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት ከመላክ ይልቅ ገቢ ወደሚያስገኝ ሥራ ያሰማራቸዋል። አንዳንዶቹም ልጆቻቸውን ለመላክ ቢሞክሩም ለትምህርት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች ማሟላት ስለማይችሉ በትምህርቱ ሳይዘልቁ ይቀራሉ። ሌላው የማቋረጥ ምክንያት በአንዳንድ ቦታዎች የትምህርት ቤቶች ተደራሽነት አለመሆን ነው። ሕፃናትና ወጣቶች በተለይ ሴት ልጆች ወደ አምስተኛ እና ዘጠነኛ ክፍሎች ሲዛወሩ በኢኮኖሚ ወይም ከቤተሰብ ርቀው ለመማር አስቸጋሪ መሆኑ ነው። ከትምህርት ጥራት ጋር ተያይዞ ተማሪዎች በክፍል ደረጃቸው ማወቅ የሚጠበቅባቸውን እውቀትና ክህሎት ባለማግኘታቸው በራሳቸው ተነሳሽነት የማጣትና ተስፋ የመቁረጥ እንዲሁም ከዚሁ ጋር ተያይዞ በወላጆች ፍላጐት ማጣት ምክንያት እንዲያቋርጡ መደረጋቸው ሌላው ችግር ነው። በሌላ በኩል የትምህርት ቤቶች የት/ቤት ምገባ ፕሮግራም ባልተጀመረባቸው ት/ቤቶች ለማቋረጥ ምክንያት የሚሆን አንዱ ምክንያት ነው። በስታንደርዱ መሠረት የተማሪ ክፍል ጥምርታው 50 መሆን ሲገባው በአንዳንድ ክፍሎች ከ70 እና 80 በላይ ተማሪዎች ተፋፍገው እንዲማሩ መደረጋቸው እንዲሁም ልዩ ፍላጐት ለሚሹ ወገኖች ት/ቤቶችን ለእነሱ ምቹ ካለማድረግ እና አስፈላጊውን ቁሳቁስ ስለማይማሉላቸው ትምህርት ጀምረው የሚያቋርጡት በርካታ ሕጻናት ናቸው።

1.2.2 የትምህርት ጥራትና አግባብነት

1.2.2.1 ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ምላሽ የማይሰጥና መሰተካከል ያለበት ሥርዓተ-ትምህርት

ሥርዓተ-ትምህርት የትምህርት ፍልስፍና እንዲሁም ይህን ተከትሎ በፖሊሲ ደረጃ የሚቀረፁትን የትምህርት አላማዎችን መሠረት በማድረግ ዜጋን ብቁ አድርጐ ለመቅረጽ የሚያስችለን የትምህርት ሥርአቱ ቁልፍ መሣሪያ ነው። በዚህም መሠረት ባለፉት ሃያ አራት አመታት በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ የተቀመጡ አላማዎችን መሠረት በማድረግ ሥርዓተ- ትምህርት በመቅረጽ የአገሪቱን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች በመደገፍ በኩል አስተዋጽኦ አድርጓል።

ምንም እንኳን አሁን ለደረስንበት የእድገት ደረጃ ሥርዓተ-ትምህርቱ የራሱ ድርሻ የነበረው ቢሆንም ከዚህ የበለጠ ለማሳደግ ያላስቻሉን በየትምህርት እርከኑ በርካታ ችግሮች አሉ። በሁሉም እርከን ያለው ሥርዓተ-ትምህርት አለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን መሠረት ያላደረገ፣ በየጊዜው እየተፈተሸ የማይከለስ፤ በተግባር ላይ ከማተኮር ይልቅ በንድፈ-ሃሳብ ላይ የተመሠረተ መሆኑና ለፈተና የማዘጋጀት መርህ የሚከተል መሆኑና በሀገራችን የትምህርት ሥርዓተ-

[26] UNESCO. (June, 2017). Reducing Global Poverty through Universal Primary and Secondary Education,Policy Paper 32/Sheet 44, p.7.
[27] [27]UNESCO. (2017). GLOBAL EDUCATION MONITORING REPORT 2017/2018. https://en.unesco.org/gem-report/

ትምህርት የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው። ከዚህ አንፃር የቅድመ መደበኛ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርትን ስናይ ስታንደርዱን የጠበቀ አይደለም።[28] በተለይ በገጠር አካባቢዎች ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚስማማ ተለማጭ ሥርአተ ትምህርት በማዘጋጀት ሕፃናቱን እንዲሳተፉ አማራጭ የሚያቀርብ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪም በዚህ መርሃ ግብር አሁን በት/ቤቶች እየተተገበረ ያለው ሥርአተ-ትምህርት ሕጻናቱን ንድፈ-ሃሳብ ለማስጨበጥ እንጂ ሥነ ምግባርን፣ ተግባቦት፣ በራስ የመተማመን፣ አካባቢያቸውን ብሎም አገራቸውን እንዲያውቁና እንዲያደቅሩ፣ ሙያዊ የሆኑ ጉዳዮችን፣ ወዘተ. ከእድሜያቸው ጋር የተመጣጠነ በጨዋታ መልክ የሚሰጥ ሳይሆን በተበጣጠሰና በተለይም በግል ተቋማት ከእድሜያቸው በላይ የታጨቁ እውቀቶች ለገበያ ተብሎ ከሥርአተ ትምህርቱ ውጪ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ከሌሎች አገሮች የተገለበጡ የሚመስሉ ይዘቶች የሚሰጡበት ሁኔታ በሰፊው ይታያል።

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ሥነ-ውበትን በሚገባ ያላካተተ፣ በንድፈ-ሃሳብ የታጨቀ፣ የሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ትምህርት የጐላ የባህሪ ለውጥ ያላመጣ፣ ለብዝሃነት የሰጠው ቦታ አናሳ መሆን፣ ለሙያ ትምህርቶችና ለፈጠራ ቦታ የሰጠ አይደለም።[29] በተለይ ይህ የእድሜ ክልል ለቀጣይ የትምህርትና ሥልጠና መሠረት የምንጥልበት መሆኑ እያታወቀ የቴክኖሎጂ፣ የፈጠራ፣ የሙያ፣ ወዘተ. በደረጃቸው እንዲያውቁ መደረግ ሲገባው በሥርዓተ-ትምህርቱ ውስጥ ተካቶ አናገኘውም። በግል ትምህርት ቤቶች ያለው ሁኔታ ከመደበኛው የተሻለ አይደለም።የሚሰጡት ይዘቶች ከሥርዓተ-ትምህርቱ ውጪ የሆኑና ከሕጻናቱ የእድሜ ደረጃ የሚመጣጠኑም አይደሉም። የሚዘጋጁ የመጻሕፍት ብዛት ለሕጻናቱ ለሽክምም አስቸጋሪ የሆኑ ናቸው።

አሁን ያለው የሁለተኛ ደረጃ ሥርዓተ-ትምህርት የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም ከሚል መርህ የሚነሳ አይደለም። የተዘጋጀው ሥርዓተ-ትምህርት የተወሰኑ ተማሪዎችን ለከፍተኛ ትምህርት የሚያዘጋጅ ከመሆኑም ባሻገር በአካዳሚክ ንድፈ-ሃሳብ የታጨቀና በሁለት አመት ለማጠናቀቅ የሚሞክር ነው።[30] ይዘቱም ቢሆን ከሌሎች አገሮች ጋር ሲወዳደር ከባድ እንደሆነ ጥናቶች ያረጋግጣሉ።[31] አንዳንዶቹ ይዘቶች ለመምህራኑም የሚከብዱ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ከላይ በመጀመሪያ ደረጃ እንደተጠቀሰው ትምህርቱ ከቴክኖሎጂና ከሥራ ፈጠራ ጋር ያለው ትስስር የላላ ከመሆኑ አንጻር ወጣቶች ስለቴክኖሎጂና ስለሥራ ፈጠራ በቂ ትውውቅ፣ እውቀትና ክህሎት ሳይኖራቸው ትምህርታቸውን ያጠናቅቃሉ። በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት በአብዛኛው ከተግባር ይልቅ በንድፈ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ እንዲሁም ሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር እንዲሁም ብዝሃነትን በሚገባ ያካተተ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪም ሥርዓተ-ትምህርቱ አለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ላይ የተመሠረተ አይደለም። የተማዎችንም ልዩነት የማያስተናግድና የይዘት አማራጮች (content differentiation) የሉትም።[32] ሥርዓተ-ትምህርቱን በትምህርት ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመደገፍ የተማሪዎችን የመማር ውጤት ለማሻሻል እንዲቻል ብዙ ሀብት ፈሶበት ትምህርቱ በኘላዝማ ቴሌቪዥን እየተሰጠ ይገኛል። ይሁን እንጂ አፈጻጸሙ ሲታይ የሚተላለፋበት ቋንቋ መክበድና ገለፃውም በጣም ፈጣን መሆን፣

[28] Ministry of Education. (2017.) Ethiopian Education Development Roadmap: An integrated Executive Summary (Draft).
[29] Ibid.
[30] Ibid.
[31] The World Bank. (2013). Secondary Education in Ethiopia. (p. 44).
[32] The World Bank. (2013). Secondary Education in Ethiopia. (p. 44).

የመምህሩንና የተማሪውን የሁለትዮሽ በመስተጋብር የማይፈቅድ መሆኑ፣ መምህራን በኘላዝማ ቴሌቪዥኑ ሙሉ በሙሉ እምነት በመጣል የራስን ዝግጅት አለማድረግ[33]፣ በቴክኖሎጂው ተጠቅሞ ሰፊ እውቀት ለተማሪው አለመስጠት፣ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተገቢው አደረጃጀት ፈጥሮ ሥራውን በብቃት አለመሥራት፣ አደረጃጀት በተፈጠረባቸውም በቅንጅትና በትብብር አለመሥራት፣ የባለሙያዎች እጥረት፣ ያሉትንም በአግባቡ አለመጠቀም፣ የመሠረተ ልማት አለመሟላት፣ በትናንሽ ብልሽት ለረጅም ጊዜ ኘላዝማ ቴሌቪዥኖች አገልግሎት አለመስጠት፣ ወዘተ. ችግሮች አሉበት።

1.2.2.2 የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ ያልቻለ የመምህራን ምልመላና ዝግጅት


የመምህርነት ሙያ የሰው ልጅን ለዛሬውም ይሁን ለነገ አገር ገንቢ ዜጋ አድርጐ የመቅረጽ ከባድ ኃላፊነት ያለበት የሙያዎች ሁሉ ቁንጮና የተከበረ ሙያ ነው። ይህ ከባድ ኃላፊነት ውጤታማ የሚሆነው መምህራን ሙያቸውን በማፍቀር እና በሚሠሩት ሥራ ልዩነት ማምጣት እንችላለን ብለው በውስጣቸው እምነት ከፈጠሩ ያለሙትን ግብ ለማሳካት እንደሚችሉ ጥናቶች ያሳያሉ። የመምህራን ሙያቸውን መውደድ እና በማስተማር ሙያ ልዩነት መፍጠር እችላለሁ ብሎ በራስ የመተማመን ስሜት መፍጠር (Teachers' self-efficacy) በማስተማር ሙያቸው ውጤታማ ለመሆንና የተማሪዎችን የመማር ውጤት ከፍ ወደአለ ደረጃ ለማድረስ ቅድመ ሁኔታ ነው።[34] ከዚህ መርህ አኳያ ለየደረጃው የመምህራንን ምልመላና የሥልጠና ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተል። በዚህም መሠረት 73% የመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያው ሣይክል (ከ1ኛ-4ኛ ክፍል)፤ 95% የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛው ሣይክል (ከ5ኛ-8ኛ ክፍል)፣ 93% የሁለተኛ ደረጃ መምህራን (9ኛ-12ኛ ክፍል) ለደረጃው ብቁ የሚያደርግ የትምህርት ዝግጅት እንዳላቸው የ2009 ዓ.ም. አመታዊ ስታትስቲክስ መጽሐት ያመለክታል።[35] ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ መምህራን ለደረጃው የሚጠበቀውን የትምህርት ዝግጅት የሚያሟሉ ቢሆንም ከ2006 እስከ 2009 በተካሄዱ የሙያ ፍቃድም ምዘናዎች ምዘናውን ከወሰዱት 140,435 የመጀመሪያ እና 24,063 ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ውስጥ የመቁረጫ ነጥቡን በማሟላት ያለፉት 22% መምህራን ብቻ ናቸው።[36]

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ መምህራን በተለያዩ ምክንያቶች የትምህርት ክፍለ ጊዜ ማባከን ችግር ከፍተኛ እንደሆነ ጥናት ያሳያል። መምህራን ሥራቸውን ሳይለቁ ነገር ግን ከመልቀቅ ባልተናነሰ ሁኔታ ጥናት በተደረገባቸው በ222 የገጠር፣ በ125 የከተማ በድምሩ በ347 ናሙና ት/ቤቶች ውስጥ ወደ 12% ያህሉ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት መምህራን ያለምንም በቂ ምክንያት ከት/ቤት ይቀራሉ፤ 28% ያህሉ በት/ቤት ውስጥ እያሉ ክፍል ውስጥ የማይገቡ ሲሆኑ 7% ያህሉ ከዚህ በከፋ ሁኔታ በክፍል ውስጥ ያሉ ግን የማያስተምሩ ናቸው። በአጠቃላይ ሲታይ በክፍል ተገኝተው በአግባቡ የሚያስተምሩት 51% ያህሉ ብቻ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ለትምህርት የተመደበው ውስን የጊዜ ሀብት ምን ያህል እየባከነ እንደሆነና ሀገሪቱ ከእያንዳንዱ ተማሪ የምትጠብቀው የእውቀት፣ የክህሎትና

[33] Ibid.
[34] Schleicher, A. (2015), Schools for 21st-Century Learners: Strong Leaders, Confident Teachers, Innovative Approaches, international Summit on the teaching profession, oeCd publishing. http://dx.doi.org/10.1787/9789264231191-en
[35] Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016/17), p. 88.
[36] ትምህርት ሚኒስቴር (ሰኔ/2009)። የ2009 በጀት ዓመት አቅድ ማጠቃለያ የአፈፃፀም ሪፖርት።

የአስተሳሰብ ልማት በምን ያህል የጉዳት ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል።[37] ከዚህ በተጨማሪም በ2009 ዓ.ም. ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ለመከታተል የ11ኛና የ12ኛ ክፍል ይዘቶችን የያዙ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው የመግቢያ ፈተና ከተፈተኑ 21,091 የሁለተኛ ደረጃ መምህራን መካከል 50% በላይ ውጤት ያመጡ 37.72% ብቻ ናቸው። በየትምህርት አይነቱ የመምህራን ውጤትን በተመለከተ በሚከተለው ግራፍ ተመላክቷል።

ግራፍ 16፣ በ2009 ዓ.ም. ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ለመከታተል ፈተና የወሰዱ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ውጤት




ከላይ የቀረበው ግራፍ እንደሚያመለክተው ለፈተና ከተቀመጡት የፊዚክስ መምህራን 50% እና በላይ ውጤት ያመጡት 0.69% (ከ1732 መምህራን ውስጥ 12) ብቻ ናቸው። በተመሳሳይ የኬሚስትሪ (4.34%)፣ የትግርኛ (11.64%)፣ የሒሳብ (11.86%)፣ መምህራን ብቻ 50% እና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ በመሆናቸው በአጠቃላይ ውጤቱ በጣም ዝቅተኛ ነው። የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡት የአፋን ኦሮሞ (85.41%)፣ የአማርኛ (75.02%)፣ እና የእንግሊዝኛ (59.08%) መምህራን ናቸው።[38] የሒሳብ፣ የፊዚክስ፣ የኬሚስትሪ እንዲሁም የባዮሎጂ መምህራን ውጤት ከተማሪዎች ውጤት ጋር የሚዛመድ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች በእነዚህ የትምህርት አይነቶች ያመጡት ውጤት በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ ነው። ይህም ተማሪዎች የሚማሩት ብቁ ባልሆኑ መምህራን መሆኑን ያመለክታል። የመምህራን አሠልጣጠናችንም ምን ያህል ችግር እንዳለው ያሳያል። ከዚህ በተጨማሪም በ2010 ዓ.ም. በአንላይድ ሣይንስ ዲግሪ ከተመረቁት ውስጥ ለሁለተኛ ደረጃ መምህርነት በመመልመል በሙያው ለማሠልጠን ለፈተና ከተቀመጡ 4,282 እጩዎች. ውስጥ ማለፍ የቻሉት 1,147 (26.79%) ብቻ ናቸው። ይህ የሚያመለክተው የዩኒቨርስቲ አሰልጣጠናችን ምን ያህል ችግር እንዳለበት ነው።[39]

[37] ትምህርት ሚኒስቴር (ነሐሴ/2007)። የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የ2008 ዓ.ም. መሪ እቅድ።
[38] በትምህርት ሚኒስቴር፤ የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት (2009)። የ2009 ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ምልመላ የፈተና ውጤት።
[39] በትምህርት ሚኒስቴር፤ የመምህራንና የትምህርት አመራር ዳይሬክቶሬት፤ (2010)። እጩ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ምልመላ የመግቢያ ፈተና።

1.2.2.3 እጅግ አሳሳቢ የሆነ የትምህርት ቤቶች ሁኔታ

የትምህርት ቤቶችን ሁኔታ ስናይ አብዛኛዎቹ ለሕጻናቱም ሆነ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ሂደት ምቹ የሆኑ አይደሉም። ከ2006-2008 አመታት በመጀመሪያ ደረጃ (1ኛ - 8ኛ ክፍል) እና በሁለተኛ ደረጃ (9ኛ - 12ኛ ክፍል) ትምህርት ቤቶች በውጤት፣ ግብአትና ሂደት መስፈርቶች በተደረጉ የኢንስፔክሽን ሥራዎች ውጤታቸው ከ50% በታች ከሆነ ደረጃ 1 (ስታንዳርድ የማያሟሉ)፣ ከ50%-69.99% ከሆነ ደረጃ 2 (በመሻሻል ላይ ያሉ)፣ ከ70%-89.99% ከሆነ ደረጃ 3 (ስታንዳርዱን ያሟሉ) እንዲሁም ከ90%-100% ከሆነ ደረጃ 4 (ስታንዳርዱን በከፍተኛ ደረጃ ያሟሉ) በሚል ተፈርጀዋል። የኢንስፔክሽን ውጤቱን በየክልሉ በሚከተለው ግራፍ ተመላክቷል።


ግራፍ 17፣ ከ2006-2008 አመታት የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን አፈጻጸም ደረጃ



በግራፉ ላይ እንደተመለከተው ካሉት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ በ31,594 (95.88%) ኢንስፔክሽን የተካሄደ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 28,498 (90.2%) ደረጃቸውን ያልጠበቁና ለሕጻናቱ ምቹ ያልሆኑ ናቸው፤ በተለይ 8,342 ት/ቤቶች በከፋ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ።[40] በየደረጃው ያለው አመራር እነዚህን ችግሮች ቢያውቅም ሕብረተሰቡን በማስተባበር ለችግሮቹ መፍትሔ ሲሰጥ አይታይም። ክልሎች ያሉበትን ሁኔታ ስናይ ኢትዮጵያ ሱማሌ 100%፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ 97.8%፣ አፋር 97.2%፣ ድሬደዋ 96.2%፣ ጋምቤላ 94.7%፣ ደቡብ 94.3%፣ አሮሚያ 92.3%፣ አማራ 88.8%፣ አዲስ አበባ 81.4%፣ ሐረሪ 70.8% እንዲሁም ትግራይ 66% ደረጃ አንድና ሁለት ያሉና ትምህርት ቤቶቹ ለሕጻናት ትምህርቱን ለመስጠት ምቹ ያልሆኑ መሆናቸው ያሳያል።

[40] ትምህርት ሚኒስቴር (ሚያዝያ፣ 2010)። የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን የመጀመሪያ ዙር የትምህርት ቤቶች አፈጻጸም ደረጃ ትንተና።

ግራፍ 18፣ ከ2006-2008 አመታት የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን አፈጻጸም ደረጃ



ከላይ በግራፉ እንደተመለከተው ካሉት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ በ2,532 (91.24%) ኢንስፔክሽን የተካሄደ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 2,102 (83%) ደረጃቸውን ያልጠበቁና ለሕጻናቱ ምቹ ያልሆኑ ናቸው፤ በተለይ 398 ት/ቤቶች በከፋ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ።[41] ይህ ችግር በጣም አሳሳቢ ቢሆንም በችግሩ ልክ በየደረጃው ያለው አመራር መፍትሔ ሲሰጥ አይታይም። ክልሎች ያሉበትን ሁኔታ ስናይ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ 100%፣ አፋር 100%፣ ኢትዮጵያ ሱማሌ 98.8%፣ ትግራይ 98.5%፣ ጋምቤላ 88.9%፣ አማራ 85.9%፣ ደቡብ 85.3%፣ ኦሮሚያ 79.6%፣ አዲስ አበባ 70.8%፣ ድሬደዋ 66.7%፣ ሐረሪ 50% የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ምቹ ይደሉም። በአጠቃላይ በኢንስፔክሽን ከታዩት 28,503 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ውስጥ 9.8% ብቻ ደረጃቸውን የጠበቁ ሲሆን ቀሪዎቹ 90.2% ለመማር-ማስተማሩን በብቃት ለመስጠት ብቃት የሌላቸው ናቸው። የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ጋር ሲነፃፀሩ የተሻሉ ቢመስሉም 16.98% እንጂ ቀሪ 83.02%ቱ ደረጃቸውን የጠበቁ አይደሉም። ከዚህ በተጨማሪም በገጠርና በከተማ ትምህርት ቤቶች መካከል ሰፋ ያለ የአፈፃፀም ልዩነቶች ተስተውለዋል። በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ እንዲሁም በገጠርና በከተማ ትምህርት ቤቶች መካከል ያሉ ልዩነቶች ትኩረት አድርጎ ለውጥ በሚያመጣ መልኩ መሥራ ይጠበቃል።[42]

1.2.2.4 በፖሊሲው ላይ የተቀመጠውን ያላሳካ የተማሪዎች የመማር ውጤት

ተማሪዎች በሥርአተ ትምህርቱ የተቀመጠውን የትምህርት ውጤቶች በሚፈለገው ደረጃ እንዲበቁ ለማስቻል የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ ግብር ተቀይሶ ተግባራዊ በመደረጉ የተማሪዎችን ውጤትና አስተሳሰብ እየተሻሻለ

[41] ዝኪከማሁ።
[42] ትምህርት ሚኒስቴር (ሚያዝያ፣ 2010)። የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን የመጀመሪያ ዙር የትምህርት ቤቶች አፈጻጸም ደረጃ ትንተና።

መጥቷል። ለቋንቋ፣ ለሒሳብና ሣይንስ ትምህርቶች እንዲሁም በዝቅተኛ ክፍሎች የማንበብ፣ የመረዳት የማስላት ክህሎትን ለማሳደግ ሰፊ ሥራ ተሠርቷል። ይሁንና በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው ሁሉም ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት አይነቶች 50% እና በላይ ውጤት ማምጣት እንዳለባቸው ያስቀመጠ ቢሆንም አሁን ያለን አፈጻጸም በጣም አሳሳቢ ነው።

የዝቅተኛ ክፍሎች የንባብ ክህሎት ምዘና ጥናት[43] **ውጤት በተመለከተ** እኤአ በ2010 በ2ኛ፣ በ3ኛና በ4ኛ ክፍሎች ላይ በየክልሉ በስድስት የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ከተማሪዎች የማንበብ ክህሎት ጋር ተያይዞ በተጠናው ጥናት የክህሎት ጥናቱ እንደተከናወነባቸው ክልሎች መጠነኛ ልዩነት ቢኖረውም የንባብ ክህሎት ምዘናው ውጤት ዝቅተኛ እንደነበር ለመረዳት ይቻላል። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ሕጻናት ሁለተኛ ክፍልን ሲያጠናቅቁ በሚገባ ማንበብ ካልቻሉ ሁለት የተለያዩ ነገር ግን ተከታታይ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። የመጀመሪያው ዝቅተኛ ክፍሎች በተለይም ሁለተኛ ክፍል ለሚቀጥሉት የትምህርት ደረጃዎች መሠረት በመሆኑ ሕጻናት ሦስተኛ ክፍል ሲደርሱ ማንበብ ካልቻሉ በቋንቋም አንብቦ ለመረዳት ከመቸገራቸውም ባሻገር ሌሎች ትምህርቶችን መከታተል አይችሉም። ሁለተኛው ችግር ደግሞ በቀጣይ ክፍሎች ያሉ መምህራን የተጨናነቀውን ሥርዓተ-ትምህርት በመሸፈን ላይ ትኩረት የሚያደርጉ እንጂ የማንበብ ችግር ያለባቸውን ሕጻናትን ተረድተው ክፍተታቸውን በመሙላትና ለማገዝ የሚጨነቁ ባለመሆናቸው ሕጻናቱ ምንም ሳያውቁ በቅብብሎሽ ወደቀጣዮቹ ክፍሎች እንዲያልፉ ወይም ደግሞ እንዲደግሙ ይደረጋል።[44]


የዝቅተኛ ክፍሎች የሂሳብ ክህሎት ምዘና ጥናት[45] **ውጤት በተመለከተ** እስካሁን ሀገር አቀፍ ደረጃ ከተደረጉት የትምህርት ቅበላም ሆኑ ሌሎች ጥናቶች በተሻለ አመርቂ የተማሪዎች ውጤት የታየው እኤአ በ2014 በተካሄደው የዝቅተኛ ክፍሎች የሂሳብ ክህሎት ምዘና ነው። በ11 የምዘና ፈርጆች ተመዝኖው ውህድ አማካይ ውጤቱ 71.92% ሆኖ ተመዝግቧል። ይህ ከፍተኛ ውጤት የሚያስገነዝበው ተማሪዎቻችን ሂሳብ ትምህርትን ለመማርና የላቀ ውጤት ለማምጣት የሚያስችል በቂ መሠረታዊ ዕውቀት ያላቸው መሆኑንና ከዝቅተኛ ክፍሎች ጀምሮ የክፍል መማር ማስተማሩ በጠንካራ የክፍል ተከታታይ ምዘና ቢታገዝ በዚህ ደረጃም ሆነ በወደፊት ሕይወታቸው ጥሩ ብቃት ያላቸው ተመራማሪ ዜጎች ማፍራት የሚያስችል መሠረት ያለ መሆኑን ነው።

የ4ኛና 8ኛ ክፍሎች የትምህርት ቅበላ ጥናቶች[46] አማካይ ውጤት ከ50% በታች የሆነ፣ ብዙም ለውጥ ሳያሳይ የቀየ ነው። እ.ኤ.አ በ2015 በአምስተኛው የትምህርት ቅበላ ጥናት የወሰዱት የ4ኛና የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤት

[43] EGMA 2010
[44] The World Bank. (2018). Learning to Realize Education's Promise, p. 74.
[45] EGMA 2014
[46] Ethiopian National learning Assessment Grade 4 & 8 (2011) and (2015)

እንደዚሁ ብዙም መሻሻል አያሳይም። ውጤቱም ማለትም 50% እና በላይ ውጤት ያመጡት በሚከተለው ግራፍ ተመላክቷል።[47]

ግራፍ 19፣ የ4ኛ ክፍልና የ8ኛ ክፍል የትምህርት ቅበላ ጥናት ውጤቶች /50% እና በላይ ውጤት ያመጡ/




በግራፉ እንደተመለከተው በ4ኛ ክፍል ምዘና ከግማሽ በላይ ተማሪዎች (51.90%) በሒሳብ ትምህርት 50% እና በላይ ውጤት ያመጡ ሲሆን ከሌሎቹ የትምህርት አይነቶች ብዙ ተማሪ ያለፈበት የትምህርት አይነት ነው። በንባብ 44.9% ተማሪዎች የተሻለ ብዙ ተማሪዎች በማሳለፍ ይከተላል። እንግሊዝኛ (27.40%) እና የአካባቢ ሣይንስ (31.80%) ዝቅተኛ ውጤት የተመዘገበባቸው ናቸው። የአራቱ የትምህርት አይነቶች አማካይም ዝቅተኛ (36.60%) ነው። የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤት ከአራተኛ ክፍል ውጤት የከፋ ነው። በሁሉም የትምህርት አይነቶች ማለትም እንግሊዝኛ (28.90%)፣ ሒሳብ (18.40%)፣ ፊዚክስ (32.60%)፣ ባዮሎጂ (42.80%) እንዲሁም ኬሚስትሪ (28.20%) የተመዘገበው ውጤት ከግማሽ በታች ነው። አማካይ ውጤቱም (25.20%) በጣም ዝቅተኛና አሳሳቢ ጉዳይ ነው።

በ10ኛና 12ኛ ክፍሎች ላይ የተሰሩት የትምህርት ቅበላ ጥናቶች[48] ውጤቶችም በተመሳሳይ የትምህርት ስርዓቱ የደረሰበትን የትምህርት ጥራት ደረጃ አሳይተዋል። እኤአ በ2016 በተደረው የትምህርት ቅበላ ጥናት የ10ኛ ሆነ የ12ኛ ክፍል ውጤቶች አሳሳቢ መሆናቸውን ከሚከተለው ግራፍ መረዳት ይቻላል።

[47] Ethiopian National learning Assessment Grade 4 & 8 (2016).
[48] NEAEA. (2017). *Ethiopia Third National Learning Assessment of Grades 10 and 12 Students Achievements.* (Unpublished).

ግራፍ 20፣ የ10ኛ ክፍልና የ12ኛ ክፍል የትምህርት ቅበላ ጥናት ውጤቶች /50% እና በላይ ውጤት ያመጡ/



ከላይ ከግራፉ መረዳት እንደሚቻለው የሁለቱም ክፍሎች የትምህርት ምዘና ውጤቶች እጅግ አሳሳቢ መሆኑን ነው። ከሁለቱ ክፍሎች ደግሞ የ10ኛ ክፍል የትምህርት ቅበላ ውጤት እጅግ በጣም ዝቅተኛ (9.1%) ነው። የ10ኛ ክፍል የየትምህርት አይነት ውጤቶች ስንመለከት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ጀምሮ እንደቅደም ተከተላቸው ፊዚክስ 4.6%፣ እንግሊዝኛ 10.6%፣ ሒሳብ 11.9%፣ ኬሚስትሪ 14.8%፣ ባዮሎጂ 22.9% ውጤት ተመዝግቧል። የ12ኛ ክፍል ውጤት በአንጻራዊነት የተሻለ (26.6%) ቢሆንም ውጤቱ አሳሳቢ ነው። የየትምህርት አይነቶቹን ውጤት ስናይ በባዮሎጂ ወደ ግማሽ የተጠጉ (48.5%) ተማሪዎች 50% እና በላይ ውጤት አስመዝግበዋል። ከዚህ በተጨማሪ ፊዚክስ 7.4%፣ ሒሳብ 27.2%፣ ኬሚስትሪ 34.3%፣ እንግሊዝኛ 37.4% ውጤት ማስመዝገባቸው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በፖሊሲው የተቀመጠው 50% እና ውጤት አለማስመዘገባውን የሚያመለክት ነው። ይህ በሁለቱም ደረጃዎች የተደረገው የትምህርት ምዘና ጥናት ከእ.ኤ.አ. 2013 ከተደረገው ጥናት ጋር ሲነጻጸር የተማሪዎች አማካይ ውጤት ከመሻሻል ይልቅ ጭራሽ ያሽቆለቆለ ነው።

በአጠቃላይ በሁሉም የትምህርት ምዘና ጥናት ዓይነቶች የሴት ተማሪዎች ውጤት በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ከወንድ ተማሪዎች ውጤት ጋር ሲነፃጸር ያነሰ መሆኑ እና የታዳጊ ክልሎች የተማሪዎች ውጤት ከሌሎች ክልሎች የተማሪዎች ውጤት ጋር ሲወዳደር ዝቅተኛ መሆኑ ተረጋግጧል። ለውጤት መጨመር ወይም መቀነስ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ከተማሪ፣ ከመምህራን፣ ከርዕሰ መምህራንና ወላጆች ጋር ግንኙነት ያላቸው ተለዋዋጮችም በጥናቱ ተለይተዋል። ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የተማሪዎች ቤተሰብ ነባራዊ ሁኔታ፣ የተማሪዎችን የትምህርት መሳሪዎችን አለመሟላት፣ በቤት ውስጥ የተለያዩ መርጃ መሳሪዎችን ማቅረብ አለመቻል፣ የትምህርት ቤቶች ከተማሪዎች መኖሪያ አካባቢ ያለው ርቀት፣ ልጆችን በቤት ውስጥ መርዳት አለመቻል፣ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው። የተማሪዎች የመማር ፍላጎት፣ ከትምህርት ቤት የመቅረት እና የመድገም ሁኔታዎች እንደ ችግሩ መንስዔዎች ተወስደዋል። ከመማር መስተማር ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ጉዳች የሱፐርቪዥን አገልግሎት ውስንነት፣ የስራ ላይ

ስልጠና በበቂ ሁኔታ ለመምህራን አለመሰጠቱ፣ የትምህርት ማበልፀጊያ ማእካላት አለመደራጀት እና በትምህርት ቤቶች አካባቢ ለመምህራን መኖሪያ ቤት እጥረት እንደ ችግር መንስኤነት ተወስደዋል። የስርዓተ ትምህርት መሳሪያዎች ማለትም የሂሳብ፣ የሳይንስ እና የአፍ መፍቻ ቋንቋ የመምህሩ መምሪያ በበቂ ሁኔታ አለመሟላት፣ የትምህርት ቤት አመራር የትምህርት ቤቱን የውስጥ ገቢ በተገቢው መልኩ ያለማሳደግ እና የትምህርት ቤቱን የስነ ምግባር ችግር መኖሩ ሰኬት እንዳይመጣ እንቅፋት ሆነዋል። የምዘና ውጤቱን በየደረጃው ያለው አካል ተቀብሎ ለማሻሻል ጥረት ማድረግ ሲገባው ቅድመ መደበኛ-ወላጅን፤ የመጀመሪያ ደረጃ-ቅድመ መደበኛን፣ ሁለተኛ ደረጃ-የመጀመሪያ ደረጃን፤ ዩኒቨርስቲ-ሁለተኛ ደረጃን፤ ኢንዱስትሪው-ተቋማትን አንዱ ሌላውን እየኮነነ ራሱን የመፍትሔ አካል ሲያደርግ አይታይም። በሌላ በኩል እያካሄድን ያለው ምዘና በአለም ላይ የት ደረጃ እንዳለን የሚያሳይም አይደለም። እስካሁን በአለም አቀፍ በሚካሄዱ የትምህርትና ሥልጠና ምዘናዎች ተሳትፈን የምናውቅ ባለመሆኑ ችግሮቻችንን ለይተን በአለም አቀፍ ተወዳዳሪነት አቅም ለመፍጠር አልቻልንም።

1.3 ሚናቸውን በሚገባ ተገንዝበው ድርሻቸውን ያልተወጡ የአጠቃላይ ትምህርት የባለድርሻ አካላት

1.3.1 ተማሪዎች

በትምህርት ሥርአታችን ውስጥ ዋናው ተዋናይና ተጠቃሚ ተማሪ ነው። እስካሁን በተሰሩ ሥራዎች ለምን እንደሚማሩ አውቀው የሚጠበቅባቸውን ጥረት የሚያደርጉ፣ ችግሮችን በዲሞክራሲያዊ አግባብ የመፍታትና ለውጤት የሚተጉ፣ የት/ቤትን ህግና ደንብ አክብረው ትምህርታቸውን የሚከታተሉ፣ የተፈጠሩ አደረጃጀቶችን በመጠቀም በጋራ የሚደጋገፉ ተማሪዎች ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ይሁንና የእነዚህ መልካም ተማሪዎች ሥራና አርአያት ጥላ የሚያጠሉ የሥነ ምግባር ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ጉዳይ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል። እነዚህ ተማሪዎች የሚማሩበትን አላማ በውል ያልተረዱ፣ እውቀትና ክህሎት ጨብጦ ከመውጣት ይልቅ ከክፍል ክፍል መሸጋገርን ብቻ እንደስኬት የሚቆጥሩ፣ በሀገሪቱ እየተፈጠሩ ያሉ መልካም እድሎችን ተገንዝቦ እራስን በትምህርትና በሥነምግባር አንፃ የዚህ ለውጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ ለመሆን ዝግጁነት ከመፍጠር ይልቅ የባዕድ ሀገር ናፋቂ የሆኑ ትምህርት አቋርጠው ወደተለያዩ አገሮች መሄድ የሚመኙ፣ አደረጃጀቶችንና ተጨማሪ የማብቂያ ስርአቶችን ለትምህርታቸው ስኬት አቅም አድርገው የማይወስዱ፣ በተለያዩ ሱሶች የተጠመዱ፣ ወዘተ. ከመሆናቸውም ባሻገር ችግሮች እየቀነሱ መምጣት ሲገባቸው የትምህርት ሥርአታችን ወሳኝ ችግር እየሆነ መጥቷል። ከዚህ በተጨማሪ ከቅድመ መደበኛ ጀምሮ ስለሥራ ፈጠራ መሠረታዊ እውቀት ስላላስጨበጥናቸው ከሥራ መፍጠር ይልቅ ሥራ ጠባቂ እንዲሆኑ ምክንያን ሆኗል። በተለያዩ ሱሰ አስመጪዎች በመጠመድ አልባሌ ቦታ የሚውል ተማሪ ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ይህ ደግሞ ሕጻናትንና ወጣቶችን ከታች ጀምሮ በሥነ ምግባር አንፀንና ገንብተን እንዲያድጉ ባለማድረጋችን ሰውን የማክበር፣ እርስ በርስ የመረዳዳት፣ የመደማመጥ፣ ባህልን የመጠበቅ፣ ወዘተ. መልካም ባህሎቻችን እንዲሸረሸሩ እያደረገ ነው።

1.3.2 *መምህራን*

ከፍ ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመምህርነት ሙያ የነገ አገር ተረካቢ ዜጐችን የመቅረጽ ከባድ ኃላነት ያለበትና የተከበረ ሙያ ነው። በመሆኑም ባለፉት አመታት በተሠሩ ሥራዎች መምህራን መራሄ ሙያውን አክብረውና ተገቢውን ስነምግባር ተላብሰው የሚሰሩና በመማር ማስተማሩ ሂደት የተቻላቸውን ሁሉ በማድረግ ተማሪዎቻቸውን በማብቃት ኃላፊነታቸውን የሚወጡ መምህራን ቁጥር በየጊዜ እየጨመረ መጥቷል። በተለይ ሠራዊት በተገነባባቸው ትምህርት ቤቶች የተማሪ ውጤትን ለማሻሻል በተደረገው ጥረት ካስቀመጡት ግብ በላይ ውጤት ማሻሻል ተችሏል። በዚህም ልክ በሞዴልነት የሚታዩ መምህራን ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። በአንፃሩ የመምህርነት ሙያ የተማሪዎችን የወደፊት ህይወት የመቅረፅና በሀገራችን ልማትና ሁለንተናዊ እድገት ላይ የማይተካ ሚና ያለው ሀይል መሆኑን በተደጋጋሚ በተደረጉ ውይይቶች ከመግባባት ቢደረስም ተግባሩን በዚህ ልክ ሲሠራ የማይታየው መምህር ቁጥር ቀላል አይደለም። ተማሪዎችን መክሮና ደግፎ በትምህርት ሥርዓቱ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ወሳኝ ሥራው ሆኖ ሳለ '**ተማሪዎች የመማር ፍላጎት የላቸውም**' በሚል ጉዳዩን ውጪያዊ አድርጎ የመግፋት ሁኔታዎች አሁንም ይንፃባረቃሉ። በተጨማሪም '**ሁሉም ተማሪ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር መማር ይችላል**' የሚል እምነት ጨብጦ ተማሪዎችን በተከታታይ ምዘናና በአሣታፊ የትምህርት አቀራረብ ለማብቃት በሙሉ ተነሳሽነት ያለመንቀሳቀስ፣ ከሌሎች የሥራ ባልደረቦችና ባለድርሻ አካላት ጋር ተባብሮ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን በማመን ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት አለማድረግ፣ በትምህርት ቤቶች የተፈጠሩ አደረጃጀቶችን ለተማሪው ውጤትና ስነ ምግባር የተጣሉ ግቦችን ማስፈፀሚያ መሣሪያ አድርጐ አለመውሰድ፣ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ ፕሮግራምን ትኩረት ሰጥቶ አለመከታተልና ከጥቅም ጋር ብቻ አያይዞ ማየት ችግሮች ይታያሉ።[49]

1.3.3 **የትምህርት አመራሩ**

የትምህርት አመራሩ በትምህርት ሥርአቱ ውስጥ የሚታዩትን ችግሮች በመለየትና መፍትሔ በመስጠት የትምህርትና ሥልጠና ጥራትና አግባብነት የማረጋገጥ ሥራን በውጤታማነት መምራት ይጠበቅበታል። የትምህርትና ሥልጠና ውጤት የትምህርት አመራሩ ነፀብራቅ ነው። አመራሩ የትምህርት ባለድርሻ አካላትን በሚገባ አደራጅቶና ሠራዊት ገንብቶ በመራባቸው ጥቂት ተቋማት የተሻሉ ውጤት እንደተመዘገቡ በተለያዩ ጊዜያቶች በተደረጉ የመስክ ግምገማዎች ማወቅ ተችሏል። ከላይ የተጠቀሱት የትምህርትና ሥልጠና ሥርአታችን ችግሮች የትምህርት አመራሩ በየጊዜ እየፈታ መፍትሔ መስጠት ባለመቻሉ የተፈጠሩ ችግሮች ናቸው። እነዚህ ችግሮች ከአመለካከትና ክህሎት ችግሮች የሚመነጩ ናቸው። ከአመለካከት አንፃር የአገልጋይነት ስሜት መጓደል፣ ጠባቂነትና አድርባይነት፣ የመንግሥት የሥራ ሰዓትን ባአግባቡ ያለመጠቀም ይስተዋላሉ። ከክህሎት አኳያም ለደረጃው የሚመጥን የአመራር ብቃት ይዞ አለመገኘት፣ ዋና ዋና የእቅድ ዶክመንቶችን መሠረት አድርጐ ደረጃውን የጠበቀ ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደ ሥራ አለመግባት፣ የጠራ ሪፖርት አዘጋጅቶ አለማቅረብ፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለይቶ በመቀመርና በማስፋት የትምህርት ተቋማትን የተቀራረበ ብቃት እንዲኖራቸው አለማድረግ፣ መቀረፍ ያለባቸው ችግሮች ናቸው። ከግብአት

[49] Aike, W.M. and Ayle, B.K. (2015). State of Service Delivery in Ethiopian Primary Schools: Findings from the Ethiopia Education Service Delivery Indicator Survey. Middle Eastern & African Journal of Educational Research, Issue 16, pp. 34-58.

አኳያ ከላይ እንደተገለፀው አብዛኛዎቹ ትምህርት ቤቶች ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆናቸው የትምህርት አመራሩ ትኩረት ሰጥቶ በግብአት ለማሟላት ጥረት ያለመደረጉን የሚያመለክቱ ችግሮች ናቸው።

1.3.4 ወላጆች

በትምህርት ጥራት መጠበቅና በተማሪዎች ውጤት መሻሻልና ባህሪ ለውጥ ላይ ወላጆች እና መላ ህብረተሰቡ የማይተካ ሚና አላቸው። በዚህም መሠረት ህብረተሰቡ ትምህርት ቤቶችን በመገንባትና አንዳንድ ግብአቶችን በማሟላት ረገድ ከፍተኛ ሥራ ሠርተዋል፤ እየሠሩም ይገኛሉ። የአፈፃፀም ደረጃው ከቦታ ቦታ የተለያየ ቢሆንም በአካባቢያቸው ያሉትን የልማት ሠራዊት አደረጃጀት በመጠቀም እድሚያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት ወደ ትም/ቤት እንዲገቡ በማድረግ፣ በትምህርት ላይ ያሉትም ትምህርታቸውን እንዲከታተሉና እንዳያቋርጡ ከፍተኛ ሥራ ሰርተዋል። ይሁን እንጂ ልጆቹን ማስተማርና መከታተል የትምህርት ቤቶችና የመምህራን ሃላፊነት ብቻ አድርጎ መውሰድ እና የወላጅን ሚና አሳንሶ ማየት፣ የትምህርትን ፋይዳ አሳንሶ የማየት ወይም ትምህርት ቁልፍ የልማት መሳሪያ ነው ብሎ አለመውሰድና ከዚህም የተነሳ የትምህርት ተሳትፎና ጥራት ፓኬጆችን በማረጋገጥ ሂደት የሚጠበቀውን ያህል እንቅስቃሴና ተሳትፎ አለማድረግ፣ በልጆቻቸው የትምህርት ጉዳይ ወደ ትምህርት ቤት ሲጠሩ አለመምጣት፣ የልጆችን ትምህርት አለመከታተል፣ ትምህርት ቤትን እንደ ማቆያ ቦታ አደርጎ መውሰድ፣ ከደላላዎች ጋር በመመሳጠር ልጆቻቸውን ከትምህርት ገበታ እያስጣሉ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ለሚደረግ ህገ ወጥ ዝውውር ተጋላጭ የማድረግ ሁኔታ አሁንም በአንዳንድ ወላጆች ላይ የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው።[50]


2. ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና

2.1 ፍትሐዊነትና ተደራሽነት ያላረጋገጠ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የአገራችን ኢኮኖሚ በዝቅተኛና በመካከለኛ ደረጃ የሚያስፈልገውን የሠለጠነ ሙያተኛ በማፍራት እና ቴክኖሎጂ በማቅረብ በኩል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። በመሆኑም ዘርፉ አገራቱን ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪው በምታደርገው የኢኮኖሚ ሽግግር ለኢንዱስትሪው አቅምና መሠረት የሚጥል ነው። ከዚህ አኳያ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው ከወጣ በኋላ ላለፉት አመታት በዘርፉ በተለያዩ የሙያ አይነቶች ሰፊ የአቅም ግንባታ ሥራ ሲሰራ ቆይቷል። ከ2005 እስከ 2009 ዓ.ም. ያለውን ተሳትፎ በሚከተለው ግራፍ ማየት ይቻላል።


[50] ትምህርት ሚኒስቴር። (ነሐሴ/2007)። የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የ2008 ዓ.ም. መሪ እቅድ።

ግራፍ 21፣ ከ2005 እስከ 2009 ዓ.ም. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተሣታፊዎች በአሃዝ



ከግራፉ መረዳት እንደሚቻለው ከ2007 ዓ.ም. ውጭ በሌሎች አመታት የነበረው የተሣትፎ እድገት በጣም አዝጋሚ ነው። የጾታን ተሣትፎ ስንመለከድ በሁሉም አመታት የሴቶች ተሣትፎ ከ50% በላይ እንደሆነ ያመለክታል። በሌላ በኩል ወጣቶች 10ኛ ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ 80% የሚሆኑት ወደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በመሳተፍ ሥራ እንዲፈጥሩ ኢኮኖሚውን እንዲደግፉ ከሚለው አንፃር ሰናየው ሰፊ ክፍተት ይታያል። ለአብነት ያህል በ2008 ዓ.ም. ለ10ኛ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ፈተና የተቀመጡት 1,030,097[51] ሲሆኑ በ2009 ዓ.ም. ወደ መሰናዶ ትምህርት 11ኛ ክፍል የገቡት 265,339 ናቸው።[52] ይህ የሚያመለክተው ወደ 824,000 ሠልጣኞች መሳተፍ ሲገባቸው አሁን በመደበኛ ቴክኒክና ሙያ የሰለጠኑት 302,083 ብቻ ናቸው። የተሳትፎው ዝቅተኛ መሆን ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የማስፋፋት ሥራችን ጋር የተያያዘ ነው። እስካሁን በየወረዳው ያስፋፋነው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን ከሚከተለው ግራፍ ማየት ይቻላል።

ግራፍ 22፣ የ2009 ዓ.ም. በክልል ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ብዛት



[51] Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2015/16), p. 72.
[52] Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016/17). GE 2009_Annex.

ከግራፉ እንደምንረዳው በአገር አቀፍ ደረጃ ካሉት 1027 ወረዳዎች ውስጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ያላቸው 367 ወረዳዎች ብቻ ናቸው።[53] ይህም 35.74% ያክሉ ማለትም 660 ወረዳዎች አገልግሎቱን አላገኙም ማለት ነው። የክልሎችን አፈጻጸም ስናይ ኢትዮ-ሱማሌ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ድሬዳዋ፣ አዲስ አበባና ቤንሻንጉል ጉሙዝ እንደቅደም ተከተላቸው በከፋ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪም ተቋማቱ ስታንደርዱን በጠበቀ ግብአት ያልተሟሉና አብዛኛዎቹ በትልልቅ ከተሞች የተቋቋሙ ናቸው።[54] በዚህ አፈጻጸማችን ከተጓዝን ኢኮኖሚ የሚፈልገውን የሰው ኃይል ማቅረብ ካለማቻላችንም በላይ ሠልጥኖ ሥራ በመፍጠር ራሱንና አገሩን የሚጠቅም ወጣት ከማበራከት ይልቅ ሥራ አጥ ወጣት እየፈጠርን መሄዳችን አይቀርም። በአጠቃላይ የተቋማቱ ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ከአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን የሚያጠናቅቁ ወጣቶችን የመቀበል አቅም የላቸውም። ባሉትም ተቋማት የመጠቀም ሁኔታ ሲታይ ከዋና ከተሞች ውጪ ባሉ ተቋማት ያለው ተሳትፎ አጥጋቢ አይደለም። ይህም የሚመነጨው በሕብረተሰቡ ዘንድ ስለተቋማቱ ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆኑ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ።[55]

2.2 የውጤት ተኮር ሥልጠና ጥራትና አግባብነት

2.2.1 የቅንጅትና የውህደት ችግር ያለበት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕቀፍ

ቀደም ሲል ለረጅም አመታት በብዙ አገሮች የነበረው የትምህርትና ስልጠና ስርአት ዜጎች በአንድ በተወሰነ ጊዜ በትምህርትና ስልጠና ማእከላት በሚያሳልፉት ጊዜ ብቻ ላይ ተመስርቶ ብቃታቸው ይለካ ነበር። ከትምህርትና ሥልጠና ውጪ በስራ ዓለም ላይ የሚያካብቱት ከፍተኛ የሆነ ተጨማሪ የብቃት ማረጋገጫ ስርአት ባለመኖሩ የእድሜ ልክ ትምህርትና ስልጠናን እውቅና የሚሰጥ ስርአት አልነበረም። በተጨማሪም በአንድ የሙያ ዘርፍ የተገኘን ብቃት ከሌላ የሙያ ዘርፍ ካለ ብቃት ጋር ለማወዳደርና ለመለካት ወይም የጎንዮሽ ተያያዥነትን (horizontal permeability) ለማሳየት እና በሌላ በኩልም በአንድ ዘርፍ ውስጥ ያሉ ተመሳሳይ ብቃቶችን ወይም ዓምዳዊ ተያያዥነት (vertical permeability) ለማሳየት የሚቻልበት አሰራር አልነበረም። ይህን ችግር በመሠረታዊነት ለፈታ እንዲችል በአገራችን ውጤት ተኮር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ በመቅረጽ በተበጣጠሰና በተበታተነ መልኩ ይተገበር የነበረውን የስልጠና አሰጣጥና የብቃት ደረጃ ሰብሰብ በማድረግና ወጥነት ባለው መልኩ ለመተግበር እንዲቻል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕቀፍ እንዲቀረጽ ተደርጓል። የብቃት ማዕቀፉ በአምስት ደረጃዎች የሚፈለገው የሰው ኃይል ሊኖረው የሚገባውን ብቃት የሚገልጽ ሰነድ ነው። በተለያየ ሁኔታ፣ ጊዜና ቦታ የሚሰጡ ስልጠናዎችን በአንድ ማዕቀፍ እንዲታዩና ተበታትኖ የነበረውን የትምህርትና ስልጠና ስርዓትና ስልጠናዎች ያላቸውን ደረጃ አንድ ላይ ያመጣና በማዕቀፉ የብቃት መግለጫዎች የሙያ ብቃት ደረጃ እንዲለይ ያደረገ ነው:: ማንኛውም ስልጠና ይህን የብቃት ማዕቀፍ መነሻ አድርጎ በሚዘጋጀው የሙያ ደረጃ መሰረት የሚሰጥ መሆኑና በመጨረሻም በሙያ ብቃት ምዘና የሚቋጭ መሆኑ ስርዓቱ የራሱ ቼክ ኤንድ ባላንስ (self Check and

[53] TVET Agency (2017). Project for Wereda Based TVET Accessibility Ethiopia, p. 12.
[54] Ministry of Education. (2017.) Ethiopian Education Development Roadmap: An integrated Executive Summary (Draft).
[55] Ibid..

Balance) ያለው መሆኑን ያሳያል። በተጨማሪም ሀገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማዕቀፍ በውጤት ተኮር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂያችን ላይ የተቀመጡትን የተቀናጀና የተዋሀደ ስርአት፤ የግልጽነት፤ በብቃት ደረጃዎች መካከል ያለውን የጎንዮሽና የአግድሞሽ ተያያዥነት፤ የተለማጭነትና የፍትሀዊነት መርሆዎችን ለመተግበር እንደ ማጣቀሻ የሚታይ ነው። የብቃት ማዕቀፉ ምንም እንኳን ከላይ ለመጥቀስ የተሞከሩ ጥቅሞች ቢኖሩትም ከአጠቃላይ የትምህርት ዘርፍና ከፍተኛ የትምህርት ዘርፍ ጋር የተናቦትና የቅንጅት ክፍተት አለበት። በሦስቱ ዘርፎች መካከል ያለው የቅንጅትና የውህደት ችግር ሰልጣኞች ወደ ቴክኒክና ሙያ ለመግባት ፍላጎት እንዳይኖራቸውና በስርዓቱ ውስጥ አልፈው ወደ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ለመድረስ ግልጽና አበረታች ያልሆነ ስርዓት መኖሩ መስተካከል ያለበት ነው።

2.2.2 ከኢንዱስትሪው ፍላጐት ጋር ያልተሳሰረ የሙያ ደረጃ ምደባ

ከግብዓት ተኮር ወደ ውጤት ተኮር ስርዓት በተደረገው ሽግግር ሂደት ዋነኛ መሳሪያውና የአገራችንን ልማት ለማሳደግ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የተከናወነው ተግባር የሙያ ደረጃ ምደባ ነው። የሙያ ደረጃዎች ዋነኛ ባለቤት ኢንዱስትሪው ወይም ቀጣሪ ሲሆን እስከ አሁን ባለው ሁኔታ የሙያ ደረጃውን በባለቤትነት የሚመራ የኢንዱስትሪ አደረጃጀት ያልተፈጠረ በመሆኑ መሪነቱን የትምህርትና ስልጠና ዘርፉ ይዞት ይገኛል። ይህም ከልማት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመቀናጀት ደካማም ቢሆን ካለው ኢንዱስትሪ ባለሙያዎችን በማሰባሰብ የሙያ ደረጃ በማዘጋጀት ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን ብቃት ከሰው ሀብት ልማት ጋር የማስተሳሰር ሥራ እየተሰራበት ይገኛል። ባለፉት አመታት 800 የሚደርሱ ሙያዎች የሙያ ደረጃ የወጣላቸው ሲሆን ይህም በአለም አቀፍ ደረጃ ከተቀመጠው የሙያ ደረጃ ብዛት (ILO Standard) አኳያ ሲታይ ቁጥሩ ብዙ ነው። ሆኖም ግን እነዚህ የተዘጋጁት ስታንደርዶች ከኢንዱስትሪው ፍላጐት ጋር በሚፈለገው ደረጃ የተሳሰሩ ከመሆናቸው አንጻር ክፍተት ያለባቸው ሲሆኑ በዋነኛነት ምክንያቱ የሙያ ደረጃዎችን ዝግጅት ሂደት በባለቤትን የሚሸከም የኢንዱስትሪ አቅም አለመፈጠሩና አደረጃጀቱም አለመኖሩ ነው።[56]

2.2.3 ፈጠራን የማያበረታታና ከሥራ ጋር ያልተቀናጀ ሥርዓተ-ትምህርት

አገራችን ለምታካሂደው ሁለንተናዊ እድገት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በተለያዩ ዘርፎች የሚያስፈልገው ብቁ የሰው ኃይል፣ ቴክኖሎጂ እንዲሁም የኢንዱስትሪ አሠራር እውቀት ወሳኝ ነው። በዝቅተኛ፣ በመካከለኛ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል አስፈላጊ ነው። የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በዝቅተኛ፣ በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ ቴክኒሽያኖችንና መሪ የእድ-ጥበብ ሰዎች በስፋት ማምረት ይጠበቅበታል። በመሆኑም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከቅድመ መደበኛ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ በማስተሳሰር ብቁ ሠልጣኞችን ማፍራት ይገባል። ከዚህ አኳያ ሲታይ ሕጻናትን ከቅድመ-መደበኛ ትምህርት ጀምሮ ለእድሜ ደረጃቸው የሚመጥን የሙያ ትምህርት እንዲያውቁና የሥራ ፍቅርን፣ የፈጠራን፣ ሙያ፣ ወዘተ. እየተለማመዱ መምጣት ሲገባቸው በዚህ መልክ እየተገበርን አይደለም። ወደ ሥልጠና የገቡትም ሠልጣኞች ፈጠራን በይበልጥ በሚያበርታታ

[56] Ministry of Education. (2017.) Ethiopian Education Development Roadmap: An integrated Executive Summary (Draft).

መልኩ እየሰለጠኑ አይደለም። በየተቋማቱ በተለይም በገጠር አካባቢ የሚዘጋጁት ኘሮግራሞች ለሥራ አለም ዝግጁ የሚያደርጉ አይደሉም። አብዛኛዎቹ ስልጠናዎች የስራ ገበያን መሰረት በማድረግና የስራ ገበያውን በአግባቡ አጥንቶ በዚሁ መሰረት የሚሰጡ ሳይሆን በግምት የሚሰጡ በመሆናቸው ሰልጣኞች ከስራ ጋር እንዳይተሳሰሩ ከአደረጉት ምክንያቶች መካከል ነው። የሥራ ገበያ መረጃ፣ የሥልጠና መሣሪያ እና የተቋማት ማስፋፊያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሠልጣኞች ከሥልጠና በኋላ ወደ ሥራ እንደሚገቡ ማረጋገጫ ሆኖ ሳለ በዚህ ላይ እየተሠራ ያለው ሥራ በአቅም ውስንነት እና በአደረጃጀት ምክንያቶች ተገቢው ትኩረት አለማግኘቱ አተገባበሩ ከፖሊሲውና ከስትራቴጂው አቅጣጫ ክፍተት ያለበት መሆኑን መረዳት ይቻላል፣፣ ከዚህ በተጨማሪም ወደ ዘርፉ ለመደበኛ ሥልጠና ገብተው የሚሰለጥኑትም ወጣቶች አብዛኛዎቹ ለመመዘን ፍላጐት የሌላቸው ሲሆኑ ከተመዘኑትም ውስጥ የብቃት ፈተና የማያልፉት ቁጥሩ ብዙ (31.3%) ነው። ከሥልጠናው ብቃት ችግር አኳያም በራሳቸው ሥራ ከመፍጠር ይልቅ ሥራ ሲጠብቁ ይስተዋላሉ ለዚህም ዋናው ምክንያቱ የኢኑተርፕነርሺፕ ስልጠና አለመጠናከሩ ነው። በዚህ ምክንያትም አብዛኛዎቹ ወደ ሥራ አለም ሲገቡ አይታይም።


2.2.4 ኢንዱስትሪውን በእምነት ያልተቀበው የትብብር ስልጠና

የትብብር ስልጠና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና በኢንዱስትሪው የጋራ ትብብር የሚሰጥ ስልጠና ሲሆን ሰልጠኞች በስራ ቦታ ላይ በመሰልጠን ኢንዱስትሪው በሚፈልገው ቅርፅ ተቀርፀው ስለሚወጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራትና አግባብነት ማረጋጫው አንዱ ዘዴ ነው። የስልጠናውን 70 በመቶ የሚሸፍነውን በስራ ቦታ ከኢንተራፕራይዞችና ኢንዱስትሪዎች ጋር በትብብር የሚሰጥ እንዲሁም የስልጠናውን ጥራት ለማረጋገጥ የተቋማት መሠረታዊ ብቃቶች ላይ 30 በመቶ የማሰልጠን ድርሻ በብቃት እንዲወጡ አገር አቀፍ የተቋማት ብቃት ስታንዳርድና የትብብር ሥልጠና መስጫ ቦታ ስታንዳርድ ተዘጋጅቷል። በመሆኑም ወደ ስታንዳርዱ እንዲመጡ በማድረግና በኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪው በኩል የሚሰጠው የትብብር ስልጠና ጥራት እንዲኖረው የኢንዱስትሪውን ሰራተኛ የማብቃትና ብቃቱንም በምዘና የማረጋገጥ፤ የማሰልጠን ስነ-ዘዴ እንዲሰጥ በማድረግ የኢንዱስትሪ ውስጥ አሰልጣኝ እንዲሆኑና ኢንዱስትሪውን ለትብብር ስልጠና መስጫነት ምቹ እንዲሆን የሚያስችል ስታንዳርድ በማዘጋጀት ድጋፍ የማድረግ ስራ ይጠበቃል። ከዚህ አኳያ አፈጻጸማችን ሲታይ ካሉት የመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች አነስተኛነት እንዲሁም ከኘሮግራማቸው ውስንነት አኳያ ብዙዎቹ ኢንዱስትሪዎች በትብብር ሥልጠና የመሳተፍ ፍላጎት የላቸውም። ለዚህም ዋና ምክንያቱ የኢንዱስትሪዎች ማበረታቻና ማነሳሻ ፓኬጅ በማዘጋጀት አለመተግበሩ ነው። በታዳጊ ክልሎችና በገጠር አካባቢዎች ኢንዱስትሪዎች ባለመኖራቸው የትብብር ሥልጠና አለ ማለት አይቻልም። ይህ አይነቱ የሥልጠና ሥርዓት ኢንዱስትሪ በብዛት ባለባቸው አገሮች እንደ በኦስትሪያ እና ሲዊዘርላንድ ውጤታማ ነው። በመሆኑም ለአገራችን ተስማሚ የሚሆን የአሠልጣጠን ሥርአት መቀየስ ይጠይቃል። ኢንዱስትሪውም ሥራውን በእምነት ተቀብሎ ሥልጠናውን በጥራት መስጠት እንዲችል የራሱን የሠራተኛ ኃይል በማነሳሳት ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር በትብብር መሥራት የሚያስችል ግልጽ የአሠራር ሥርዓት መቅረጽ ያስፈልጋል።

2.2.5 ኪራይ ሰብሳቢነት ያልፀዳ፤ ኢንዱስትሪው በባለቤት ያልሆነበት የሙያ ብቃት ምዘና

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥልጠና ጥራቱን ለማረጋገጥ ከተዘረጋው ሥርአት አንዱ በመደበኛም ሆነ መደበኛ ባልሆኑ ዘርፎች የሠልጣኞችን ብቃት መመዘን ነው። በዚህ መሠረት በ2009 ዓ.ም. በየሥልጠና ዘርፎቹ ለመመዘን በፍቃደኝነት የመጡ፣ የተመዘኑ፣ ብቁ የሆኑትን በሚከተለው ግራፍ ማየት ይቻላል።[57]

ግራፍ 23፣ በ2009 ዓ.ም. ከመደበኛ ሥልጠና ውጪ በየሥልጠና ዘርፎቹ ለመመዘን ፍቃደኛ የሆኑና የተመዘኑ እንዲሁም ብቁ የሆኑ በ%



ከግራፉ እንደምንረዳው ከመደበኛ ሥልጠና ውጪ በተለያዩ ዘርፎች ሥልጠና ከወሰዱት ውስጥ ለመመዘን ፍቃደኛ የሆኑትና ብዛት ያላቸው ሠልጣኞች የተመዘኑት የኢንዱስትሪ ባለሙያዎች (73.5%) ሲሆኑ ብቁ ሆነው የተገኙት ግን 52.3% ናቸው። በአንፃሩ 65.4% አርሶ አደሮች ፍቃደኛ ሆነው የተመዘኑ ሲሆን ከሌሎቹ በተሻለ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ (93.7%) ብቁ ሆነው ተገኝተዋል። በጣም አነስተኛ የምዘና ፍላጐት የታየበት የገበያ ተኮር አጫጭር ሥልጠናዎች ነው። ሥልጠና ከወሰዱት ውስጥ 13.5% ብቻ ለመመዘን ፍቃደኛ የሆኑ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ብቁ የሆኑት 85.5% ናቸው። መደበኛ ሠልጣኞችን በተመለከተ በ2009 ዓ.ም. የሰለጠኑና ከዚህ ቀደም ምዘና ያልወሰዱት ጨምሮ የተመዘኑ ሲሆን ብቁ የሆኑት 68.7% ናቸው። ምንም እንኳን በሁሉም ዘርፎች ከተመዘኑት ውስጥ 75.48% ያህሉ ብቁ መሆናቸውን በግራፉ የተመላከተ ሲሆን የምዘና ሥርአቱ በብዙ ችግሮች የተወሳሰበ ነው። ከላይ በግራፉ እንደተመላከተው ብዙዎቹ ሠልጣኞች ለመመዘን ፍላጐት የላቸውም። ከቀጣሪ መሥሪያ ቤቶችም የተመዘነውና ያልተመዘነውን ለይተው አለመቅጠራቸው፤ ምዘናው በተለያዩ የኪራይ ሰብሳቢነት አሠራሮች ተጋላጭ መሆኑ፣ ኢንዱስትሪው ምዘናውን በባለቤትን የሚሸከምበት ደረጃ ላይ አለመድረሱ፤ ለምሳሌ መዛኝና የምዘና ማእከል ከኢንዱስትሪው መሆን ሲገባው ሰነ ምግባር የጐደላቸውና ለኢንዱስትሪው ወገንተኛ ያልሆኑ መዛኞችን በማሳተፍ

[57] ትምህርት ሚኒስቴር። (ነሐሴ/2009)። የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የ2010 በጀት ዓመት እቅድ።

ምዘናው በኪራይ ሰብሳቢነት ችግር ውስጥ መግባት፤ እንደዚሁም የምዘና ማዕከላት በተቋማት በመሆናቸው ስልጠናውን በሚመራው አካል ጣልቃ ገብነት መጋለጣቸው ምዘናውን በአግባቡ ተግባራዊ አለማድግ ችግሮች ሆነው ይስተዋላሉ። ከዚህ በተጨማሪም የልማት ፕሮግራሞቻችን አፈፃፀም የላቀ እንዲሆን ለማድረግ በኢንዱስትሪው የተሰማራውንና አዲስ የሚቀላቀለውን የሰው ኃይል ብቃት የማረጋገጥ ወሳኝ ተግባር በልማት ፈፃሚ መ/ቤቶች ባለቤትነት አለማግኘቱ፣ በዚህም ምክንያት ተግባሩ የዋነኛው የልማት ዕቅዳችን አካል አለመደረጉ፣ በተመሳሳይ መልኩ በየልማት ፕሮግራሞቹ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማትን የማረጋገጥ ተግባር በባለቤትነት አለመያዙ፣ በየልማት ፕሮግራሞቻችን የኢንዱስትሪ ሙያተኛን ብቃቱን በማረጋገጥ ሰፊ ቁጥር ያለው የኢንዱስትሪ መዛኝና አሰልጣኝ በማፍራት የልማት ፕሮግራሞቻችን የምዘናና የማሰልጠኛ ማዕከል ማድረግ አለመቻሉ የዘርፉ ተግዳሮቶች ናቸው።

ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ለሚደረገው ኢኮኖሚያዊ ሽግግር የግብርና ምርት በስፋት ማምረት ብሎም ለኢንዱስትሪ በቂ ግብዓት እንዲሆኑ ለማድረግ አምራቹን ገበሬ ማብቃት ወሳኝ ቦታ አለው። ከዚህም አንጻር የአርሶ/አርብቶ አደር ብቃት ምዘና ተደራሽነትና ጥራት ከማረጋገጥ አንጻር በሚፈለደው ደረጃ ለመፈጸም የቁርጠኝነት ችግር ይስተዋላል። በመሆኑም የብቃት ምዘና አገልግሎት ሽፋን የማሳደግ፣ የምዘና ሥርአታችንን ጥራት የማረጋገጥና በኢንዱስትሪውና ህብረተሰቡ ዘንድ የምዘና ስርዓቱን በሚመለከት ያሉ የአመለካከት ክፍተቶችን የማስተካከል ተግባራት በቀጣይ መከናወን ይኖርባቸዋል። ከዚህም ባሻገር የምዘና ተደራሽነትን ማሳደግ የሚችሉ አደረጃጀቶችን የማስተካከል ስራ፣ ቀልጣፋና ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት እንዲሁም ከኪራይ ሰብሳቢነት የጸዳ ስርዓት ለመፍጠር የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ረገድ ክልሎች ትኩረት ሰጥተው ሊያከናወኑት ይገባል። የሙያ ብቃት ምዘና ዜጉች በሀገር አቀፍ የብቃት ማዕቀፍ መሰረት ተመዝኖው ሀገራዊ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የሚሰጥበት ቢሆንም ከክልል ክልል ባለው የማሰፈጸምና የመፈጸም አቅም ልዩነትና ክፍተት በርካታ ችግሮች ይስተዋላሉ። ለዚህም ከአንድ ክልል ላይ ያለውን አቅም በሌላ ክልል ላይ ለመጠቀምና በክልሎች መካከል ወሀደትና የአቅም ክፍተት እንዳይኖር መሰራት ይጠይቃል። ከሌላ ሀገር ለዕውቀት ሽግግር ባለሙያ አምጥተን እንደምናሰራ ሁሉ ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል ባለሙያ ወስዶ ማሰራትና የእውቀት ሽግግር ማረጋገጥ የሚያስችል መሆን ይገባዋል። ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ የሚሰጥ ፖሊሲ ሊቀረጽ ይገባል።

2.2.6 የሥልጠና ጥራትን ማረጋገጥ ያልቻለ የአሠልጣኝ ምልመላና ዝግጅት

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የአሠልጣኝ ፍላጎት ለማሟላት የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩትና በኢንስትቲዩቱ ሥር በየክልል የተደራጁ አስራ አምስት ሳተላይት የፖሊቴክኒክ ኮሎጆች፣ ስድስት የዩኒቨርስቲዎችን (ሐዋሳ፣ዲላ፣ ወላይታ፣ አዲግራት፣ አርባ ምንጭ እና በህር ዳር) እና አንድ ኢንስትቲዩት (የሆቴልና ቱሪዝም) አቅም እንዲሁም ከዩኒቨርስቲዎች የተመረቁ አሰልጣኞችን በመጠቀም ሥልጠናውን እንዲሰጡ እየተደገ ይገኛል። እነዚህ አሰልጣኞች የኢንዱስትሪ ልምድ የላቸውም። አብዛኛዎቹም የሙያ ደረጃ እውቀት፣ ለሙያው የሚያስፈልገውን ክህሎት፣ የማሰልጠን ሥነ-ዘዴና አመለካከት ዝግጅታቸው በቂ አይደለም። ኢንዱስትሪዎችና

ተቋማቱ በዘርፉ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ ባለሙያ ያስፈልጓቸዋል፤ እነዚህን ከፍተኛ ባለሙያዎች ቢገኙ እንኳን ተቋማቱ የማቆየት አቅሙ የላቸውም።[58] በመሆኑም ሥልጠናው የሚሰጠው አቻ-ለአቻ በመሆኑ የአሠለጣጠን ዘዴ ነው።

2.2.7 በበቂ እውቀት ላይ ያልተመሠረት የቴክኖሎጂ ሽግግር

ከአሴት ሰንሰለት በመነሳት አዋጪ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ማሸጋገርና ኢንዱስትሪው በተለይም ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል አንዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ተልዕኮ ነው። ሆኖም ተግባሩን በአግባቡ ከመምራት አንጻር ሰፊ ክፍተት ያለው ሲሆን በዋነኛነት የአሰልጣኙን አቅም በሚፈለገው ደረጃ ከማምጣት አንጻር ያለው ክፍተት ከፍተኛ ነው። ለተግባሩ በቂ በጀት ከመመደብና ተግባሩን ከዩንቨርስቲዎች ጋር በመተሳሰር ከመምራት አንጻርም ችግር ይስተዋላል።

አሰልጣኞች በቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲበረታቱ የሚያደርግ አሰራር አለመኖሩና በተቋም ደረጃ የሚሰሩ ቴክኖሎጂዎች ወደ ውጤት እንዲቀየሩ የግል ባላሃብቱ ከትምህርትና ስልጠና ተቋማት ጋር በጋራ የሚሰራበት ሁኔታና አሰራርም የለም። እውቀትን ወደ ምርትና ሃብት ለመቀየር የግሉ ዘርፍ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጋር በቅርበት በመስራት እራሱም ተጠቃሚ መሆን ይችላል፤ የእውቀቱ ባለቤቶችም ተጠቃሚ ይሆናሉ፣ ለፈጠራና ለቴክኖሎጂ ሽግግርም ይነሳሳሉ። ቴክኖሎጂ መፍጠር እየቻሉ ነገር ግር በርካታ ገንዘብ ስለሚጠይቅ ሰርተው ወደ ገበያ ማቅረብ የሚችሉ ቴክኖሎጂ ወይም ፈጠራ ባለቤቶችን የሚያበረታታ ስርዓት ሊፈጠር ይገባል።

2.2.8 ቅንጅት የጐደለው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት

ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጠው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ በተቀመጠው አግባብ ኢንተርፕራይዞችና አንቀሳቃሾችን በአራቱ የድጋፍ ማእቀፎች (በክህሎት፣ ምርትና ምርታማነት/ካይዘን፣ ቴክኖሎጂና ኢንተርፕነርሺፕ) በተሟላ የመደገፍና ድጋፉም ክፍተት መሰረት ያደረገ ሆኖ የሚሰጠዉ ድጋፍ ማጠናቀቂያ የኦፕሬተሮችን ብቃት በሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጥና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት መሆን ሲገባው በተግባሩ የማስፈጸምና የመፈጸም አቅም ክፍተት ይስተዋላል።

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ውጤታማነት መለኪያው በተሰጠው ድጋፍ ከአንድ ደረጃ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ያደጉ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ሲሆን ለዚህ መረጋገጥ የተለያዩ ቀጥታ ተሳትፎ ያላቸው አካላት ድጋፍ ቅንጅት እጅግ በጣም የሚወስነው ተግባር ነው። ለምሳሌ የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የሚሰጥ ድጋፍ ሲሆን ኢኮኖሚና ፋይናንስ መሰረተ ልማቶች ለምሳሌ የመስሪያ ቦታ፣ብድር፣ የንግድ ፈቃድ፣ የመሳሰሉት በሌሎች አካላት የሚሰጥ ነው፤ እነዚህ አካላት በአንድ ላይ ተቀናጅተው ሚሰሩበት ሁኔታ ስለሌለ ብቻ ሳይሆን እርስ በእርስ ሲካሰሱ ጊዜ የሚያጠፉ በመሆናቸው፣ አንድ የሚያደርጋቸው አደረጃጀትና አሰራር ስለሌላቸው አጠቃላይ ስራው በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ ሊሆን አልቻለም። ኢንተርፕራዞች የማምረቻ ጥሬ ዕቃ የሚገዙት

[58] Ministry of Education. (2017.) Ethiopian Education Development Roadmap: An integrated Executive Summary (Draft).

ከአስመጪ ነጋዴዎች መሆኑ ሌላው በዚህ ዘርፍ ያለ ችግር ነው። ይኽውም ነጋዴዎች ከውጪ የሚያስገቡትን የኢንተርፕራይዞች ጥሬ ዕቃ ተመሳጥረው ዋጋ ከፍ በማድረግ በአንድ ጊዜ አመራች ኢንተርፕራይዞች እንዲሞቱ ያደርጓቸዋል። ለዚህ ዋናው ምክንያቱ አምራች ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተው እንዲሰሩ የሚያደርግ አሰራር ባለመኖሩ ነው።

2.2.9 ውጤት ላይ ትኩረት ያላደረገና ያልተቀናጀ የባለድርሻ አካላት ተሣትፎ

በየደረጃው ያለው አመራርና ባለድርሻ አካላት ሁኔታ ከላይ በአጠቃላይ ትምህርት የተቀመጡት ይህንም ዘርፍ የሚመለከቱ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም በዘርፉ አመራርና ባለድርሻ አካላት መደበኛውም ሆነ አጫጭር ሥልጠናዎች፣ በልማት ኮርደሮች ባለው የሥራ ገበያ ፍላጎት እና በሙያ ደረጃ በተቀመጠው የብቃት አሃድ ተመርኩዞ፣ በፕሮጄክት ላይ ተመሥርቶ በትብብር ሥልጠና የሥልጠናዉ ጥራትና ብቃት እየተረጋገጠ የሚከናወንበትና የሥልጠናዉም ማጠናቀቂያና ሊፈጠር በሚችለዉ የሥራ ዕድል ስምሪት በሙያ ብቃት ምዘና አማካኝነት በሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት መሆን ሲገባዉ በተገቢዉ ትኩረት አለመሰጠቱ የዉጤት ተኮር ቴሙትሥ ሥርዓት እንዲሸራረፍ ክፍተት ፍጥሯል። አመራሩም ሆነ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሴክተሩን በደንብ በመረዳት በእውቀት ላይ የተመሠረት አመራር በመስጠት በኩል የጐላ ክፍተት ይታያል። ሌላው የአመራሩ ችግር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በሁሉም ወረዳዎች ተደራሽ ለማድረግ ያለዉ ትኩረትና ተነሳሽነት አናሳ መሆን ነው። ዘርፉ ከፍተኛ በጀትን የሚጠይቅ ቢሆንም በአመራሩ ትኩረት ማነስ አሁን እየተመደበ ያለው ለትምህርት ሴክተር ከሚመደበው 10% ብቻ እንዲሆን አድርጓል። ይህ ደግሞ የሚፈለገውን ያህል ኘሮግራሙን ለማስፋፋት በቂ አይደለም፤ ተቋማቱም በአስፈላጊው ግብአቶች ሲሟሉ አይታይም። አመራሩም ስለሴክተሩ በሚፈለገው ደረጃ ግልጽነት ስለሌለው ይህንን ሊመራ የሚችል ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማዘጋጀት በኩል ትኩረት አልሰጠውም። በትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት 10ኛ ክፍልን ከአጠናቀቁት ውስጥ 80% በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እንዲሳተፉ ቢጠበቅም አመራሩ ትኩረት የሚሰጠው ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት እንዲገቡ ነው። በሌላ በኩል የውጤት ተኮር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና በተሟላ ሁኔታ ከመተግበር አንጻር በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ በስትራቴጂው መሰረት የሁሉም ባለድርሻ አካላት በተለይም የልማት ፕሮግራም መሪ መስሪያ ቤቶች ከዘርፉ ጋር ተሳስረው በባለቤትነት መፈጸም ላይ ክፍተት አለበት።

2.2.10 በተለያዩ ችግሮች የተወሳሰበ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አደረጃጀትና አመራር

አደረጃጀት፡ አስተዳደርና አመራር በተመለከተ በዘርፉ የታዩ ችግሮች የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ከሚመራው የሥራ ስፋት፡ ጥልቀትና ብዛት የሚመጥን እና ተገቢነት ያለው የፖለቲካ፡ የአስተዳደርና የአመራር ስልጣንና አቅም ያለው አለመሆን፤ የሥራ ፈጠራን፡ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ማስፋፋት ኃላፊነት የተሰጣቸው ኤጄንሲዎችን አቀናጅቶ የሚመራ የበላይ ተቋም አለመኖር፤ የክልሎች የቴክኒክና ሙያ አስተዳደርና አመራር አቅም ውስንነት ምክንያት ለክልሎቹ እና በውስጣቸው ላሉ ዞኖችና ወረዳዎች የኢኮኖሚ ልማት ለማፋጠን እቅድ ማቀድና

ማስፈጸም አለመቻል፤ የሚፈለገውን የሥልጠና ደረጃ የሚመጥን ሀገራዊ የሥርዓተ-ሥልጠና (curriculum) እና የሥልጠና መጽሐፍት አለመኖር ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊስተካከሉ ይገባቸዋል።

የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ትግበራ በተመለከተ የሚስተዋሉና ዘርፉ ውጤታማ እንዳይሆን ካደረጉት ችግሮች ውስጥ የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ከሚመራው የሥራ ስፋት፣ ጥልቀትና ብዛት የሚመጥን እና ተገቢነት ያለው የፖለቲካ፣ የአስተዳደርና የአመራር ስልጣንና አቅም ያለው አለመሆን፤ ወደ ዘርፉ በመካከለኛ ደረጃ ሙያ ለመሰልጠን የሚገቡ አብዛኛው ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ችሎታ ደካሞች ስለሆኑ የሥልጠናው ጥራት ጉዳት እያደረሰ መሆኑ፤ ጥራት ያላቸው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት እኩል ተደራሽነት አለመሆን፤ በሰልጣኞች ምዘና የእንዱስትሪ ተሳትፎ ደካማ መሆን፣ የሚሰጡ የሥልጠና ዓይነቶች ሀገራዊ፣ ክልላዊና ቀጠናዊ ኢኮኖሚ ከሚፈልገው የሰለጠነ የሰው ኃይል ጋር የማይናበብ መሆን፤ ተቋማት መሀከል ያለው በመምህራኖቻቸው የሚዘጋጁ ሥርዓተ-ሥልጠና እና የሥልጠና መጻሕፍት /ማቴሪያሎች/ መለያየት፤ ከክልል ክልል የሰልጣኝ ምሩቃን የሚመዘኑበት የብቃት ምዘና ሁኔታ በጣም የተለያየ መሆን በተመሳሳይ የሙያ ደረጃ ብቁ የተባሉትን መወዳደር አለመቻል፤ ብቁና ተነሳሽነት ያላቸው የቴክኒክና ሙያ መምህራንና አሰልጣኞች እጥረት፤ በተማሪዎች፣ በወላጆችና እና በቀጣሪዎች ያለው ዝቅተኛ አመለካከት የተሸሉ ተማሪዎች እንዲርቁ ማድረጉ፤ በዋናነት የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው።

የዘርፉ አመራር ወቅታዊና ጥራቱ የተጠበቀ መረጃ ስርዓቱን ለመምራት ወሳኝ መሆኑን አምኖ የመረጃ ቋት ለመዘርጋት ያለው ተነሳሽነት አናሳ መሆን ሌላው ችግር ነው። የየዕድገት ቀጠናዎቹ የልማት ፕሮግራሞች የሚፈልጉትን ሙያተኞች በተቀመጠው ስብጥር መሰረት ተቀብሎ ጥራቱ በተጠበቀ ትብብር ስልጠና አብቅቶ ማቅረብ የስርአቱ አመራር ዋነኛ ተልዕኮ መሆኑን በእምነት ይዞ የመፈጸም ቁርጠኝነት ማነስ፣ መደበኛና ገበያ ተኮር አጫጭር ስልጠናዎችን በጥራት ለማከናወን የትብብር ስልጠና ወሳኝ ስልት መሆኑን በእምነት ይዞ አለመንቀሳቀስ፣ ሥራ ፈላጊ ዜጎችን ከስራ ጋር ለማገናኘት ብቃታቸውን ፈትሾ ያለባቸውን ክፍተት በገበያ ተኮር አጫጭር ስልጠና የማሟላት ተግባርን ጠቀሜታ በውል ተገንዝቦ የመፈጸም ተነሳሽነት ደካማ መሆን፣ የማሰልጠኛ/ማምረቻ ማሽኖች ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን መተካት በሚያስችል የቴክኖሎጂ ደረጃ ላይ መሆናቸውን ተገንዝቦ ሙሉ አቅማቸውን ለመጠቀም ያለው ተነሳሽነት አናሳ መሆን፣ ለትብብር ስልጠና መስፋፋትና ጥራት መረጋገጥ ቀዳሚው ተግባር የተቋም ውስጥ ስልጠናን ፕሮጀክት ተኮር ማድረግና የኢንዱስትሪ አሰልጣኝ ማፍራት መሆኑን አምኖ አለመተግበር የአመራሩ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው።

በአጠቃላይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ በሚፈለገው ደረጃ በማሳደግ ኢኮኖሚውን እንዳይደግፍ አንቀው የያዙት ከፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ አደረጃጀትና አሠራር፣ አተገባበር እንዲሁም ከፋይናንስ ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶችና ችግሮች አሉ። ከፖሊሲ ጋር የተያያዙ ችግሮች አሁን ያለው ፖሊስ ገዳቢ ከመሆኑ የተነሳ በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ውስጥ ጥራት ያለው መካከለኛና ከፍተኛ ባለሙያ ለማሰልጠን አለመቻል፤ የዘርፉ ምሩቃን ወደ ከፍተኛ የሥልጠና ፕሮግራም እና ትምህርት የሚያሳደግና የሚያሸጋግር (Progression and Permeation) የሚያስችል

ሥርዓትና የፖሊሲ ድጋፍ አለመኖር፣ ከእንግሊዝኛ በስተቀር ሌላ ሰልጣኞች በሚችሉት ቋንቋ መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና መስጠትን የሚያስችል (Flexible Training Language) ፖሊሲ አለመኖር ናቸው።

ከስትራቴጂ አንጻር ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተደራሽነት ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የሥልጠና ተቋማትን አለማደራጀት፤ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ መሰረት ለሆነው ለእርሻና ግብርና ትኩረት አለመስጠት፣ የተለያዩ ኢንዱስትሪና ኢኮኖሚ ዘርፎች ተቀናጅተው ለዘርፋቸው ተገቢ ብቃትና ክህሎት ያላቸውን የመካከለኛ ደረጃ ባለሙያ የሚያሰለጥኑበት ፖሊሲና ስትራቴጂ አለመኖር፤ ሀገራዊ ፍላጎትን በትክክል ያላገናዘበ የሥራ ዘርፍ ስታንዳርድ (Occupational Standards - OS) ማዘጋጀት፤ የትብብር ሥልጠናን (Cooperative Training – Dual Training) ለመተግበር በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ስትራቴጂ የታቀደው እቅድ ከሀገራችን ነበራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም አለመሆን፤ የተደራጀ መረጃ አለመኖር፣ የግል ተቋማት ገንዘብ በመሰብሰብ ላይ ያተኮሩ መሆን በዘርፉ የተስተዋሉ ችግሮች ናቸው።

2.2.11 በቂ ትኩረት ያልተሰጠው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የፋይናንስ ስርዓት

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፋይናንስ በተመለከተ ውጤታማ የቴክኒክና ሙያ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል ጠንካራና ደጋፊ የፋይናንስ ስርዓት አለመኖር፤ ኢንዱስትሪና የንግድ ድርጅቶች ለቴክኒክና ሙያ ሥልጠናና የራሳቸውን የገንዘብ ድጋፍ/አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ ፖሊሲ አለመኖር፤ በመንግሥት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የሁለት እዮሽ የመንግስታት ትብብርን የቴክኒክና ሙያ ዘርፉን ለማዘመንና ማሳደግ የተሰራው ሥራ ደካማነት ወይም ትኩረት ማጣት፤ ለመንግሥት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚመደበው በጀት ውጤታማነት ማዕከል ያደረገ የሰልጣኞች ቁጥር እና በሥልጠና ዓይነት ብዛት የሚወሰን መሆን፤ የመንግሥት የቴክኒክና የሙያ ተቋማት አምራች እንዲሆኑና ገቢ ማመንጨት የሚያስችል ፖሊሲና ስትራቴጂ አለመኖር ዘርፉ እንዳያድግ ቀይደው የያዙት ችግሮች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም የአገሪቱን መካከለኛና ዝቅተኛ የሠለጠነ የሰው ኃይል በብዛት፣ በጥራትና በብቃት ማፍራት የሚያስችል ጥራት ያለው ሥልጠና መስጠት የሚያስችል በቂ ሀብት ባለመመደቡ ሥልጠናው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አድርሷል።


3 ከፍተኛ ትምህርት

3.1 ለሴቶችና ልዩ ፍላጉት ላላቸው ወገኖች ትኩረት ያልሰጠ የከፍተኛ ትምህርት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት

የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ አላማ የደረጃውን የትምህርት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት በማሳደግ፣ ጥራቱንና አግባብነቱን በማረጋገጥ፣ ምርምርንና የቴክኖሎጂ የመቅዳት አቅም በማሳደግ፣ የተቋማቱን አመራርን፣ አደረጃጀትና አሠራር በማሻሻል አገራችን ፈጣን ልማቷን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለማስቀጠል የሚያስችላትንና ኢኮኖሚው የሚፈልገውን ብቃት ያለው የሰው ኃይል በሚፈለገው መጠን ማቅረብ ነው። በመሆኑም ኢኮኖሚው በከፍተኛ ደረጃ የሚፈልገው ብቁና በቂ የሰው ኃይል መሠረት በፍትሐዊነት ማዳረስ የግድ ይላል። ከዚህ አኳያ ባለፉት አመታት ሰፊ የከፍተኛ


ትምህርት የማስፋፋት ሥራ የተሠራ ሲሆን ከ2005 ዓ.ም. ጀምሮ የነበረው የተሣትፎ መጠን ከሚከተለው ግራፍ መረዳት ይቻላል።

ግራፍ 24፣ ከ2005 እስከ 2009 ዓ.ም. የቅድመ ምረቃ ተሣታፊዎች በአሃዝ



ከላይ ከቀረበው ግራፍ መረዳት እንደሚቻለው የከፍተኛ ትምህርት ተሣትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቶ በ2009 ዓ.ም. በበሁሉም ፕሮግራሞች በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት 788,033 (281,429 ሴቶች) የቅድመ ምረቃ ትምህርት እየተከታተሉ እንደነበር ሲያመለክት የሴቶች ድርሻ 35.7% ደርሷል። እነዚህ ተማሪዎች በ47 የመንግሥት፣ በ130 የግል በድምሩ በ177 ተቋማት ትምህርታቸው እየተከታተሉ ይገኛሉ።[59] ምንም እንኳ ከቁጥር አኳያ ሰናይ የተሣትፎው መጠንና የተቋማት ብዛት እያደገ የመጣ ቢመስልም የአገራች ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ ከሚፈልገው ብቁና በቂ የሰው ኃይል አንፃር አፈጻጸማችን በጣም ዝቅተኛ ነው። ይህን አፈጻጸማችንን ከሚከተለው ግራፍ መረዳት ይቻላል።

ግራፍ 25፣ የከፍተኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎአችን ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነፃፀር በ%




[59] Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016/17), p. 139.

ከላይ የቀረበው ግራፍ የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎአችን በ2010 ዓ.ም. 12.3% እንደሆነ ያሳያል።[60] በ2017/18 በGMR[61] ሪፖርት መሠረት እ.ኤ.አ በ2015 እድሚያቸው ለከፍተኛ ትምህርት የደረሱ 213 ሚሊዮን ወጣቶች የከፍተኛ ትምህርት የተሳተፉና የአለም አማካይ 36%፣ ከሰሃራ በታች ያሉ አገሮች 8%፣ ደቡብ ኢሲያ አገሮች 25%፣ ዝቀተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች 23%፣ ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች 46% እንዲሁም የበለፀጉ አገሮች 74% መሆኑን ያስረዳል። በዚህ መረጃ መሠረት የከፍተኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፏችን ከሰሃራ በታች ካሉ አገሮች አማካይ የተሻልን ብንመስልም ከሌሎቹ በግራፉ ከቀረቡት አገሮች አማካይ ጥቅል ተሣትፎ ጋር ስናነጻጽረው ተሳትፏችን በጣም ዝቀተኛ ነው። ለተሣትፎው ዝቀተኛ መሆን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ዝቀተኛ መሆን፣ የዩኒቨርስቲዎች የመቀበል አቅም ውሰን መሆን፣ የግንባታዎች በመርሃ ግብሩ መሠረት አለመጠናቀቅ፣ ግብአቶች አለመሟላት፣ ወዘተ. በዋናነት የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው። በመሆኑም በ2012 ዓ.ም በሁለተኛው የእድገትና ትራንሰፎርሜሽን እቅድ መጨረሻ እንደርሰበታለን ካልነው የ15% ጥቅል ተሳትፎ ግብ እንዲሁም የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ አገር ለመገንባት ካሰቀመጥነው ግብ አኳያ ብዙ መሥራት ይገባናል። ቢያንስ፣ ቢያንስ በየአመቱ ከ1.5% በላይ የጥቅል ተሣትፎ ጭማሪ ማስመዝገብ ይኖርብናል። በሌላ በኩል ግልጽ የሆነ የከፍተኛ ትምህርት መስፋፋት የሚያስችል የተደራሽነትም ሆነ የፍታሃዊነት አመላካች አለመኖር በትምህርት ጥራቱ ላይም አሉታዊ እያሳደረ በመሆኑ ጥናት ላይ የተመሠረተ የማስፋፋት ሥራ መሥራት ይገባል።

ከፍትሐዊነት አንፃር ሴቶች፣ አካል ጉዳት ያለባቸው ዜጐች፣ የአርብቶ አደርና የታዳጊ ክልል ተወላጅ ተማሪዎች በታሪክ አጋጣሚ በቂ የከፍተኛ ተሳትፎ ያልነበራቸው በመሆኑ አወንታዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ተሣትፎአቸውን ለማሳደግ በተደረገው ጥረት በቅድመ ምረቃ የሴቶች ተሣትፎ 34.53% ደርሷል። ከሥርዓተ-ጾታ ምጥጥን አኳያ አፈጻጸማችን 0.56 ነው።[62] ይህ አፈጻጸማችን ከአለም አቀፍ አኳያ ምን ደረጃ ላይ እንዳለን ከሚከተለው ግራፍ መረዳት ይቻላል።

ግራፍ 26፣ የ2009 ዓ.ም. የከፍተኛ ትምህርት የሥርዓተ-ጾታ ምጥጥን



[60] ትምህርት ሚኒስቴር። (ግንቦት/2010)። የትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የ2010 ዓ.ም. የ9 ወር የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት።
[61] UNESCO.(2017). GLOBAL EDUCATION MONITORING REPORT 2017/2018. https://en.unesco.org/gem-report/
[62] ትምህርት ሚኒስቴር። (ግንቦት/2010)። የትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የ2010 ዓ.ም. የ9 ወር የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት።

ከላይ የቀረበው ግራፍ የከፍተኛ ትምህርት የሥርዓተ-ጾታ ምጥጥኑ የGMR[63] ሪፖርት መሠረት ያደረገ ሲሆን የአለም አቀፍ አማካይ 1.12፣ ከሰሃራ በታች ባሉ አገሮች 0.70፣ ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ 0.99፣ ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ 1.18 እንዲሁም በበለፀጉ አገሮች 1.24 ካለው ተሣትፎ አንፃር የእኛን 0.56 አፈጻጸም ስናነፃጽር በጣም ያዘገመ እድገት እንደሆነ ያመላክተናል። ከመረጃው እንደምንረዳው የኢኮኖሚ እድገት በጨመረ ቁጥር የሴቶች ተሣትፎ እየጨመረ እንደሚሄድ ያሳያል። በመሆኑም በቀጣይ ትኩረት ሰጥተን መሥራት ያለብን ወሳኝ ጉዳይ ነው። በሌላ በኩል የአካል ጉዳተኞችና የታዳጊ ክልልና የአርብቶ አደር ተወላጅ ተማሪዎች ተሣተፎ ስንመለከት በልዩ የመቁረጫ ነጥብ ድጋፍ በማድረግ ተሣትፏቸውን ለማሳደግ ጥረት ቢደረግም የተሣትፎ መጠናቸውን ለማየት እንኳን ግልጽ መረጃ የሌለ ከመሆኑም ባሻገር ከፍተኛ ችግር ያለበት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

የድህረ-ምረቃ ኘሮግራም በተመለከተ ኘሮግራሙ በዋናነት የከፍተኛ ትምህርት የአሠልጣኝ መምህራንን አቅም ማጐልበት ሲሆን ከዚህ መርህ በመነሳት የዩኒቨርስቲ መምህራንን ምጥጥን በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎሚሽን እቅድ መጨረሻ 0:70:30 (የመጀመሪያ ዲግሪ : ሁለተኛ ዲግሪ : ሦስተኛ ዲግሪ) ለማድረስ ታቅዷል። ከዚህ አኳያ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሁለተኛና የሦስተኛ ዲግሪ የመምህራን ሥልጠና እየተሰጠ ቢሆንም በ2010 ዓ.ም. መድረስ የቻልነው 21:64:15 የመምህራንን ምጥጥን ነው። ይህ ደግሞ የሚያመላክተን የዩኒቨርስቲ መምህራን ምጥጥን ስታንዳርድ ማሟላት አለመቻላችንን ብቻ ሳይሆን በአገር ውስጥ አቅም በመገንባት የትምህርት ጥራትና አግባብነት የማሳደግ ሥራችን ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ከማሳደሩም ባሻገር ወደ ውጭ አገር ልከን የምናሰለጥነውን የሰው ኃይል በማሰቀረት የውጪ ምንዛሬን ማዳን አልቻልንም። የውጭ ሥልጠናውን በአገር ውስጥ ሥልጠና በማስጠጥባቸው የትምህርት መስኮች መሆን ይገባዋል። በሌላ በኩልም የሴት አሠልጣኝ መምህራንም 15% ብቻ መሆኑ ከፍተኛ ሥራ የሚጠይቀን መሆኑን ያመለክታል።

3.2 የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት


3.2.1 ጥራትና አግባብነት ያላረጋገጠ የመምህራን ብቃት

የትምህርትን ጥራት ለማረጋገጥ የመምህራን ብቃት ወሳኝ ነው። ከዩኒቨርስቲዎች መስፋፋት ጐን ለጐን መምህራን ምልመላ፣ የአቅም ግንባታ ኘሮግራም በሰፊ ሲካሄድ ቆይቷል። በዚህም መሠረት የመምህራን ቁጥር በፍጥነት እያደገ መጥቷል። ለአብነት ያህል በ2005 ዓ.ም. 23,905 የነበረው በ2009 ዓ.ም. ወደ 32,734 አድጓል። ከብቃት አንጻር ሲታይ ግን በብዙ ችግሮች አሉበት።[64] ከከፍተኛ ትምህርት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ለደረጃው ብቁ የሰው ኃይል በብዛት ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ ከዩኒቨርስቲ በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁ መምህራን ተመልምለው ወደ ሥራ እንዲሰማሩ መደረጉ በመማር ማስተማሩ ላይ አሉታዊ ጫና አሳድሯል። ለዩኒቨርስቲ መምህርነት የሚመለመሉት በከፍተኛ ማእረግ ከተመረቁት ማለትም 3.25 እና በላይ ውጤት ካመጡት ውስጥ ሲሆን ፈተና በመስጠት እንዲለዩ

[63] UNESCO.(2017). GLOBAL EDUCATION MONITORING REPORT 2017/2018. https://en.unesco.org/gem-report/
[64] Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016/17), p. 151.

ይደረጋል። የፈተናው ውጤትም የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓታችን ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይጠቁማል። የፈተና ውጤቱን በሚከተለው ግራፍ ማየት ይቻላል።

ግራፍ 27፣ በ2009 ዓ.ም. ለዩኒቨርስቲ መምህርነት ተፈትነው 50% እና በላይ ውጤት ያመጡ የዩኒቨርስቲ የቅድመ ምረቃ ምሩቃን



	እንግሊዝኛ	ሒሳብ	ፊዚክስ	ኬሚስትሪ	ባዮሎጂ	ኢኮኖሚክስ	ጂኦግራፊ	ታሪክ	ማኔጅመንት	አካውንቲንግ	የተፈ.ሀብት አስ./NRM/	ግብርና ኢኮኖሚክስ	አጽዋት ሳይንስ	የእንስሳት ሳይንስ	አጠቃላይ
ድምር	3.48	1.30	4.61	9.20	64.68	2.65	20.78	3.77	56.98	8.37	63.98	59.85	45.66	26.58	27.79
ሴት	2.86	0.00	1.45	2.64	45.19	0.99	9.74	1.06	35.94	1.66	36.50	40.00	21.29	11.70	17.67
ወንድ	3.90	2.17	6.49	13.45	80.39	2.84	25.90	5.26	62.68	9.53	74.12	65.42	55.44	30.41	31.54

ከግራፉ መረዳት እንደሚቻለው ለፈተና ከተቀመጡት 8392 እጩዎች ውስጥ በተመረቁበት የትምህርት አይነት መሠረታዊ ሣይንሱን ተፈትነው 50% እና በላይ ውጤት ያመጡት በጣም አነስተኛ (27.79%) ናቸው። በተለይ ሒሳብ (1.30%)፣ ኢኮኖሚክስ (2.65%)፣ እንግሊዝኛ (3.48%)፣ ታሪክ (3.77%)፣ ፊዚክስ (4.61%)፣ አካውንቲንግ (8.37%)፣ ኬሚስትሪ (9.20%) እጅግ አነስተኛ አፈጻጸም ያለባቸው የትምህርት አይነቶች ናቸው። ጂኦግራፊ (20.78%)፣ የእንስሳት ሣይንስ (26.58%)፣ እጽዋት ሣይንስ (45.66%) አነስተኛ አፈጻጸም ታይቶባቸዋል። ሌሎቹ ባዮሎጂ (64.68%)፣ የተፈጥሮ ሀብት አስተዳደር (63.98%)፣ ግብርና ኢኮኖሚክስ (59.85%)፣ ማኔጅመንት (56.98%) የተሻለ አፈጻጸም ታይቶባቸዋል። ይህ ውጤት የሚያሳያን የከፍተኛ ትምህርት ጥራት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን ነው።

3.2.2 የሕብረተሰቡን ችግር ያልቀረፈ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎት

ከመማር ማስተማር በተጨማሪ ከመምህራን ብቃት ጋር ተያይዞ የዘርፉን የትምህርት ጥራትንና አግባብነትን የምናረጋግጥባቸው ዘዴዎች የጥናትና ምርምር እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎቶች ናቸው። ጥናትና ምርምርን በተመለከተ መንግሥት ለጥናትና ምርምር የሚመድበው በጀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ እንዲሁም በዩኒቨርስቲዎች ጥናትና ምርምር መሥራት የሚችሉ በርካታ ነባርና አዳዲስ መምህራን ያሉ ቢሆንም በተግባር የሚታየው የጥናትና ምርምር ሥራ ግን በጣም ውስን ነው።[65] በ2010 ዓ.ም. በተሰበሰበው መረጃ መሠረት በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች በጥናትና ምርምር እየተሳተፉ ያሉት መምህራን ብዛት ወንድ 4684፤ ሴት 604 በድምሩ 5288

[65] Ministry of Education. (2017.) Ethiopian Education Development Roadmap: An integrated Executive Summary (Draft).

(16.15%) ብቻ ናቸው።[66] ከዚህ የምንረዳው በጣም ውስን መምህራን ብቻ በጥናትና ምርምር እንደሚሳተፉ መሆኑን ነው። የሚጠኑ ጥናቶችም ከሕብረተሰቡ ችግር ጋር አለመተሳሰር፣ ከመማር ማስተማሩ ጋር አለመዛመድ፣ አዳዲስ መምህራን የጥናትና ምርምር ክህሎት አለመኖር፣ የጥናትና ምርምር ግብአቶች አለመኖር፣ የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው። የጥናትና ምርምር እርሶች አጥኚው ወይም የገንዘብ ድጋፍ በሚያደርገው አካል ምርጫ እንጂ ትክክለኛ የሕብረተሰቡን ችግር ለይቶ የሚመረጥ አይደለም።[67] የሚጠኑ የጥናትና ምርምር ሥራዎችም ጥናቱ በሚጠናበት አካባቢ ቋንቋ አለመሆን፣ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ተደጋጋሚ መሆን፣ አንዱ ከሌላው መቀዳዳት መኖር፣ በጥናትና ምርምር የተፈቱ ችግሮችን ቆጥሮ አለመያዝ፣ ወዘተ. ችግሮች እስከሁን ያልተፈቱ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም ዩኒቨርስቲዎች ብሎ መምህራን በአገሪቱ የሚታዩ ችግሮችን እየለዩ በጥናትና ምርምር የተደገፈ ምክረ-ሃሳቦችን በመቅረብ ማህብራዊ፣ ኢክኖሚውንና ፖለቲካዊ መስተጋብሩን የማሻሻል ኃላፊነታቸው መወጣት ሲጠበቅበቸው አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ጥናቶች እንደሚያሳዩት በኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲዎች የጥናትና ምርምር አቅም ውስን ከመሆኑም ባሻገር የሚጠኑት ጥናቶችም በነባር ዩኒቨርስቲዎች ሆኖ ትኩረታቸው በግብርና እና በጤና ላይ ያተኮሩ ናቸው። በኢንጂነሪንግ ዘርፍ የተደረጉ ጥናቶች ብዛት በጠቅላላው ከተጠናው ጥናት ከ2% አይበልጥም።[68] በተመሳሳይ መልኩ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሥራዎችም አዝጋሚዎች ናቸው። ከ2008 እስከ 2010 ዓ.ም. ድረስ የተሻገገሩት ቴክኖሎጂዎች 394 ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ ውጤታማ የሆኑት 289 ብቻ ናቸው። ይህ አፈጻጸም ከሚፈለገው ቴክኖሎጂ ብዛትና ከውጤታማነት አኳያ በሚፈለገው ደረጃ አለመድረሳችንን ያሳያል።[69] ከሁሉም የዩኒቨርስቲ ተልእኮዎች ትኩረት ያልተሰጠው የማህበረሰብ አገልግሎት ነው። በአብዛኛዎቹ ዩኒቨርስቲዎች የማህበረሰብ አገልግሎት እንደተጨማሪና የመያድ ሥራ አድርጉ የሚታይ ነው።[70] ከምርምርና ቴክኖሎጂ የተገኘ ውጤትን ሕብረተሰቡን ለመቀየር አለመጣርም ጉልህ ችግር ነው።

3.2.3 ብቁ ምሩቃን ማፍራት የተሳነው የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት

በዩኒቨርስቲዎች መካከል የነበረውን የሥርዓተ-ትምህርት አሰጣጥ ልዩነት ለማቀራረብ በቅድመ ምረቃ ኘሮግራም የሞጁላራይዜሽንና የማስማማት ሥራ ተሠርቷል። የቅድመ-ምረቃ ሞጁላራይዝ ሥራ ተግባራዊ በመደረጉ ዝግጁቱን መሠረት ያደረገ የመማር ማስተማር ሂደትን፣ ተከታታይ ምዘናን፣ ተማሪዎች እርስ በርስ የሚማማሩበትን ሁኔታ በመፍጠር በኩል የተወሰነ አወንታዊ ለውጦች ነበሩት።[71] ይህ የአሠራር ሂደት በአመዛኙ በተማሪዎች መካከል ኩረጃን በማባባስ፣ የተማሪዎችን ግምገማ በመፍራት ያልተገባ ውጤት ለተማሪ በመስጠት የውጤት መጋሸብ መፍጠሩ፣ ወዘተ. በትምህርት ጥራቱ ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጥሯል። ዝግጅቱም ቢሆን ብቃትን መሠረት ያላደረገ፣ አቀራረቡም ከተለምዶዊ ዝግጅት ያልወጣ፣ የሥራውን አለም ያላገናዘበ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም የከፍተኛ ትምህርት የሥርዓተ-ትምህርት ዋናው ችግር ከሕይወት ክህሎት ጋር ያልተዛመደና ለሥራ የሚያዘጋጅ አይደለም።

[66] ትምህርት ሚኒስቴር። (ግንቦት/2010)። የትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የ2010 ዓ.ም. የ9 ወር የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት።
[67] Ministry of Education. (2017.) Ethiopian Education Development Roadmap: An integrated Executive Summary (Draft).
[68] Salmi, J., Sursock, A. and Olefir, A. (2017). Improving the Performance of Ethiopian Universities in Science and Technology: A policy note, p. 11.
[69] ትምህርት ሚኒስቴር። (ግንቦት/2010)። የትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የ2010 ዓ.ም. የ9 ወር የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት።
[70] Ministry of Education. (2017.) Ethiopian Education Development Roadmap: An integrated Executive Summary (Draft).
[71] Ibid

ከኢኮኖሚ ኮሊዶር ጋርም አልተሳሰረም። ኘሮግራም አከፋፈትን በተመለከተ በገበያ መረጃ ላይ ያልተመሠረተ በአብዛኛው በመምህራን ፍላጐት እንጂ ከአገር የሰው ሀይል፣ ቴክኖሎጂ ፍላጐትን በጥናት ላይ ተመሥርቶ አይከፈትም። ሁሉም ዩኒቨርስቲዎች የሚሰጡት ሥልጠና አንድ አይነት ነው። በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አስተሳስሮ የልሕቀት ማእከል ሆነው ሥልጠና የሚሰጡ ዩኒቨርስቲዎች የሉም። ዩኒቨርስቲዎች ከኢንዱስትሪው ጋር የጠበቀ ትስስር ባለመኖሩ ምክንያት ተማሪዎች ስለሚጠብቃቸው የሥራ አለም ጋር የመተዋወቁ ሁኔታ ውሰን አድርጐታል። ሌላው ሥርዓተ-ትምህርቱን ለተማሪዎች በተገቢው መንገድ ለመስጠት ችግር የሆነው የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርትን አጠናቀው የሚመጡ ወጣቶች በቂ ይዘት ጨብጠው አለመምጣትና በእንግሊዝኛ ቋንቋም ማንበብና መፃፍ አለመቻል አሳሳቢና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው።[72]

3.2.4 ለብክነት የተጋለጠ የዩኒቨርስቲዎች ሀብት /ውስጣዊ ብቃት/

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በሁለት አሥርት አመታት ጊዜ ውስጥ የዩኒቨርስቲዎች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። ይህ የከፍተኛ ትምህርት የማስፋፋት ሥራችን በከፍተኛ ፍጥነት ማደጉን ተከትሎ ውስጣዊ ብቃቱ ላይ ተግዳሮት ሆኗል። ከእነዚህ ውስጥ የሚጠቀሱት በመጀመሪያ የሚጠቀሰው ተቋማቱ የሚከፈቱት ሙሉ በሙሉ የዩኒቨርስቲ ይዘትን አሟልተው አይደለም። በዚህ ምክንያትም የተሟላ ወርክሾፕ፣ ኢንተርኔት፣ የመረጃ ሥርአት፣ ብቁ መምህራን፣ ወዘተ. ችግሮች ውስጥ ሆነው ሥራ ይጀምራሉ። በመሆኑም በዩኒቨርስቲው ተልእኮ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሲያሳድሩ ይታያሉ። በሌላ በኩል መንግሥት ለዩኒቨርስቲዎች ከፍተኛ በጀት እየመደበ ያለ ሲሆን ትግበራው ላይ ከፍተኛ ብክነት የሚታይበት ነው። በተደጋጋሚ የኦዲት ግኝነት አስተያየት እየተሰጠ መቀነስ ሲገባው መሻሻል አይታይበትም። የሚመደበው በጀትም በአብዛኛው ለአስተዳደር እንጂ በዋናው ተልእኮ ለሆኑት የመማር ማስተማር፣ የምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት አይደለም። የከፍተኛ ትምህርት የፋይናንስ ሥርአቱም ቢሆን የቤተሰብ የፋይናንስ አቅምን ያላገናዘበ፣ ስኮላርሺፕ የማይሰጥበት፣ ሁሉንም በአንድ ጃኬት ውስጥ አስገብቶ በ15% የወጪ መጋራት ሥርአት የሚያይ ነው። ከአመራር አኳያ ዩዩኒቨርስቲ አመራርም ዋናው ስትራቴጂክ የሆነውን የመማር ማስተማር፣ የምርምር እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎት ላይ አተኩሮ መሥራት ያለበት ቢሆንም እነዚህ ተዘውታሪ ሥራዎችን ማለትም የግንባታ ሥራዎች፣ የቅጥር፣ የግዢ፣ ወዘተ. ሥራዎችን እየሰራም ቢሆን ችግሮቹ ሊቀረፉ አልቻሉም። በመማር ውጤት መውደቅ ተጠያቂ ሲሆን አይታይም። ቦርድም ቢሆን መደበኛ ስብሰባ ከማድረግ ውጪ እነዚህን ችግሮች ለይቶ የማስተካከያ እርምጃ አይወስድም።

3.2.5 የትምህርት ጥራትን ያላረጋገጠ፤ ገንዘብ መሰብሰብ ላይ ያተኮረ የግል ተቋማት ሚና

በመሠረታዊነት የግል ከፍተኛ ትምህርት በትምህርት ተደራሽነትና ጥራት ላይ ለየራሳቸው ሚና አላቸው። ባለፉት አመታት ከመንግሥት ተቋማት ይልቅ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሦስት እጥፍ እየተስፋፉ መጥተዋል። ምንም እንኳን በከፍተኛ ቁጥር እየተስፋፉ ቢመጡም አፈጻጸማቸው ሲታይ ስታንደርዳቸውን ያልጠበቁ ተቋማት ቁጥር ቀላል አይደለም። ከዚህ በተጨማሪም አብዛኛዎቹ ከጥራት ይልቅ ገንዘብ መሰብሰብ ላይ ያተኮሩ ናቸው።

[72]Ministry of Education. (2017.) Ethiopian Education Development Roadmap: An integrated Executive Summary (Draft).

3.2.6 ያልተቀናጀ የባለድርሻ አካላት ሚና

3.2.6.1 ተማሪዎች

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያልፉ ዜጎች የየአገራቸውን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚወስኑ ዋነኞቹ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው። በመሆኑም የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ዓለም በሣይንስና ቴክኖሎጂ የደረሰችበትን ደረጃና ትምህርት ያስገኘውን ጥቅም በመረዳት፣ አካባቢን በማወቅ፣ በመገንዘብና የመለወጥ አቅም በመሆን የአገራችንን ሁለንተናዊ እድገት ላይ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ኃላፊነት አለባቸው። ከዚህ አኳያ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያሉ ተማሪዎቻችን የማይመቹ ተቋማዊ ሁኔታዎችና አየር ፀባይን ቻምር በመታገስ ብቃታቸውን ለማሳደግ፣ በአገራችን አጠቃላይ ልማት ለመሳተፍና ያሉ የመልካም አስተዳዳር ችግሮችን ለመፍታት ቻምር ሲተጉ ይታያሉ። አብዛኛው ተማሪ በዩኒቨርሲቲ ቆይታው በሚያገኘው አጋጣሚና እድል ሁሉ ብቁ ሆኖ ለመውጣት ይተጋል። በማህበረሰብ ሥራዎች በመሳተፍና በክበባት ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የአመራር ጥበብንና ማህበራዊ ኑሮን ለመልመድ የሚተጉም በርካቶች ናቸው። ከሁሉ በላይ ተማሪዎቻችን ከእለት ምግባቸው ቻምር በመቀነስ በአገራዊ ጥሪዎችና ልማቶች በመሳተፍ የህዝብ ወገንተኝነታቸውን ያሳያሉ። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ቁጥራቸው ውስን ቢሆንም በግለሰብና ማህበረሰብ ኃብት አጠቃቀም ረገድ ደንታ ቢስ የሆኑ፣ የስራ ጠባቂነት መንፈስ የተጠናወታቸው፣ በሌሎች የሚነዱና የራሳቸው አቋም የሌላቸው፣ በዓለምና በአገራችን ያሉትን ለውጦች ለማወቅ የማይጓጉ፣ በጎጂና መጠ ባህል የተጠመዱ፣ የ1ለ5 አደረጃጀትን ወይም በመተባባር መማርን በአመለካከት ተቀብሎ ወደ ተግባር ከመቀየር ይልቅ አደረጃጀቱን ማጥላላትና ለመሳተፍ ፍቃደኛ አለመሆን፣ በራስወዳድነት ስሜት መታጠር፤ ከመረጃ መረብ የተገኘን ሁሉንም ሳያመዛዝኑ የሚቀበሉ፣ በስርቆት ተሳትፈው የሚያዙ፣ አደንዛዥ ዕፅ ተጠቅመው ለችግር የሚጋለጡና ፆታዊ ትንኮሳ የሚያደርሱ፣ የጥልቅ እውቀትና ክህሎት ባለቤት ሆነው እንዲወጡ በጥብቅ የሚከታተሉና የሚደግፏቸውን መምህራን በበጎ የማያዩትንና የጥላቻ ስሜት የሚያሳዩትን ተማሪዎች ቁጥር ቀላል አይደለም። የአገሩን ባህል የማያውቅ፣ ልዩነትንና መቻቻል፣ አብሮ የመኖር ባህልን በመተው ራሱን ብቻ የማስቀደም አስተሳሰቦች እየጎሉ መምጣቱ ለትምህርት ሥርአታችን ብቻ ሳይሆን እንደአገርም በጣይ አሳሳቢ ጉዳይ ነው።[73] ሌላ በኩል በኢትየጵያ የከፍተኛ ትምህርት ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ተማሪ ተማሪን የገደለበት አሳዛኝ ክስተትም ተፈጥሯል።

3.2.6.2 መምህራን

በከፍተኛ ትምህርት የሚገኙ መምህራን አገራችን በከፍተኛ ደረጃ የሚያስፈልጋትን ብቁ የሰው ኃይል በእውቀት፣ በክህሎትና በሥነ ምግባር በማነጽ ሚናቸው እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። በመሆኑም አብዛኛዎቹ መምህራን መምህርነት እጅግ የከበረ ሙያ መሆኑን የሚገነዘቡ፣ ተማሪዎችን ብሎም ቀጣይ ትውልድንና አገር የመቅረፅ ሃላፊነትን ክብደት የሚረዱ በተከታታይ ራሳቸውን በማብቃት ይህንንም ተማሪዎቻቸውን ለመጥቀም የሚተጉ፣ አገራችን ከድህነት ጋር የገጠመችውን ትግልና ያስመዘገበቸውን ድልና ፈተናዎቹን በአግባቡ የሚረዱና ሌሎች እንዲረዱት የሚያደርጉ ናቸው። ይሁንና ሙያቸውን ለማዳበር የግል አቅም ግንባታ ሥራ የማይሰሩና ከዘመኑ

[73] ትምህርት ሚኒስቴር። (ግንቦት/2009)። የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የ2010 በጀት ዓመት ጠቋሚ እቅድ።

ቴክኖሎጂ ጋር ለመሄድ ጥረት የማያደርጉ እና ለትምህርት ጥራት መረጋገጥ የማይንቀሳቀሱ ጥቂቶች አይደሉም። የመምህራን ዋና ሥራ ተማሪን በማብቃት የትምህርት ጥራትን ማምጣት መሆኑ እየታወቀ ይህንን ለማምጣት የሚያስችል ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴን፤ ተከታታይ ምዘናን፣ ለሴት ተማሪዎችን የማጠናከሪያ ትምህርት ከመስጠት አንፃር እና በመተባበር መማር በአመለካከትም ሆነ በተግባር ተቀብሎ ተግባራዊ የማያደርጉ መምህራን ቁጥር ቀላል አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ ቁጥራቸው ውስን ቢሆንም ሙያው የሚፈልገውን ዝግጅትና ባህሪ ፈፅሞ የሌላቸው፣ ኢ-ዲሞክራቲክ የሆኑና በአካዳሚክ ነፃነት ሽፋን የራሳቸውን አመለካከቶች በሌሎች ላይ ለመጫን የሚሞክሩ፣ ውጤት በተማሪው የሥራ ትጋት የተገኘ መሆኑ ቀርቶ የመምህራኑ ችሮታ ተደርጎ የሚያስቡ፣ የከፍተኛ ትምህርት ማህበረሰብ መገለጫ የሆነውን ምክንያታዊነትንና ሰላማዊ የሃሳብ ትግልን ተቃርነው የሚሰሩ፣ በሱስ የተጠመዱ፣ ከሰዓት በኋላ ክፍል የማይገቡ፣ በፀጉር አቆራረጣቸውም ይሁን በአለባበሳቸው ዓርዓያ መሆን የሚከብዳቸው፣ በያታዊ ትንኮሳ ተሳትፈው የሚገኙ፣ የመልካም አስተዳደር ችግር ሲያጋጥም የመፍትሔው አካል ከመሆን ይልቅ ችግሮች የሚያባብሱ፣ በብሄር፣ በሃይማኖትና በአካባቢ ልጅነት ተማሪን ለያይተው ውጤት የሚሰጡ መምህራን መኖራቸው ለምንገነባው የሰው ሀብት ልማት ትልቅ ተግዳሮት ነው። ስለሆነም መምህራኑን በተልዕኳቸው ልክ ማዘጋጀት ተገቢና ትኩረት ልንሰጠው የሚኖርብን ጉዳይ ነው።[74]

3.2.6.3 የከፍተኛ ትምህርት አመራር

የከፍተኛ ትምህርት በመምራት በየደረጃው ያለው አመራር ማለትም ቦርዶች እና በየደረጃው ያለው የዩኒቨርስቲው አመራር ሥላማዊ የመማር ማስተማር ሂደትን በመፍጠር፣ ዩኒቨርስቲዎች ተልእኳቸውን በሚገባ እንዲወጡ በማድግ ረገድ ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። ከዚህ አንጻር ተቋማቱን በመምራትና ተልዕኮዎቻቸውን እንዲወጡ ድጋፍ በመስጠት፣ መልካም አስተዳደር ለማስፈንና ሰላማዊ መማር ማስተማር እውን ለማድረግ በየጊዜው ከዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ጋር ውይይቶችና ክትትሎች የሚያደርጉ ቦርዶች ቁጥር እየጨመረ ይገኛል። ይህም ሆኖ ቦርዶች ከተሰጣቸው ሀገራዊ ትልቅ ኃላፊነት አኳያ ተገቢውን የስራ እቅድ አዘጋጅቶ ወደስራ በመግባትና በየጊዜው ያለውን አፈፃፀም በመከታተልና ሪፖርት በማድረግ በኩል ሰፊ ክፍተት አለባቸው። በአንዳንድ ተቋማት የዩኒቨርሲቲዎችን ቁልፍ ማነቆዎች ለመፍታት የሚያደርጉት እርዳታ አነስተኛ ሆኖ አልፎ አልፎ ደግሞ ጭራሹን የሌለ ሆኖ ይታያል። ከዚህ ሌላ የቦርድ ስብሰባን ዩኒቨርስቲ ካለበት ከተማ ውጭ ማካሄድ፣ በውስን አጀንዳ ላይ ማተኮርና ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን ያለማግኘት ችግር ያልተፈታ ጉዳይ ነው። በተማሪዎች፤ በሠራተኞችና ሌሎች አካላት በተቋማት ላይ የሚነሱ የመልካም አስተዳደር መጓደል ፈጣን ምላሽ እንዲያገኙ የሚደያደርጉት ክትትል አናሳ በመሆኑ ወደ አላስፈላጊ የመልካም አስተዳደር ችግር ሲያመራ ይስተዋላል። ከሁሉ በላይ በተቋማት የሚከናወኑ ምርምሮች የአካባቢውን እንደዚሁም የአገርን ችግር በሚፈቱበት አኳኋን እንዲፈፀሙ፤ የኘሮግራሞች አከፋፈት አገራዊ ፍላጉትን ማዕከል ያደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ፤ የኢንዱስትሪ ዩኒቨርስቲ ትስስር በአግባቡ እንዲፈጸም ለማድረግ የሚሰጡት አመራር በቂ ባለመሆኑ ለቀጣይ ዓመታት ትኩረት ተሰጥቶት ሊስተካከል ይገባዋል። እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም መላውን የዩኒቨርስቲ ማህበረሰብ አግኝቶ ማወያየት ላይ አሁንም ከተቋም ተቋም ቢለያይም ክፍተት ይታይበታል።

[74] ትምህርት ሚኒስቴር። (ግንቦት/2009)። የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የ2010 በጀት ዓመት ጠቋሚ አቅድ።

የዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ አመራርን በተመለከተ ተቋማት ላስቀመጧቸው ግቦች መሳካት አለመሳካት ከፍተኛ አመራሩ ያለውን ሚና ተተኪ እንደሌለው ይታወቃል። አብዛኞቹ የዩኒቨርስቲ አመራር አባላት በእ.ት.ዕ ያስቀመትናቸውን የተለጠጡ ግቦች ለማሳካት ሌት ተቀን የሚተጉ፣ እልህ አስጨራሽ በሆኑ ችግሮች ሳይፈቱ መስዋትነት በመክፈል ጭምር ለተመዘገበው ውጤት ሲረባረቡ ቆይተዋል። በባለፉት ዓመታት የተካሄዱት የአመራር ማስተካከልና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች እያደገ ለመጣው ውጤታማና ሰላማዊ መማር ማስተማር እንደዚሁም ለተመዘገበው የመልካም አስተዳደር መሻሻል የነበራቸው አስተዋፅኦ እንደተጠበቀ ሆኖ የአመራሩ ቁርጠኝነት ግን ለቀጣይ ስራችንም ጭምር ምቹ ሁኔታ መኖሩን የታየበት ነው። ይሁን እንጂ በከፍተኛ አመራሩ ረገድ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የችግሮቹን ምንጮች ከመለየት፣ ዕቅድ ከማውጣትና በእቅድ ከመፍታት በደራሽ ችግሮች ላይ ብቻ ማተኮር ይታይባቸዋል። የትምህርትና ቴክኖሎጂ ሰራዊት ግንባታንና ኪራይ ሰብሳቢትን ለመታገል፣ መልካም አስተዳዳር ለማስፈንና የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ያለውን ጠቀሜታ ተረድቶ በቂ ትኩረት በመስጠት አፈፃፀሙን ከመከታተል በያዝ ለቀቅ ከማደራጀት ያለፈ ያስገኘውን ውጤት በጉልህ ለማየትም አላስቻለም። በመማር ማስተማሩ ስራ ውስጥ ከፕሮግራሞች ቀረፃ፣ መማር ማስተማር እስከ ምረቃ ያለውን ሂደት ከጫፍ እስከ ጫፍ ወጥ በሆነ በተልዕኮና በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት እየተፈፀመ ስለመሆኑ የሚያደርጉት ክትትል ክፍተት ይስተዋልበታል። መማር ማስተማሩን በላቀ መልኩ ለማካሄድ አስቻይ የሆነ ሥርዓትን በመዘርጋት፣ ምቹ የትምህርት ከባቢን በመፍጠርና ግብዓት በማሟላት የተሰጠው አመራር በቂ እንዳልነበረ ከግምገማዎቻችን ለመረዳት ችለናል። የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎቻችን ችግር ፈቺ በሆነ መልኩ እንዲካሄዱ የተዘረጋው ሥርዓት፣ የተመደበው ሃብትና የተመራበት አግባብ እንደዚሁ በቂ አልነበረም። በተመሳሳይ የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎቻችን በዛም ውስጥ የኢንዱስትሪ ዩኒቨርስቲ ትስስሩ የአገራችንን ችግር በዘላቂ መልኩ በሚፈታ መልኩ ላለመደራጀቱና ላለመመራቱ ከዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ አመራር ጋር ይያያዛል። መላውን ተቋም ተረድቶ እያንዳንዱ አደረጃጀት ያጋጠመውን ማነቆ በመለየት ተገቢውን ድጋፍ የመስጠትና ለተቋሙ ማህበረሰብ ተደራሽ በመሆኑ ፈጣን ምላሽ የሚሹ ጉዳዮችን ከመፍታትም አኳያ አሁንም ያልተቀረፉ ችግሮች ይስተዋላሉ። የተዘረጉ ስርዓቶች በትክክል ስለመተግበራቸው በቂ ክትትል አድርጎ ከሥርዓት የሚወጡትን ከማረም ይልቅ በሪፖርት ብቻ ላይ በመመስረት ለመምራት የሚደረግ አካሄድ ይታያል። አልፎ አልፎና በጥቂት አመራሮች ዘንድ የሚታይ ፍፁም ዲሞክራቲክ ያልሆነ ባህሪና በተቋሙ ያለመገኘት ችግር ይስተዋላል። በመጨረሻም ፈጻሚውን በማብቃት፣ ተከታታይነት ያለው ግብረ መልስ የመስጠት፣ የማሳተፍና የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር በማድረግ ስራተኛውን መዝኖ የማበረታታትና እውቅና የመስጠት ሥራ በበቂ ስላልተሰራ ለቀጣይ ጊዜያት የቤት ስራ ሆኖ ሊያዝ ይገባዋል። በተጨማሪም ተቋሞቻቸውን ዜሮ የአዲት ግኝት ከማድረግ አንፃር፤ ከትምህርት ሚኒስትር ለሚፈለጉ መረጃዎች ፈጣን ምላሽ ያለመስጠት፤ የኃብት አጠቃቀም ችግር፤ የንብረት አያያዝ ጉድለት፤ በዩኒቨርስቲዎች ዙሪያ በተማሪዎች ሰነ-ምግባር መጓደል መንስኤ የሚሆን ችግሮችን በመለየትና ከአካባቢው አስተዳደር ጋር በመሆን በቅንጅት አለመስራት፤ የግዥ ስርዓት መጓደል፤ የሁለተኛውና ሦስተኛው ትውልድ አብዛኞቹ ዩኒቨርሲቲዎች ስታንዳርዱን የጠበቀ የካምፓስ ኔትዎርክ አለመኖር ያልተፈቱ መሠረታዊ ችግሮች ናቸው።

መካከለኛው አመራር (ዲኖች/ዳይሬክተሮችና ትምህርት ክፍል ኃላፊዎች) በተመለከተ የዩኒቨርሲቲውን ራዕይ በሚያሳካና በተልዕኮ መሰረት እየተፈፀመ ስለመሆኑ ለፈፃሚው የሚሰጡት ድጋፍና ለስኬቱም የሚያደርጉት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። ባለፉት ዓመታት ከጊዜ ወደ ጊዜ የአመራርና አስተዳደር ብቃታቸው እየተገነባ የመጣ ሲሆን ለተቋማዊ አፈፃፀም መሻሻል ደጋፊ ኃይል ሆነው የወጡ በርካቶች ናቸው። በአጠቃላይ የመካከለኛው አመራር በቂ መሰረተ ልማት ባልተሟላባቸው ተቋማትም ጭምር የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት፣ ላቦራቶሪዎችና ወርክሾፖች እንዲሟሉ የበኩላቸውን ጠንካራ ሰራ ሰርተዋል። መልካም አስተዳደር እንዲሰፍንና የአገልግሎት አሰጣጡ እንዲሻሻል ገንቢ ሚና ተወጥተዋል። ይሁንና ቁልፍ የሆነውን መልካም አስተዳደር ማስፈንና ማረጋገጥ፣ የትምህርት ጥራትን ማስጠበቅና ለሰላማዊ መማር ማስተማር የሰጡት ትኩረትና አመራር ክፍተት ይስተዋልበታል። ውጤት ለማስመዝገብ ሁነኛ መሳሪያ ነው ተብሎ ተሰፋ የተጣለበት የትምህርትና ቴክኖሎጂ ሰራዊት ግንባታ በአግባቡ ስላልተያዘ ችግሩን መቅረፍ አልቻሉም። የተማሪዎችንና የመምህራኑን ችግር በማድመጥ፣ በቅርበትና በፍጥነት መልስ መስጠት ያላቸውን እድል ሳይጠቀሙ በመቅረታቸው ችግሮቹ ተጠራቅመው አልፎ አልፎ ውስብስብ ሲሆኑ ይስተዋላል። የለውጥ መሳሪያዎችና ፕሮግራሞች ለውጤታማና ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥ ያላቸውን ጠቀሜታ ተገንዝበው በሙሉ ከመተግበር አሁንም አልፎ አልፎ እንደሚታየው ለዩኒቨርሲቲ አይሰራም ብሎ ማመንታትም ይታይባቸዋል። ከዚህም ሌላ መምህራንንና ሌሎች ሰራተኞችን በመከታተል፣ በውጪ አካል እንዲሰራ መደረግ ያለባቸውን እየለዩና እያጠኑ በማስወሰን ተግባራዊ እንዲደረጉ ባለመደረጉ የትምህርት አመራሩ በዩኒቨርስቲው ዋና ተልእኮው ጊዜውን ማጥፋት ሲገባው በአስተዳደራዊ ጉዳዩች ላይ ማለትም የሰራተኞች ቅጥር፣ ዝውውር፣የደረጃ እድገት እና ስንብት እንዲሁም በውጪ መምህራን ስምሪትና ቁጥጥር ዙሪያ ጊዜውን ሲያጠፋ ይውላል።[75]

4 የትምህርት አመራርና አደረጃጀት

4.1 ከወቅቱ ጋር ያልተሳሰረ የትምህርት ፍልስፍና/ዓላማ

በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ አምስት አጠቃላይ የትምህርት ዓላማዎችና አሥራ አምስት ዝርዝር አላማዎች ተቀምጠዋል። በዚህም መሠረት የተለዩ ስትራቴጂክ እቅዶች፣ የትምህርት ስታንደርዶች፣ ማእቀፎች፣ መመሪያዎች፣ ወዘተ. እየተዘጋጁ ፖሊሲውን ለማስፈፀም ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። ይሁንና ብቁ ዜጋ ከመገንባት አንፃር የፖሊሲው ዓላማዎች በየጊዜ እየተፈተሹ ሲስተካከሉ አይታዩም። ወቅቱ የሚጠይቀው የሰው ሀብት ልማት አለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት በመሆኑ ከዚህ ጋር የሚናበብና የሚስማማ የትምህርት ዓላማ/ፍልስፍና የለንም። በመሆኑም አገራዊ እና አለም አቀፋዊ ፍላጐቶች ሊያሟላ የትምህርት አላማ ሊኖረን ይገባል።[76]

[75] ትምህርት ሚኒስቴር። (ግንቦት/2009)። የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የ2010 በጀት ዓመት ጠቋሚ አቅድ።
[76] Ministry of Education. (2017.) Ethiopian Education Development Roadmap: An integrated Executive Summary (Draft).

4.2 የሕጻናትን እድገት ከሥራ አላም ጋር ያላገናዘበ የትምህርት መዋቅር

አሁን እየተከተልን ያለው የትምህርት መዋቅር ቅድመ መደበኛ ትምህርት ከ4 አመት እስከ 6 አመት እድሜ፤ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ከ7 አመት 14 አመት እድሜ /ከ1ኛ ክፍል እስከ 8ኛ ክፍል/፤ ሁለተኛ ደረጃ ከ15 አመት እስከ 16 አመት እድሜ /9ኛ ክፍል እና 10ኛ ክፍል/፤ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት 17 አመት እና 18 አመት እድሜ /11ኛ ክፍል እና 12ኛ ክፍል/ ሆና ተደራጅቷል። ይሁንና ይህ አደረጃጀት ከሕጻናት እድገት፣ በየደረጃው የትምህርት መዋቅሩ ከሚያስፈልገው ባህሪ ጋር በሥርአት የተቀናጀ አይደለም። የዩኒቨርስቲ የትምህርት ጊዜ እንዲቀንስ ተደርጐ ሥርአተ ትምህርቱ ወደ 11ኛ ክፍል እና 12ኛ ክፍል እንዲወርድ ተደርጓል። በተመሳሳይ የትምህርት ይዘቶች ወደ ታችኛው ክፍል እንዲወርዱ በመደረጉ ከሕጻናቱ የእድሜ ብስለት ጋር ሊጣጣሙ አልቻሉም። ቀደም ብለው 10ኛ ክፍልን እንዲያጠናቅቁ መደረጉም በእውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከት ሳይበስሉና በአካል ሳይደረጁ ወደ ቴክኒክና ሙያ እንዲሁም መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ትምህርትና ወደ ሥራ አለም እንዲሰማሩ ማድረጉ የተወሳሰበ ችግር ፈጥሯል።[77]

4.3 በቀጣይነት ራሱን እያበቃ የማይሄድና ለሌሎች አቅም መሆን ያልቻለ የትምህርት አመራርና አስተዳደር

የትምህርት አመራሩ የተማሪዎችን የመማር ውጤት በማጉልበት በኩል ጉልህ ድርሻ አለው። ይህ የሚሆነው ደግሞ ብቃት ያላቸውን አመራሮች ግልጽነት በተሞላው መልኩ በመመልመል፣ በመመደብ፣ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ በማብቃት ለሌሎች አቅም መሆን ሲችሉ ነው። ይሁንና ከፌደራል እስከ ትምህርት ቤት ያለው የትምህርት አመራር ምልመላ፣ ምደባ፣ የሥልጠና ሥርአት አፈጻጸማችን ሲታይ ግልጽነት የጐደለው እና ያለውድድር ምደባ የሚካሄድበት ነው። ከዚህ በተጨማሪም የትምህርት አመራር ልማቱ እና ትግበራው ጥናትን መሠረት ያደረገ አይደለም።[78] በተለይ የትምህርት ሚኒስቴር በየደረጃው ያለው አመራር ለክልሎች አቅም በመሆኑ የትምህርት ሥርአቱ በመደገፍ በኩል ጉልህ ክፍተቶች አሉበት። የትምህርት አመራሩ በትምህርት ሥርአቱ የሚፈለጉ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን የትምህርት ዘርፉን ሥራ የማቀድ፣ የመምራት፣ የመከታተልና የመገምገም እውቀት እና ክህሎት አቅም እንዲኖረው ቢጠበቅም በዚህ ደረጃ ላይ የሚገኝ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪም በየደረጃው የተጠያቂነት አሠራር ባለመዘርጋቱ የትምህርት ጥራት እያሽቆለቆለ ለመምጣት ምክንያት ሆኗል። በሌላ መልኩ በየደረጃው ያለው የትምህርት መዋቅር ማለትም ከፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር፣ ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ትምህርት ቤት ተግባርና ኃላፊነታቸው ግልጽነትና ተጠያቂነት የጐደለው ነው። የትምህርት ሕግ አለመደንገጉም ጭምር የኃላፊነትና የተጠያቂነቱን ሥርአት በሚገባ ተገንዝቦ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ሆኗል።

[77] Ministry of Education. (2017.) Ethiopian Education Development Roadmap: An integrated Executive Summary (Draft).
[78] Ibid.

4.4 በችግር የተወሳሰበ የሀብት አቅርቦትና አጠቃቀም

በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው የመንግሥት የፋይናንስ ድጋፍ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትና ሥልጠና 10ኛ ክፍል እስከሚጠናቀቅ ድረስ እንደሚሆን ያመለክታል።[79] በዚህ መሠረት መንግሥት ከፍተኛ በጀት ይመድባል። የአለም ባንክ በቅርቡ ይፋ ባደረገው ጥናት ከሳህራ በታች ካሉ አገሮች ውስጥ ከፍተኛውን ማለትም ከ25% በላይ የመንግሥት በጀት በግንባር ቀደምነት ሀገራችን እንደምትመድብ አረጋግጧል።[80] ምንም እንኳን ከፍተኛ በጀት የተመደበ ቢሆንም ሥርጭቱ ፍትሐዊ አይደለም። የፕሮግራሞችን የበጀት ምደባ ስናይ ለመጀመሪያ ደረጃ 45%፣ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት 12%፣ ለከፍተኛ ትምህርት 25% እንዲሁም ለቴክኒክና ሙያ 5% ነው። ከዚህ ውስጥም 85% በጀት የሚመደበው ለደመወዝ ነው። በመሆኑም ለትምህርት ጥራት የሚሆን አስፈላጊ የላብራቶሪ፣ የወርክሾፕ፣ ለጥናትና ምርምር፣ ወዘተ. የሚመደበው በጣም ዝቅተኛ በጀት ነው። ይህም ሆኖ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በትምህርት ተቋማት በተለይም በከፍተኛ ትምህርት የሚባክነው ሀብት በጣም አሳሳቢ ነው።

4.5 ወቅታዊና ተአማኒነት የጐደለው የትምህርት መረጃ ሥርአት

የትምህርት መረጃ የትምህርትና ሥርአታችን ያሉበትን ችግሮች ለመለየትና ውሳኔ ለመሰጠት ቁልፍ አቅም ነው። ይሁንና በትምህርት ሥርአታችን ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ችግር አለ። የመጀመሪያው መረጃዎቹ ከትምህርት ተቋማት ወቅቱን ጠብቀው አይላኩም። ሁለተኛው የሚላኩትም መረጃዎች ተአማኒነታቸው አጠራጣሪ እየሆነ ዳግም ወደ ማጣራት ሥራ የሚያስገቡ ናቸው። ሦስተኛው ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ መረጃን መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣ ወቅታዊ ማድረግ ሲገባ የአቅም ውስነት በጉልህ የሚታይና ፈጣን ማስተካከያ ማድረግ የሚሻ ነው። ወቅታዊና ታአማኒ መረጃ ባለማደራጀታችን ምክንያትም ከአለም አቀፍ የትምህርት መረጃ ሥርአት ወደኋላ እያስቀረን ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪም ሀብት በማፈላለግ የትምህርት ሥርአቱን ለማደገፍ እንቅፋት እየሆነ ነው።

4.6 ከፖሊሲውን ያፈነገጠ አተገባበር

የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው ዜጐች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ፣ ለአገር አቀፍ ግንኙነት የአማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት እንዲሰጥ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እንደ አንድ የትምህርት አይነት እንዲሰጥ፣ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲሰጥ፣ እንደተማሪዎች ፍላጐት ለአገራዊ አንድነት ተጨማሪ የአገር ውስጥ ቋንቋ፣ የአለም አቀፍ ግንኙነትን ለማስፋት ደግሞ ሌላ አንድ ተጨማሪ የውጭ ቋንቋ ማስተማር እንደሚገባ አስቀምጧል።[81] በዚህም መሠረት በ51 የአፍ-መፍቻ ቋንቋዎች ትምህርት እየተሰጠ ይገኛል። ይሁንና በፖሊሲው ከተቀመጡት ውስጥ አንድ ተጨማሪ የአገር ውስጥ ቋንቋ፣ የውጭ አገር ቋንቋ አሰጣጥ

[79] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት። (መጋቢት፣ 1986)። አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ። አዲስ አበባ፣ ሚጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ገጽ 16።

[80] The World Bank. (2018). Facing Forward: Schooling for Learning in Africa

[81] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት። (መጋቢት፣ 1986)። አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ። አዲስ አበባ፣ ሚጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ ገጽ 12-13።

እስካሁን የተተገበሩ አይደሉም። ምንም እንኳን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የትምህርት ቋንቋ አሰጣጥ በክልሎች የሚወሰን ቢሆንም አሁን ያለው አተገባበር የተዛባ ጉድለትና ወጥነት ያለው አይደለም።

ማጠቃለያ

የትምህርትና ሥልጠና ሥርአታችን በበርካታ ችግሮችና ተግዳሮቶች የተሞላ ነው። ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፤

- የትምህርትና ሥልጠና ሥርአታችን በንድፈ-ሃሳብ ላይ እንጂ ተግባር፣ ክህሎትና ፈጠራ ላይ ያተኮረ አይደለም፤ የምዘና ሥርአታችንም እውቀትን ብቻ የሚመዝን ነው። ዜጐችንም በ16 አመታቸው የሁለተኛ ደረጃ እንዲያጠናቅቁ በማድረግ ከትምህርትና ሥልጠና ሥርአቱ ውጪ እያደረግናቸው ነው።
- እስካሁን እየተገበርን ያለው የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ሥራ ፈላጊ እንጂ ሥራ ፈጣሪ ትውልድ እየፈጠረልን አይደለም። በዚህ ምክንያትም ሕብረተሰቡ በትምህርትና ሥልጠና ሥርአታችን የጥራትና የተገቢነት ጥያቄ እያነሳ ይገኛል። በተለይ የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን ልጆች ከሥራ አፈናቅለን የተሻለና የሰለጠነ ትውልድ እንፈጥራለን ብለን ወደ ትምህርት ቤት አምጥተን ከተማሩ/ከሠለጠኑ በኋላ ወደ ቤተሰቦቻቸው ተመልሰው ሥራ ሲያግዙና ሥራ ሲፈጥሩ አይታዩም።
- በትምህርትና ሥልጠና የሚያልፈው ትውልድ ከትምህርትና ሥልጠናው እውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከት በበቂ ሁኔታ ይዞ ከመገኘት ይልቅ የምስክር ወረቀቱን/ዲኘሎማውን ይዞ መገኘትና ዲኘሎማ አምላኪ ሆኗል፤ በሂደቱም የኩረጃና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ጉልቶ ይታያል።
- በትምህርትና ሥልጠና ያሉት ሁሉም ዘርፎችና ባለድርሻ አካላት ተቀናጅቶና ተናቦ አይሰሩም።
- የምርምርና የቴክኖሎጂ ሥራችንም ጉልበቶ ኢኮኖሚው በሚፈለገው መጠን እያገዘ አይደለም።
- ከሌሎች አገራት ጋር ሲነፃፀር የትምህርትና ሥልጠና ጥራታችን በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ራሳችንን የምናይበት ሥርአት አልዘረጋንም።
- ሥርዓተ-ትምህርታችን የአገር ፍቅርን፣ ብዝሃነትን፣ የመቻቻል፣ አብሮ የመኖር፣ ግብረገብነትን፣ ወዘተ. እሴቶችን በእውቀት፣ በክህሎትንና በአመለካከት በተጨባጭ ማስረጽ ባለመቻላችን ግለኝነት እያየለ፤ ብሔርተኝነት እየገነነ፤ የአገር ፍቅር እየደበዘዘ እየመጣ ነው።

በመሆኑም አማራጫችን ጥፍሩን በመከርከም፤ ምንቃሩን ,በመሳል ኑሮውንና እድሜውን እንደሚያራዝመው ንስር አሞራ በጥገናዊ ለውጥ መቀጠል ወይስ መሠረታዊ ለውጥ በማምጣት የምናልመውን እድገትና ብልጽግና ላይ መድረስ?

ክፍል አራት

የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ማሻሻያ ሃሳቦች

አጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በመጋቢት ወር 1986 ተቀርጾ በ1987 ዓ.ም. ወደ ትግበራ መገባቱ ይታወሣል። በፖሊሲው ላይ የተቀመጡትን የትምህርት ዓላማዎች ላለፉት ሃያ አራት አመታት ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። በዚህ ሂደት አሁን ላለንበት ደረጃ ያደረሱንን የሰው ኃይል በማፍራት የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካዊ ልማቶች ማምጣት ችለናል። ይሁንና በትግበራ ሂደት በክፍል ሁለት እንደተገለፀው የአገራችን ዋና ዋና የትምህርትና ሥልጠና ችግሮችና ተግዳሮቶች ተለይተዋል። እነዚህ ችግሮች ጥናትን መሠረት ያደረገ የማሻሻያ ሥራ ለመሥራት እንዲቻል ለአሥራ አምስት አመት የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ግብአት እንዲሆን የጥናት ቡድን ተቋቁሞ በተጠናው ጥናት መሠረት ቡድኑ ለችግሮቹ ተግዳሮቶቹ መፍትሔ ሊሆን የሚችሉ ምክረ-ሃሳቦችን አቅርቧል።[82] እነዚህ ምክረ-ሃሳቦች የጥናት ቡድኑ ሃሳቦች ከጥናቱ ተተርጉመው የቀረቡ ናቸው። በእነዚህ ምክረ-ሃሳቦች ላይ ወደፊት በዝርዝር በመወያየት የጋራ መግባባት ላይ የሚደረስ ይሆናል። ምክረ-ሃሳቦቹም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. **የትምህርት ፍልስፍና**
   - ዜጐች በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ብቁና በምክንያታዊ ትንተና የሚያምኑ፣ በሙያቸው ብቃት ያላቸው በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ብቁ ዜጋ አድርጐ አጠቃላይ ሰብእናቸውን መገንባት፣
   - ሥራ ፈጣሪዎች፣ አዳዲስ ግኝቶችን አፍላቂዎች፣ ጠንካራ የሥነ ምግባርና ግብረገባዊ እሴቶችን የተላበሱ እና ለሕግ ዘብ የቆሙ ዜጐችን ማፍራት፣
   - ብዝሃነትን ላካተተው አገራዊ አንድነትና ሠላም ዘብ እንዲቆሙ ማድረግ፣

2. **የትምህርት መዋቅር**
   - ቅድመ-መደበኛ ትምህርት ሕፃናት ከ4 - 5 እድሚያቸው እንዲማሩ ማድረግ፣
   - የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት 6 አመት ከ1ኛ- 6ኛ ክፍል እንዲሆን፣
   - ዝቅተኛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከ7ኛ - 8ኛ ክፍል እንዲሆን፣
   - ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከ9ኛ – 12ኛ ክፍል እንዲሆን፣
   - የዩኒቨርስቲ ትምህርት ቆይታ 4 አመት እንዲሆን (ለኢንጂነሪንግ 5፤ ለሜዲሲን 6)፣

[82] Ministry of Education. (2017.) Ethiopian Education Development Roadmap: An integrated Executive Summary (Draft).

3. የመምህራን ዝግጅትና ምልመላ

3.1 ምልመላ

- ሁሉ-አቀፍ ማለትም የምልመላ፣ የመረጣ፣ የሥራ ላይ ሥልጠና፣ እውቅና የመስጠት፣ ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ፣ የሥልጠና እድል፣ የማልማት፣ የሙያ ፍቃድ፣ ዝውውር፣ አገልግሎትን የማቋረጥ ፣ ወዘተ. ያካተተ መምህራንን የሚያዘጋጀና የሚያለማ ፖሊሲ ማዘጋጀት፣
- እጩ መምህራንን 12ኛ ክፍልን የተሻለ የመማር ውጤት ካመጡት ውስጥ መምረጥ፣
- በዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ምደባ ወቅት የመምህርነትን ሙያ እንደ አንድ የሥልጠና መስክ ማካተት፣

3.2 የመምህራን የሥራ ምደባና ዝውውር

- የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ዝውውርን በትምህርት ሚኒስቴር አማካኝነት እንዲሠራ ማድረግ፣
- ብዙሃነትን በሚያጐለብት መልኩ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ምደባ ፖሊሲ ማስተዋወቅ፣

3.3 የመምህራን ሥልጠና ተቋማትና አሠልጣኝ

- በሁሉም ደረጃዎች የእጩ መምህራንን ሥልጠና ጥራት ማሻሻል
- የመምህራን ሥልጠናና የትምህርት መሰጫ ቋንቋ እንዲጣጣም ማድረግ፣
- የመምህራን ትምህርት ሥርአተ ትምህርት እጩ መምህራን ከምረቃ በኋላ ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ፣
- በመምህራን ትምህርት ላይ ትኩረት አድርጐ የሚሰራ/የሚሰሩ የመምህራን ትምህርት ዩኒቨርስቲዎች ማቋቋም፣
- መምህራንን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ የተለያዩ አማራጮችን መጠቀም (የተጣመረውን እንዲሁም የኦንላይድ ትምህርት ጨርሰው የሚሰጠውን የአንድ አመት የመምህርነት ሙያ ሥልጠና ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ይይዛል)
- መሠረታዊ ክህሎት፣ የሕይወት ክህሎት እንዲሁም ከፍተኛ የአስተሳሰብ ክህሎትን ማስተማር፣
- አንድ አገር አቀፍ የመምህራን የምርምር እና የስትራቴጂ ኢንስቲትዩት መመሥረት፣
- በሁለተኛ ደረጃ የመምህራን ትምህርት ላይ የሚሠሩ በሚገባ የተደራጁ አምስት የልህቀት ማእከላትን ማደራጀት፤ በየክልሉ ቢያንስ አንድ፣ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ የመምህራን ትምህርት የልሕቀት ማእከል ኮሌጅ ማደራጀት፣
- የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ብቁ መምህር መሆን የማይችሉትን እጩዎችን ቀበላ በመከላከል ለትምህርት ጥራትና አግባብነት ዘብ የመቆም ሚናቸውን እንዲጫወቱ አቅማቸውን ማጐልበት፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሁሉም ተቋማትና እጩዎች ገዢ የሆነ የመመልመያ መስፈርት ማዘጋጀት (የኮታ አሠራርን ማስወገድ)፣

3.4 አሠልጣኝ መምህራን ምልመላ

- የመምህራን አሠልጣኞችን ለመለየት፣ ለማዘጋጀትና ለማልማት የሚያስችል ማእቀፍ ማዘጋጀት፣

3.5 ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ

- ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ኘሮግራምን በትምህርት ቤትም ሆነ በኮሌጆች ተቋማዊ ማድረግ፣
- ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ኘሮግራም የትምህርት አይነት እውቀትንና የማስተማር ዘዴ ዝግጁነት ክፍተቶችን እንዲመልስ አድርጐ እንደገና ማሻሻል፣
- የክረምት የትምህርት ደረጃ ማሳደግ ሥልጠናን በመተው ለተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ብቻ መጠቀም፣
- ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ኘሮግራም ከደረጃ እድገት ጋር እና ከሙያ ፍቃድና እድሳት ጋር ማስተሳሰር፣

3.6 የመምህራን ሥልጠና ደረጃና ጥቅማጥቅም

- የመምህራን የሥልጠና ደረጃ በተመለከተ፣
    - ለቅድመ-መደበኛና ለመጀመሪያ ትምህርት በ12+3 ደረጃ የሰለጠኑ፣
    - ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (9-10)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው፣
    - ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (11-12) ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው፣
- የመምህራንን ጥቅማጥቅሞችንና የማበረታቻ ዘዴዎች ማሻሻል፣ ቢያንስ ቢያንስ የመምህራን ደመወዝ ከሌሎች ሙያዎች ጋር ተመጣጣኝ/ተወዳዳሪ እንዲሆን ማድረግ፣ ጥቅማጥቅሞችን ማለትም ቤት፣ ትራንስፖርት፣ ነፃ ሕክምና፣ በጡረታ ወቅት ሙሉ ደመወዝ፣ በዝቅተኛ ወይም ያለ ወለድ የብድር አገልግሎት፣ ወዘተ. ማቅረብ፤ በአስቸጋሪ ቦታ ለሚሰሩ መምህራን አበላቸውን እንዲሁም ሌሎች ፓኬጆችን ማሻሻል፣

4. አጠቃላይ ትምህርት

- የቅድመ-መደበኛ ትምህርት፣ የመጀመሪያ ደረጃና የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የግዴታ ትምህርት እንዲሆን ማድረግ፣
- ተማሪዎች በታሪክ፣ በጂአግራፊ፣ በተግባቦት፣ ወዘተ. የተሻለ አመለካከት እንዲኖራቸውና ብዙሃነትን ያካተተ አንድነት እንዲያጐለብቱ ለማስቻል የአጠቃላይ ትምህርት ኘሮግራምን እንደገና መፈተሽ፣
- በሕፃናት መካከል ያሉትን ልዩነቶችን (ልዩ ተሰጥኦ፣ ክህሎት፣ ወዘተ. ያላቸውን ሕፃናት) የሚያስተናግድ የመማር ሁኔታ እንዲሁም ልዩነቶችን የሚያስተናግድ የማስተማር ዘዴን የሚያበረታታ ፖሊሲ ማዘጋጀት፣
- የጉልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት በፌድራል እና በክልሎች ራሱን በቻለ አደረጃጀት ተዋቅሮ እንዲሰራ ማድረግ፣

- የዝቅተኛውን መካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ መሸከም የሚችል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ማስፋፋት፣
- በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የቋንቋ፣ የሒሳብና የሣይንስ ትምህርቶችን ጥራት ማሳደግ፣
- ብቃትን መሠረት ያደረገና ከቅድመ-መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሙያ ጽንሰ-ሃሳቦችን ማካተት፣
- የገቢ አቅማቸው ዝቅተኛ ከሆኑ ቤተሰቦች ለሚመጡ የቅድመ መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች የድጋፍ ሥርአት መፍጠር፣

5. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና

5.1. የፖሊሲ ማእቀፎችን በመለከተ

- ከዝቅተኛ የክህሎት ሠራተኛ እስከ ከፍተኛ ቴክኒሻንና ቴክኒካል ኢንጂነሮች ሥልጠናዎችን የሚያካትት ፖሊሲ ማዘጋጀት፣
- ጥራት ያለውና ፍትሐዊ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ለማዳረስ ሠልጣኞች እያደሩ የሚሠለጥኑበት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆችንና ፖሌቴክኒኮችን ማቋቋም
- በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ውስጥ የማስተማሪያ ማእከላትን ማቋቋም (በክልሉ የኢንዱስትሪ አቅምና የተለያዩ ዘርፎች ውስን በሚሆኑት ጊዜ ተቋማቱ በራሳቸው ካምፓስ የሚሰጡትን የተግባር ሥልጠና ለማቀላጠፍ ይረዳል።)
- ፖሊሲ አውጪዎችንም ሆነ በተግባር የተሠማሩትን ባለሙያዎች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አመራሮችን ልማት ለማሳደግ የሚያስችል ሥርአት መዘርጋት፣
- በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ቴክኒካል ዩኒቨርስቲዎች በባለድርሻ አካላት (በሠራተኛ፣ በወላጅ፣ በኢንዱስትሪ፣ በአመራር) መካከል የባለቤትነትና ጥረትን ለመፍጠር የሚያስችል የአስተዳደር ሥርአት ማዘጋጀት፣
- በዞን ወይም በክልል ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማእከላት፣ ኮሌጆች እና ፖሌቴክኒኮችን ያቀፈ የክላስተር አስተዳደር ሥርአት ማስተዋወቅ፣
- ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ወደ መደበኛ ትምህርት ሥርዓት እንዲሁም መደበኛ ባልሆነ የክህሎት ሥልጠና ሥርዓት ሚሠለጥኑትን ውጤትን መሠረት በማድረግ የሚሸጋገሩበትን ሥርዓት መፍጠር፣

5.2. የሥልጠናና የገበያ ትስስር

- በተለያዩ ወረዳዎች የቴክኒክና ሙያ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እንዲሁም የሙያ ክህሎት ሥልጠና ማእከላትን መመሥረት (በግብርና፣ በጤና፣ በኮንስትራክሽን፣ በፈጠራ፣ በውሃና ንጽሕና፣ በኤሌትሪክና በሃይል አቅርቦት አገልግሎት፣ ወዘተ.)
- መደበኛ ያልሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና በመካከለኛ ደረጃ ሥልጠና (ከደረጃ 1-5) እንደ አጭር ሥልጠና መስጠት፣

- ለተለያዩ ሙያዎች ገበያ ማፈላለግ፣ የሠለጠኑ ቴክኒሽያኖች በአለም አቀፍ ካምፓኒዎች እንዲቀጠሩ ትስስር መፍጠር፣

5.3. የሥልጠና ተቋማት እና አሠልጣጠን

- የተለያዩ የሙያ የሥልጠና ፕሮግራሞችን የሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆችና ፖሊቴክኒኮችን በአገሪቷ በሚገኙ ስትራቴጂ ቦታዎች መመሥረት፣
- አህጉራዊና አለም አቀፍ የክህሎት ሠራተኞችና ቴክኒሽያኖች ሥልጠና ተቋም ማቋቋም፣
- ለአካባቢያዊ ልማቶች የሚሆኑ የኢንተርንሽራይዝ ማስፋፊያ ቦታዎችን መለየት፣
- በሁለተኛ እና በድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እና የክህሎት ሥልጠና ይዘቶች እንዲካተቱ ማድረግ
- መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሚሰጠው በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በሰርተፍኬት ደረጃ (ደረጃ 1-2) ሲሆን፤ በኮሌጆች ውስጥ በከፍተኛ ሰርተፍኬትና ዲፕሎማ ደረጃ (ደረጃ 3-4)፤ ፖሊቴክኒኮች በከፍተኛ ዲፕሎማ (ደረጃ 5) እንዲሁም በቴክኒካል ዩኒቨርስቲዎች በመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪዎች መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መስጠት፣
- በሁለተኛ እና በድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እና የክህሎት ሥልጠና ይዘቶች እንዲካተቱ ማድረግ። የድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለእደ-ጥበብ ባለሙያዎችና ቴክኒሽያኖች በዲፕሎማ ደረጃ በቴክኒካል ኮሌጆች፤ ለዋና እደ-ጥበብ ባለሙያዎች እና ለከፍተኛ ቴክኒሽያኖች በፖሊቴክኒኮች እንዲሁም ለቴክኖሎጂስቶችና ለቴክኒካል ኢንጂነሮች በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በዋና ቴክኖሎጂስትና በዋና ኢንጂነርነት በቴክኒካል ዩኒቨርስቲዎች፤ የክህሎት ሥልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፣
- ሥራ ለሌላቸው፣ ከአጠቃላይ ትምህርት ለሚያቋርጡ፣ በወረዳ ለሚኖሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች አጭር ሥልጠና (ከ10 እስከ 15 ወር) የሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ልዩ ሙያና አጠቃላይ የክህሎት ሥልጠና የሚሰጡ ማእከላትን ማቋቋም፤
- በሕዝብና የግል አጋርነትን ሞዴል የኢንዱስትሪ ሥልጠና ተቋም መመሥረት፣
- አህጉራዊና አለም አቀፍ የክህሎት ሠራተኞችና ቴክኒሽያኖች ሥልጠና ተቋም ማቋቋም፣
- የተለያዩ የሙያ የሥልጠና ፕሮግራሞችን የሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆችና ፖሊቴክኒኮችን በአገሪቷ በሚገኙ ስትራቴጂ ቦታዎች መመሥረት፣
- በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና በቴክኒካል ዩኒቨርስቲዎች የሚሰጠውን የክህሎት ልማት ተልእኮ ውጤታማ ለማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ የቴክኒክና የምርምር እገዛ የሚሰጥ አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የምርምር ተቋም ማቋቋም

5.4. አሠልጣኞችን በተመለከተ

- የቴክኒክና ሙያ አሰልጣኞች ማሰልጠን የሚችሉ ራሳቸው የቻሉ የማሰልጠኛ ተቋማት ማቋቋም(በተለይ የ ''C'' ደረጃ መምህራን የሚያሰለጥኑ ተቋማት ጨርሰው የሌሉ መሆናቸው)
- ማበረታቻ በመዘርጋት እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ተቀባይነት በማሳደግ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚሰሩ ኢንጂነሮችን፣ ቴክኖሎጂስቶችና የኢንዱስትሪ ባለሙያዎችን ወደ ዘርፉ መሳብ፣

5.5. የሙያ ምዘና

- የንግድ ምርክ ቤት በሙያ ምዘና ስታንዳርድና በምዘና መሣሪያዎች ዝግጅት እንዲሁም የብቃት ምዘና አመራር ተሣትፏቸውን ማረጋገጥ፣
- ሰልጣኞች የውጤት አሰጣጥ ሥርዓት "የበቃ""ያልበቃ"ከማለት ውድድርን በሚጋብዝና ለቀጣይ እድገት በሚያዘጋጅ መልኩ በቁጥር የሚገለፅ ውጤት (grade) መስጠት፤

6. ከፍተኛ ትምህርት

6.1 የፖሊሲ ማእቀፍ

- ዩኒቨርስቲዎች እንደተልኳቸው ትኩረት ማደራጀት፤ የምርምር፣ አንላይድ ሳይንስ፣ ቴክኒካል ዩኒቨርስቲ ሆነው እንዲደራጁ ማድረግ፣
- አዳዲስ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከመክፈት በፊት አስፈላጊው የሰው ሃይልና ሌሎች መሠረተ ልማቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ፣
- ካምፓኒዎችና የንግድ ተቋማት በከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ እንዲያደርጉ ሕጋዊ ማእቀፍ ማስተዋወቅ፤
- የሥራ ፈጠራ ማእከላትን በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ማቋቋም፣
- አወንታዊ የድጋፍ ሥርአት በመፍጠር የሴት መምህራንን ቁጥር ማሳደግ፣

6.2 የዩኒቨርስቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር

- የዩኒቨርስቲ- ኢንዱስትሪ ትስስርን ማጠናከር፣
- የኢንዱስትሪ አመራሮችን እንዲያስተምሩ በማድረግ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጠንካራ የዩኒቨርስቲ - ኢንዱስትሪ ትስስር መፍጠር፣ (የኢንዱስትሪ-ፕሮፌሰሮች ትስስር)

6.3 የምሩቃን የተግባር ልምምድና አገልግሎት አሰጣጥ

- የዩኒቨርስቲ ምሩቃን ከመመረቃቸው በፊት ከ8-10 ወራት የተግባር አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣

- የዩኒቨርስቲ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች በተግባር ልምምድ ወቅት ከወላጆቻቸው አካባቢ/ክልል ውጪ ወደ ሌሎቹ አካባቢዎች/ክልሎች በመመደብ የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበትን ሥርአት እንደገና ፈትሾ መተግበር፣

6.4 የማስተማር፣ የምርምር፣ የማህበረሰብ አገልግሎት

- የመጀመሪያ ትኩረቱ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቃት ያላቸውን መምህራንና አመራሮች የሚያፈራ ራሱን የቻለ የጥናትና ምርምር የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መመሥረት፣
- የመምህራን የማስተማር፣ የምርምር፣ የማህበረሰብ አገልግሎትን የሥራ ሰአት ምጥጥን 60:25:15 ማድረግ፣
- አለም አቀፋዊ የምርምር ጆርናሎችን ስታንዳርድ ያሟሉ የአገር ውስጥ ጆርናሎችን አቅም በማሳደግ እንዲሁም የዩኒቨርስቲ መምህራን ከፍተኛ ተቀባይነት ባላቸው የምርምር ጆርናሎች ላይ እንዲያሳትሙ የማበረታቻ ሥርአት መዘርጋት
- የማህበረሰብ አልግሎት በጀት ተመድቦለት መሠራት ያለበት ተግባር በመሆኑ ዩኒቨርሰቲዎች ለሚያካሂዱት የማህበረሰብ አገልግሎት በቂ በጀት እንዲመድቡ ማድረግ፣
- ለምርምርና ለቤተ-መከራ ግብአት የሚሆን ልዩ የግዢ አማራጭ መመሪያ ማዘጋጀት፣
- ለምርምርና ለቴክኖሎጂ ሽግግር ከበጀት ውስጥ 5% (የመሠረተ-ልማትን በጀት ተቀንሶ ከሚቀረው ውስጥ) መመደብ፣

6.5 የከፍተኛ ትምህርት ጥራት ማጐልበት

- የከፍተኛ ትምህርትን የመሰኮች ምጥጥን ከ70፡30 ወደ 60፡40 ማድረግ፣
- የትምህርት ጥራትን ለማጐልበትና አገራዊ አንድነትን ለማጠናከር በዩኒቨርስቲ የትምህርት ሥርአት ውስጥ የመጀመሪያ አመት ትምህርትን ኘሮግራምን እንደገና መተግበር፣
- በከፍተኛ ትምህርት የርቀት፣ የተከታታይ፣ በኢንተርኔት ትምህርት ማስተዋወቅ/ማጠናከር፣
- የከፍተኛ ትምህርት ጥራትን ለማጐልበት አለም አቀፋዊነትን ማጠናከር፣
- ዩኒቨርስቲዎች ከስታንዳርድ አኳያ ተመዝነው ደረጃቸው የሚታወቅበት የዩኒቨርስቲ ደረጃ አሰጣጥ ሥርአት በመዘርጋት በዩኒቨርስቲዎች የጥራት ደረጃ ማረጋገጥ፣
- የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አግባብ ያለው የጥራት ቁጥጥር በማድረግ ትምህርት እንዲሰጡ ማበረታታት፣
- በሁሉም የትምህርት አይነቶች የመውጫ ምዘና እንዲተገበር ማድረግ፣

6.6 የዩኒቨርስቲ አስተዳደርን በተመለከተ

- ዩኒቨርስቲዎች የትምህርት ስታንደርዶችን እንዲያጐለብቱና እንዲያግዙ ለማስቻል የውስጥ ገቢ የማጠናከርን ሥራ እንዲሠሩ ማበረታታት፡

- በከፍተኛ ትምህርት የአስተዳደር ሠራተኞችና የአካዳሚክ ሠራተኞች ምጥጥን በ1፡2 እና 1፡3 መካከል እንዲሆን መወሰን፣
- የአስተዳደር ሥራዎችን የውጪ አካል እንዲሠራው በማድረግ አመራሩ በዋና ተልእኮ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ፣

7 የትምህርትና ሥልጠና ቋንቋ

- ተማሪዎች በትምህርትና ሥልጠና ወቅት እውቀትና ክህሎትን በሚገባ እንዲጨብጡ ለማድረግ የሚያስችል ተለማጭ የትምህርት መስጫ ቋንቋ ፖሊሲ ማስተዋወቅ፣
- ሶስት የአገር ውስጥ ቋንቋዎችን የመማር ፖሊሲን ማጠናከር፣
- የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ሁለተኛ ቋንቋ ለአገራዊ የጋራ መግባባቢያ፣ ሌላ ቋንቋ በክልል ውስጥ ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፣ እንዲሁም ሦስተኛ ቋንቋ ለአለም አቀፍ መግባቢያ የያዘ የቋንቋ ፖሊሲ ማስተዋወቅ፣
- እንግሊዝኛ ቋንቋን ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ማስተማር፣
- እጩ መምህራን የተለያዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን እንዲማሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

8 የትምህርት ፋይናንስ

- የትምህርት ታክስን ማስተዋወቅ፣
- ከከፍተኛ ትምህርት ተመርቀው የሚወጡ ተመራቂዎች ይከፍሉት የነበረው 15% ክፍያ በ15 አመት ውስጥ ወደ 30% እንዲያድግ ማድረግ፣
- የትምህርት ፋይናንሱ ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ፣
- የግል ተቋማት፣ መያድ፣ ትርፍ ላይ ያልተመሰረቱ ሌሎች የውጭ ድርጅቶች በትምህርትና ሥልጠና ማስፋፋት እንዲሳተፉ ማድረግ፣

9 ሥርአተ-ትምህርት

9.1 የሥርዓተ- ትምህርት ይዘቶች

- ብቃትን መሠረት ያደረገና ከቅድመ-መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሙያ ጽንሰ-ሃሳቦችን ማካተት፣
- የሥርአተ ትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ፣ ከአካዳሚያዊ እና ከሙያ ክህሎት ጋር እንዲጣጣሙ ማድረግ፣
- ለመደበኛ ፕሮግራም ብቃትን መሠረት ያደረገና ከቅድመ-መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሙያ ጽንሰ-ሃሳቦችን ያካተተ፣ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ የአካዳሚክና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፎች (የሁለተኛ ደረጃ የአካዳሚክ ትምህርት ዘርፍ እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ) እንዲሁም በአካባቢ ደረጃ የአካባቢን ፍላጐት መሠረት ያደረገ ተለማጭ አገር አቀፍ የሥርዓተ-ትምህርት ፖሊሲ ማዘጋጀት፣

- በሁሉም ደረጃዎች ሥርአተ ትምህርቱ ከእውቀት ወደ ክህሎት ትኩረት እንዲሸጋገር/እንዲለወጥ ማድረግ፣
- በሁሉም ደረጃዎች/እርከኖች አገራዊ አግባብ ያለው በአለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ ሥርአተ ትምህርት መቅረጽ፣
- መሠረታዊ ክህሎት፣ የሕይወት ክህሎት እንዲሁም ከፍተኛ ደረጃ ክህሎትን በማካተት ማስተማር፣
- ቴክኖሎጂን በመጀመሪያ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ውስጥ አካቶ ማስተዋወቅ፣
- በሁሉም ደረጃዎች አገራዊ ተዛማጅነት ያላቸው እና አለም አቀፋዊነት ተወዳዳሪነትን የሚያረጋግጥ ሥርአተ ትምህርት በሁሉም ደረጃዎች መቅረጽ፣
- ጠንካራ የሆነ ተዛማጅ የሥርዓተ-ትምህርት ኘሮግራሞችን ማስተዋወቅ፣

9.2 ብዝሃነት

- ተማሪዎችን የተለያዩ ባህሎችን/የኢትዮጵያ ሕዝቦችን እንዲያውቁ በሁሉም የትምህርት ተቋማት ብዝሃ-ባህል ኮርሶችን ማስተዋወቅ፣
- እያንዳንዱ ብሔርና ብሔረሰብ አካባቢውን ለኑሮና ለልማት እንዲስማማ አድርጐ እንዴት መለወጥ እንደቻለ የማያተኩር የኢትዮጵያ ታሪክ መጻፍና ማስተማር፣

9.3 ምዘናና ፈተና

- ምዘና እውቀትን ብቻ ሳይሆን ክህሎትን፣ አመለካከት፣ እምቅ አቅምን እንዲመዘን ማድረግ፣
- መደበኛ የሆነ ተከታታይ ምዘና ላይ ማተኮር፣
- ክልላዊና አገር አቀፍ ፈተናዎች የብቃት ምዘና ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ፣
- የወረቀት-እርሳስ የማስታወስ ፈተናዎች ወደ ኘሮጀክትና በወቅት በሚሰጡ የጽሑፍ ሥራዎች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ፣
- አገራችን በአለም አቀፍ ደረጃ ያለችበትን ሁኔታ ለመገምገም የአለም አቀፍ ምዘና አባል በመሆን አለም አቀፍ ምዘናን ሥርአትን በማስተዋወቅ መሳተፍ፣
- ተማሪዎች አስፈላጊውን የመማር ውጤት አምጥተው ትምህርታቸውን ማጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ (የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጐት በለየና በመለሰ መልኩ)፣
- በልዩ ልዩ ደረጃዎች የሚሰጡ የሁለተኛ ደረጃ ሰርተፍኬት፣ የኮሌጅ ዲኘሎማና የዩኒቨርስቲ ዲግሪ መደበኛ የትምህርትና ሥልጠና ኘሮግራሞች ደረጃዎች በአገራዊ የሙያ ማእቀፍ ማረጋገጥ፣

9.4 የመምህራን ሥልጠና ሥርዓተ-ትምህርት

- የመምህራን ሥልጠና ከደረጃው ከሚሰጠው ትምህርት ሥርአተ ትምህርት ጋር ማጣጣም፣

9.5 አካታች/ልዩነትዶች የሚያስተናግድ ሥርዓተ-ትምህርት

- በሕፃናት መካከል ያሉትን ልዩነቶችን (ልዩ ተሰጥኦ፣ ክህሎት፣ ወዘተ. ያላቸውን ሕፃናት) የሚያስተናግድ የመማር ሁኔታ እንዲሁም ልዩነቶችን የሚያስተናግድ የማስተማር ዘዴን የሚያበረታታ ፖሊሲ ማዘጋጀት፣
- የአካል ጉዳተኝነትን፣ ልዩ ፍላጐትን፣ ሥነ-ጾታን፣ ኢኮኖሚን፣ ባህልን፣ የድጋፍና የአርብቶ አደር እንዲሁም አካባቢን ሳይለዩ በሁሉም የትምህርት እርከኖች አካቶ ትምህርትን መሠረት ያደረገ ለሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቀውን ትምህርት ማቅረብ፣

10 የትምህርት አስተዳደርና መዋቅር

10.1 የትምህርት ሕግና የፖሊሲ ማእቀፍ

- አገራዊ የትምህርት ሕግ ማዘጋጀት፣
- የጉልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት መዋቅሩን፣ ሥርዓተ-ትምህርቱን፣ የኘሮግራሙን ተሣታፊዎችን፣ አመቻቾችን፣ በጀትን፣ የተለያዩ ሀብቶችን፣ ባለድርሻ አካላትን፣ ወዘተ. ያካተተና በሁሉም ደረጃ ባሉ የትምህርት መዋቅሮች እንዴት ማስተዳደር እንደሚቻል አቅጣጫ የሚያሳይ ፖሊሲ ማዘጋጀት፣
- ትምህርት ቤቶች የለውጥ ማእከል፤ ያልተማከለ ውሳኔ ሰጪ፤ ባለሙያዎችን፣ ደንበኞችንና ሌሎችንም በውሳኔ የሚያሳትፉ፣ በራስ የመማርን የሚያበረታቱ፣ ፈጠራን የሚደግፉ እንዲሆኑ ትምህርት ቤት ተኮር አስተዳደርን መተግበር፣
- ራሱን የቻለ የትምህርት ጥራትና አግባብነት የሚቆጣጠር ተቋም በማቋቋም ሁሉንም የትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን እንዲቆጣጠርና የትምህርትና ሥልጠና ጥራትና እግባብነት እንዲያረጋግጥ ማድረግ፣
- በፖሊሲ አውጪዎች፣ በትምህርትና ሥልጠና አቅራቢዎች፣ በተጠቃሚዎች መካከል ጠንካራ የተጠያቂነት ግንኙነት ሥርአት መፍጠር፣
- የሴት ተማሪዎችን እንዲሁም መምህራንን ምጥጥን ማሳደግ፤ የሥርዓተ-ጾታ ምጥጥኑን ለማጥበብ የሴቶችን አቅም የማጠናከርና አወንታዊ እርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአሠልጣኞችን፣ ሥልጠና የሚሰጡትን አካላት እንዲሁም የገበያ ፍላጐትን ለማርካት ልዩ የክህሎት ሥልጠና የሚሰጥ ዩኒቨርስቲ ማቋቋም፣
- በክልልና በአገር አቀፍ ደረጃ ራሳቸውን የቻሉ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ኤጀንሲዎች ማቋቋም፣
- ሙያን መሠረት ያደረጉ የእደ-ጥበብ ሠራተኞች/ቴክኒሽያኖች ማህበራት ወይም የተወሰነ ምርትን መሠረት ያረገ ወይም አገልግሎትን መሠረት ያደረገ የአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ምክር ቤትን ማጠናከር፣
- ማንኛውም የሙያ ሥልጠና 12ኛ ክፍልን ካጠናቀቁ በኋላ የሚሰጥ ይሆናል።
- በሁሉም ደረጃዎች በመማር ውጤት ላይ ተጠያቂነትን ማስፈን፣

10.2 የትምህርት አደረጃጀት

- የትምህርት ሚኒስቴርን፣ የክልል ትምህርት ቢሮን፣ የዞን ትምህርት መምሪያን፣ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤትን እንዲሁም የትምህርት ቤቶችን ሚና፣ ኃላፊነት፣ ተጠያቂነት እና ግንኙነት እንደገና ግልጽ ማድረግ፣
- የትምህርት ሚኒስቴርን በተሻሻለ ሥርአት በሦስት ሚኒስቴር መ/ቤቶች ማለትም የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ሚኒስቴር (መደበኛ የመጀመሪያ ዲግሪና የሁለተኛ ዲግሪ የዩኒቨርስቲ ትምህርት፣ የመምህራን ትምህርትና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኘሮግራም)፣ የአጠቃላይ ትምህርትና ሥልጠና ሚኒስቴር እንዲሁም የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር (ትምህርት የሚያቋርጡትንና ሌሎችንም በመደበኛ ባልሆነ ሥልጠና በሙያ ሥልጠና በሰርተፍኬት፣ ዲኘሎማና በዲግሪ የሚያሰለጥን)
- የአጠቃላይ ትምህርትና ሥልጠናን፣ የመጀመሪያ ደረጃ የመምህራንና የትምህርት አመራሩን ሥልጠና ጨምሮ ኃላፊነቱን ለክልል ትምህርት ቢሮዎች መስጠት፣
- የቅድመ-መደበኛ ትምህርት እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ወረዳ ት/ጽ/ቤት፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የዞን ትምህርት መምሪያ በኃላፊነት እንዲሠሩ ማድረግ፣

10.3 የትምህርት አመራር

- የትምህርት አመራሮችንና አስተዳደሮችን በተዘጋጀ ተጨባጭ መመዘኛ መሠረት ብቃት ላይ የተመሠረተና ግልጽነት ያለው ውድድር በማካሄድ መረጣ፣ ምልመላና ምደባ መካሄዱን ማረጋገጥ፣
- በሁሉም የትምህርት እርከኖች ብቃት ያላቸውን የትምህርት ቤት አመራሮችን መመደብ፣
- በሁሉም እርከኖች ዴሞክራሲያዊ የሆነ ሙያዊ አመራር ብቃትን ያማከለ እንዲሆን ማድረግ፣
- የትምህርት አመራሮችንና አስተዳደሮችን ማበረታቻን መሠረት ያደረገ የሙያ ማሻሻያ ኘሮግራም አቅማቸውን ከፍ ማድረግ፣
- የትምህርትና ሥልጠና ኘሮግራሞች ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ፍላጐት ጋር መተሳሰሩን ለማረጋገጥ እንዲቻል የክልልና የወረዳ የትምህርትና ሥልጠና መምሪያዎች/ጽ/ቤቶችን አቅም ማጐልበትና ማጠናከር፣
- ልምድ ያላቸው መምህራንን ወደ ትምህርት ቤት አመራርነት እንዲያድጉ በሚያስችል መልኩ የመምህራንን የደረጃ እድገት ማዘጋጀት፤ በት/ቤት ውስጥም ሆነ ውጪ ያሉ የድጋፍ ሥርአቶችን ለመምህራን አቅም እንዲሆኑ ማጠናከር፣

10.4 የትምህርት አስተዳደርና የመረጃ ሥርአት

- በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች/እርከኖች የተማሪዎችን የመማር ሁኔታና ፈጠራን ለመደገፍ የሚያስችል የምርምርና የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረት ልማት ማስፋፋት፣

- በሁሉም እርከኖች ያሉ ተማሪዎች መሠረታዊ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል የተማሪዎችን ዳራና አጠቃላይ መረጃ ማደራጀት፣

10.5 የባለድርሻ አካላት ኃላፊነት

- ትምህርት ተቋማት አግባብነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር (ምሳሌ፣ የዩኒቨርስቲ-ኢንዱስትሪ፣ የት/ቤት-መምህራን፣ ወዘተ.) ጠንካራ ትስስር መፍጠር፣
- ትምህርት ቤቶች ለአካባቢውና ለተማሪዎች ምላሽ ሰጪ እንዲሆኑ የት/ቤት ባለድርሻ አካላትን (ር/መምህራን፣ መምህራን፣ ወላጆች፣ ማህበረሰቡ) አቅም ማጠናከር፣
- የወላጆችንና የማህበረሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግ እንዲቻል ይህን ሥራ የሚያስተባብር አካል በወረዳ ደረጃ ማደራጀት፣
- የት/ቤት ወላጅ ተሣትፎን ማጠናከር፤ ወላጆች በተወካዮቻቸው አማካኝነት የልጆቻቸውን የትምህርት ውጤታቸው ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ ስለልጆቻቸው አጠቃላይ ደህንነት ክትትል እንዲያደርጉ ማበረታታ ያስፈልጋል።
- እንደ መምህራን ማህበር ያሉ የሙያ ማህበራት የበለጠ ሙያዊ እንዲሆኑና በራሳቸው ሙሉ ነፃነት ኖሯቸው እንዲሠሩ አቅማቸውን ማጠናከር

ማጣቀሻ መጻሕፍት

Aike, W.M. and Ayle, B.K. (2015). State of Service Delivery in Ethiopian Primary Schools: Findings from the Ethiopia Education Service Delivery Indicator Survey. Middle Eastern & African Journal of Educational Research, Issue 16, pp. 34-58.

Ministry of Education. (2016). Ethiopian Education Roadmap Development Process, 2017-2030: Preprimary and Primary Education, Desk Review Report.

Ministry of Education. (2016). Ethiopian Education Roadmap Development Process, 2017-2030: Secondary and Preparatory Education, Desk Review Report.

Ministry of Education. (2016). Ethiopian Education Roadmap Development Process, 2017-2030: Policy, Leadership and Governance in Ethiopian Education System: Practices, Challenges and Implications for Policy and Plan, Desk Review Report.

Ministry of Education. (2016). Ethiopian Education Roadmap Development Process, 2017-2030: TVET Education, Desk Review Report.

Ministry of Education. (2016). Ethiopian Education Roadmap Development Process, 2017-2030: Teacher Preparation and Development, Desk Review Report.

Ministry of Education. (2016). Ethiopian Education Roadmap Development Process, 2017-2030: Higher Education, Desk Review Report.

Ministry of Education. (2017). Ethiopian Education Roadmap Development Process, 2017-2030: Preprimary and Primary Education, Empirical Survey.

Ministry of Education. (2017). Ethiopian Education Roadmap Development Process, 2017-2030: Secondary and Preparatory Education, Empirical Survey.

Ministry of Education. (2017). Ethiopian Education Roadmap Development Process, 2017-2030: Policy, Leadership and Governance in Ethiopian Education System: Practices, Challenges and Implications for Policy and Plan, Empirical Survey.

Ministry of Education. (2017). Ethiopian Education Roadmap Development Process, 2017-2030: TVET Education, Empirical Survey.

Ministry of Education. (2017). Ethiopian Education Roadmap Development Process, 2017-2030: Teacher Preparation and Development, Empirical Survey.

Ministry of Education. (2017). Ethiopian Education Roadmap Development Process, 2017-2030: Higher Education, Empirical Survey.

Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016/17).

Ministry of Education. (2017.) Education Statistics Annual Abstract 2009 E.C. (2016/17). GE 2009_Annex.

Ministry of Education. (2017.) Ethiopian Education Development Roadmap: An integrated Executive Summary (Draft).

NEAEA. (2011). Ethiopian National learning Assessment Grade 4 & 8.

NEAEA. (2014). Early Grade Mathematics Assessment (EGMA).

NEAEA. (2015). Ethiopian National learning Assessment Grade 4 & 8.

NEAEA. (2016). *Ethiopia Fifth National Learning Assessment of Grades Four and Eight Students*. (Unpublished).

NEAEA. (2017). *Ethiopia Third National Learning Assessment of Grades 10 and 12 Students Achievements*. (Unpublished).

Salmi, J., Sursock, A. and Olefir, A. (2017). Improving the Performance of Ethiopian Universities in Science and Technology: A policy note.

Schleicher, A. (2015), Schools for 21st-Century Learners: Strong Leaders, Confident Teachers, Innovative Approaches, international Summit on the teaching profession, oeCd publishing. http://dx.doi.org/10.1787/9789264231191-en

The Wold Bank. (2017). Sharing Higher Education's Promise beyond the Few in Sub-Saharan Africa. http://creativecommons.org/licenses/by/3.0/igo.

The World Bank. (2013). Secondary Education in Ethiopia.

The World Bank. (2018). Facing Forward: Schooling for Learning in Africa

The World Bank. (2018). Learning to Realize Education's Promise,

TVET Agency (2017). Project for Wereda Based TVET Accessibility Ethiopia.

UNESCO. (2017). GLOBAL EDUCATION MONITORING REPORT 2017/2018. https://en.unesco.org/gem-report/

UNESCO. (June, 2017). Reducing Global Poverty through Universal Primary and Secondary Education,Policy Paper 32/Sheet 44.

በትምህርት ሚኒስቴር፤ የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት (2009)። **የ**2009 **ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ምልመላ የፈተና ውጤት።**

በትምህርት ሚኒስቴር፤ የመምህራንና የትምህርት አመራር ዳይሬክቶሬት፤ (2010)። **እጩ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ምልመላ የመግቢያ ፈተና።**

ትምህርት ሚኒስቴር (**ሚያዝያ፣** 2010)። **የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን የመጀመሪያ ዙር የትምህርት ቤቶች አፈጻጸም ደረጃ ትንተና።**

ትምህርት ሚኒስቴር (ሰኔ/2009)። የ2009 በጀት ዓመት እቅድ ማጠቃለያ የአፈፃፀም ሪፖርት።

ትምህርት ሚኒስቴር፣ (ነሐሴ፤ 2008)። የማሻቀልቀል ምዕራፍ ተዘግቶ የእድገት ምዕራፍ በተከፈተበት የሃያ አምስት ዓመታት ጉዞ ውስጥ የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ሚናና ለቀጣይ ተልዕኮ ሊኖረው የሚገባው ቁመና። አዲስ አበባ፡ ትመማማድ።

ትምህርት ሚኒስቴር። (ነሐሴ/2007)። የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የ2008 ዓ.ም. መሪ እቅድ።

ትምህርት ሚኒስቴር። (ነሐሴ/2007)። የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የ2010 በጀት ዓመት እቅድ።

ትምህርት ሚኒስቴር። (ነሐሴ/2009)። የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የ2009 ዓ.ም. የትምህርት ንቅናቄ ሰነድ።

ትምህርት ሚኒስቴር። (ግንቦት/2009)። የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የ2010 በጀት ዓመት ጠቋሚ እቅድ።

ትምህርት ሚኒስቴር። (ግንቦት/2010)። የትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የ2010 ዓ.ም. የ9 ወር የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት። (መጋቢት፣ 1986)። አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ። አዲስ አበባ፣ ሚጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር።

አባሪ-አንድ፣
በፍኖተ-ካርታ ጥናት ሂደት በአጥኚነት የተሳተፉ ባለሙያዎች ዝርዝር

1.1List of Researchers by thematic areas with addresses and qualifications

S.No.	Employing University/ organization	Name	Qualifications	Email address
Education Policy, Leadership and Governance				
	Addis Ababa University (AAU)	Jeilu Oumer	PhD	Theme Leader
	AAU	Kenenissa Dabi Furi	PhD in Educational Policy and Leadership,AAU, 2014	Kenenissad@yahoo.com
	Jimma	Mitiku Bekele Gemeda	**Ph.d** in Education (Educational Leadership) at Andhra University , 2003 E.C	mitikumas@yahoo.com
	Haramaya	*Getnet Demissie Bitew*	PhD in educational Policy and Management University of Melbourne, Australia,, 2008.	Associate Professor Email: ***getnetdb@yahoo.com***
	Education Bureau	Mengistu Hailu	PhD in Educational Administration and Supervision, Tennessee State University, USA, 2011	Email: whmengistu@gmail.com
	Bahir Dar	Matebe Tafere	PhD in Educational Policy and leadership, Addis Ababa University	matebetafere@yahoo.com
	Higher Education			
	AAU	Prof. Tasew W/hana	PhD	Theme Leader
	AAU	Gebregziabher Debeb	PhD in education, University Andhra University, India, 2012	gebre.dberhe@gmail.com
	Bahir Dar	Tesfaye Shiferaw Bogale	Ph.D. in Material Science and Engineering, University of Kiel, Germany, 2008	tesfaye2002@yahoo.com
	Gondar	Bekele Workie Ayele	PhD in Curriculum Design and	bekeleworkie@gmail.com

S.No.	Employing University/ organization	Name	Qualifications	Email address
			Development,2016, AAU	
	Jimma	Gemechis File Duressa	PhD in Mathematics (Numerical Analysis), National Institute of Technology, Warangal, India, 2014	gammeef@yahoo.com
	Jimma	Tefera Tadesse	Ph.D. in Curriculum and Instruction,University of Queensland, Australia, 2014.	Tefera.tadesse@ju.edu.et
Primary and Pre-primary Educcation				
	AAU	Prof. Tirussew Teferra	PhD	Theme Leader
	AAU	Abdulaziz Hussien Mamie	PhD in Education from Andhra University, India, 2005	abdihmamie@gmail.com
	AAU	Deme Aberra	PhD	
	AAU	BELAY HAGOS HAILU	PhD in Special needs education: focus area on counseling disadvantaged children, AAU, 2012	belay.hagos@aau.edu.et
	AAU	Girma Lemma Fantaye	PhD in Applied Developmental Psychology: Addis Ababa University	lemma_girma42@yahoo.com
	AASTU	Balew Demissie Kebede	PhD In English Literature, AAU, 2016	balewdem@gmail.com
Secondary and Preparatory Education				
	AAU	Prof. Amare Asgedom	PhD	
	Bahir Dar	*Dawit Asrat Getahun*	PhD in Learning Sciences, McGill University, Montreal, Canada, 2014	dawitas@yahoo.com
	AAU	Yekoyealem Desie Kebede	Ph.D. in Applied Developmental Psychology, AAU, 2014	
	AAU	Ambissa Kenea	PhD in Education, Andhra University, 2006	
	Hawassa	Tesfaye Semela	PhD in Education (Ed	Professor

S.No.	Employing University/ organization	Name	Qualifications	Email address
			Psychology and Sociology of Education, University of Tubingen, Germany, 2003	tskukem@gmail.com
	Debre Birhan	*Dereje Andargie Kidanemariam*	*PhD in Mathematics, Science and Technology Education (chemistry education), UNISA*	derejefanaye@gmail.com
Teacher Education				
	AAU	D/r Akililu Dalule	PhD	Theme Leader
	AAU	Abraha Asfaw Ambaye	PhD in Curriculum Design and Development, AAU, 2014	Email: aasfaw11@gmail.com
	AAU	Darge Wole	**PhD in** Educational Psychology, Florida State University, 1986	Professor Email: dargewolem@yahoo.com
	AAU	Dawit Mekonnen	PhD in Education, University of Leipzig, 2007	Email: dawit_mm@yahoo.com
	Ambo	**Fekede Tuli Gemeda**	**PhD in Pedagogy** , Roma Tre University, Rome, Italy and Finnish Institute of Education Research, Jyvaskyla University, Finland,2014	Email: fekede2010@gmail.com
	AAU	Derebssa Dufera	PhD in Curriculum Planning, Rostock University, Germany, 1993	Professor/ email: derebssad@yahoo.com, 0929371486
TVET				
		D/r Birehanu Asefa	PhD	Theme Leader
	AAU	Getachew Biru Worku	PhD in Electrical Engineering , Dresden University of Technology, 1998	Email: : gbiru@yahoo.co.uk
	AAU	*Daniel Tilahun*	PhD in Mechanical System engineering, University of Myazaki, Japan	Email: tdaniel412@yahoo.com
	AAU	Melaku Wakuma Duguma	Ph D in TEFL, AAU, 2011	Email: m_wakuma@yahoo.com

S.No.	Employing University/ organization	Name	Qualifications	Email address
	AAU	Wanna Leka	PhD in Education, Training and Development, Southern Illinois University, Carbondale, IL. (USA), 1989	Email: wanna_leka@yahoo.com
	Education Bureau, Bahir Dar	Melaku Mengistu	PhD in Education Policy and Leadership, AAU, 2015	Email: mmelaku25@gmail.com

1.2 Associate Researchers grouped under the Six Teams based on Regions of Deployment

S.No.	Employing University/ organization	Name	Qualifications	Email address
	Team 1: Addis Ababa and SNNPR			
1	Addis Ababa University (AAU)	Alemayehu Teklemariam	PhD, Special Needs Education, Jyvaskyla University,2010. M.Phil. University of Oslo 2000.	***alemayehutm@yahoo.com;***
2	AAU	Moges Ayele	PhD in Applied Developmental Psychology from Addis Ababa, 2014	mogesay@yahoo.co.uk;
3	Wolaita Sodo	Ashebir Bezabeh	(PhD)in Educational policy and leadership;	ashbeze@yahoo.com;
4	Dilla	Genene Abebe	PhD, curriculum design and development AAU, 2015	gagiabtd@yahoo.com,
5	Kotebe	Maeregu Biyabeyen	Assistant professor,MA in Educational policy and leadership	bmaeregu@Yahoo.Com;
6	ESC	Behailu Korma	MA in special needs education, AAU, 2016; MA in Linguistics AAU, 2010.	Behailu.korma@yahoo.com;
7	ESC	Asegedech Shawl	MA, 'Organizational Leadership' Azusa Pacific University ,2009	asegedechkikal@yahoo.com;
8	AAU	Alebachew Kemisso	PhD candidate in International and Comparative Education, AAU, 2016. MA in Curriculum and Instruction, AAU, 2009.	kemissalebachew@gmail.com; alebachew.kemisso@aau.edu.et;
9	Kotebe	Abbay Belayhun	MA in Special Needs	ababelay2014@gmail.com

S.No.	Employing University/ organization	Name	Qualifications	Email address
		Kidane	Education, AAU, July, 2009	;
10	Bahir Dar	Dejenie Nigusie	MA, Educational Planning and Management, PhD fellow, in Education Policy and Leadership, AAU, Since 2012	dejenien@yahoo.com;
11	Jimma	Kinde Getachew Abebe	Master of Arts in Educational Psychology Addis Ababa University, Ethiopia, 2004	kendie_get@yahoo.com; kinde.getachew@ju.edu.et;
12	AAU	Habtamu Diriba	MA in Research and Innovation ,2016, ERASMUS ,MBA ,2010	*habtamud1@gmail.com;*
13	AAU	Fetene Regassa Melka	PhD in Curriculum Design and Development AAU,2014.MA in Curriculum and Instruction,AAU,1998	fetenerg@gmail.com,
15	Jimma	Woldu Assefa Yadetie	M.A in curriculum and instruction from Addis-Ababa University, -july, 1999	wolduassefa@gmail.com; orwoldu.assefa.assefa@ju.edu.et; wolduyadetie2011@gmail.com;
		Team 2: Amhara and Benishangul		
1	AAU	Mulat Asnake	PhD in Developmental Psychology, AAU	mulatasnake76@yahoo.com;
2	Jimma	Wudu Melese Tarekegne	PhD Degree in Curriculum Design and Development	wudumelese@gmail.com
3	AAU	Tilahun Fanta Negeri	Assistant Professor, M.A in Curriculum and Instruction, Addis Ababa University in June 1998	tilahunfanta74@yahoo.com;
4	ESC	Animaw Tadesse	MA in Measurement and Evaluation	dinbuloanimaw@gmail.com,
5	Gondar	Mikyas Abera	PhD, Sociology, AAU, 2015	mikidar2003@yahoo.com;
6	Bahir Dar	Haftu Hindeya Gebremeskel,	PHD CANDIDATE in Social Psychology MA in Social Psychology	haftu_hg@yahoo.com;
7	Bahir Dar	Yohannes Asmare	PHD CANDIDATE in Social Psychology MA in Social Psychology	yohanneschekole@yahoo.com;
8	Bahir Dar	Yismaw Nigussie	PHD CANDIDATE in Social Psychology MA in	yismaw2003@gmail.com;

S.No.	Employing University/ organization	Name	Qualifications	Email address
			Social Psychology	
9	Bahir Dar	Zelalem Getnet Tilahun	PHD CANDIDATE in Social Psychology MA in Social Psychology	zelalemgt@gmail.com;
10	Debre Birhan	Abiyou Tilahun Ayalew	PHD CANDIDATE in Social Psychology MA in Social Psychology	abiytila22@gmail.com;
11	Gondar	Kelemu Fenta	PHD CANDIDATE in Social Psychology MA in Social Psychology	kelemusosa@gmail.com
12	Jimma	Aemero Asmamaw Chalachew	PhD program Andhra University, INDIA 2007 E.C	amasmamaw@yahoo.com; asmamawam@gmail.com;
13	ESC	Amarech Kebede Mekonnen	MA in Educational Research and Development, AAU ,2007	bemni1995@gmail.com;
14	AAU	Dawit Mekonnen Gebru	PHD CANDIDATE in Social Psychology MA in Social Psychology	**dawit.mekonneng@aau.edu.et;**
15	AAU	Birara Gebru	M Ed in Education Technology , University of Wales, 1983	birara2011@gmail.com;
		Team 3: Dire Dawa, Harari and Ethiopian Somali		
1	Jimma	Fisseha Mikre Weldmeskel	Doctor of Education in Didactics, UNISA, 2016	fisseha.mikre@ju.edu.et; weldmeskel2@yahoo.com
2	Jigjiga	Ayele Nega	PhD in TEFL at AAU in 2015	nasosinna@gmail.com
3	ESC	Fasil Tsegaye	MA in Educational Policy **and Planning AAU**, 2009	MA in Educational Policy **and Planning AAU**, 2009
4	Madda Walabu	Ashebir Demeke Gebretsadik	PhD Educational Management, University of South Africa, 2014	ashebir2005@yahoo.co
5	ECSU	Temesgen Birega	MA in Educational Planning and Management, AAU, 2005; PhD Candidate in Public MG	birega2006@yahoo.com;
6	Jimma	Abeya Geleta Geda	Master of Arts Degree in Educational Leadership, Jimma University, 2013	abeyageleta@gmail.com ; abeya.geleta@ju.edu.et
7	ESC	Ephrem Lakew	MA in EDPM, ,Haramaya University, 2013	ephladd@yahoo.com
8	Jimma	Bekalu Ferede Tefera	Ph.D, Education Policy and Leadership, AAU, (2011-todate, on progress)	feredebekalu@gmail.com: tbekaluferede@yahoo.com;

S.No.	Employing University/ organization	Name	Qualifications	Email address
			MA, Adult Education and Lifelong Learning, Aarhus University, Denmark, 2010	
9	Haramaya	Wakgari Tasisa	Ph.D Degree in Adult education, Adama Sci and Tech University, 2011	wakgaritasisa2016@yahoo.com,
10	Haramaya	Aderie Feye Debele	PhD candidate, MA in Special Needs Education in AAU, 2002	adefeyed@yahoo.com
11	AAU	Demoze Degefa	Ph.D, Education Policy & Leadership, AAU, (2011-to dates) MA, Adult Education and Lifelong Learning, Aarhus University, Denmark, 2010	demozed2008@gmail.com;
12	Haramaya	Muhammed Kedir Hiko	MA in Educational Planning and Management on July 12, 2010	think2greenlife@gmail.com or mohammed.kedir@haramaya.edu.et
			Team 4: Oromia and Gambella	
1	AAU	Teshome Tola Komo	PhD, MA in Curriculum and Instruction, AAU, 2010	teshometola@yahoo.com;
2	AAU	Sutuma Edessa Wako	PhD in Silviculture, Mendel University of Agriculture and Forestry, Czech Republic, 1996	sutuma2002@yahoo.com;
3	Arsi	Tolera Negassa	Ph.D Degree in Adult education, Adama Sci and Tech University, 2011	toleranegassad@gmail.com;
4	Arsi	Endalew Fufa Kufi	Doctor of Education in Comparative Education, University of South Africa /UNISA/, 2013	endalewkufi@yahoo.com;
5	Gambella	Aregay Berhe	Ph.D Candidate, Education Policy and Leadership, AAU, (2011-to date) MA, Adult Education and Lifelong Learning, Aarhus University, Denmark, 2010	aregaybe@gmail.com
6	Jimma	Samson Wondirad	Doctor of Education in Comparative Education,	smwonde@gmail.com; samsonwondirad@yahoo.com;

S.No.	Employing University/ organization	Name	Qualifications	Email address
		Tadesse	University of South Africa /UNISA/, 2013	
7	Jimma	Adula Bekele Hunde	PhD in Educational Leadership and Policy, Addis Ababa University, 2015	adula.bekele@ju.edu.et; kiya.adula@gmail.com;
8	Mettu	Teklu Tafase	PhD in Applied Developmental Psychology AAU, 2015	Olkaba2014@gmail.com;
9	ESC	Tesfaye Negewo Jimma	MSc in Animal Production ,Haramaya University , 2008	*tesfanegewo@yahoo.com,*
10	Wollega	Begna Ordofa	M.A in Educational Planning &Management, AAU, 2007	begnaordofa@yahoo.com;
11	Jimma	Dereje Dakisa Kenno	MSc, Mechanical Engineering, AAU, 2009	
12	Pension	Workneh Tolu Ariti	MA, Curriculum & Instruction, AAU, 2011	**worknehtolu@gmail.com**
4	Jimma	Gemechis Teshome Chali	MA inTEFL,AAU,2011	gammee30@gmail.com; gemechis.chali@ju.edu.et;
14	ESC	Serawit Handiso	MSc in Crop Protection Ambo University,2011MBA in Non-profit Corporate Management,2013, IICM	**serawithandiso@gmail.com**;
		Team 5: Tigray and Afar		
1	AAU	Alemseged Gerezgiher	PhD in Development Studies, AAU, 2016	abushalex@yahoo.com;
2	Mekelle	Yohannes G/tsadik	DEd in Inclusive Education, University of South Africa,2015 MEd in Curriculum Studies, AAU, 2004	gts.yohannes@yahoo.com;
3	Mekelle	Beyene Baraki Asgedom	MA , Curriculum& Instruction, AAU, 2013PhD in Education from Delhi University, 2013	blastnamebaraki@yahoo.com; beyene2016@yahoo.com;
4	Axum	Abraham Negash	PhD candidate , UNISA	**abrahamn3@yahoo.com;**
5	ESC	Seid Mohammmed	MA in Educational Leadership, AAU	**fasoch30@yahoo.com;**

S.No.	Employing University/ organization	Name	Qualifications	Email address
6	AAU	Biruh Assefa Gebrehiwot	PhD Candidate in Applied Linguistics & Communication, AAU,**MA** in **TEFL**,AAU, 2010.	***biruhassefa@gmail.com***; ***biruh.assefa@yahoo.com***;
7	AAU	Kebede Derbew	PhD Candidate, MA in Educational Planning and Management in 2006	kebedederibew@yahoo.com,
8	Adigrat	*Hailay Tsigab Kahsay*	*PhD candidate at AAU,*MA *in Development Economics, ECSU ,2012.*	*hailay20@gmail.com* ,
9	***Adigrat***	G/selassie Sebhatleab	PhD Candidate AAU, .M.A in Development Studies ,Mekelle University in 2011	gebreselassiesebhat@yahoo.com; binigere2002@gmail.com;
10	Mekelle	Nigusse Weldemariam	Master of Philosophy in Higher Education, University of Oslo, Norway	kg_weldie@yahoo.com;
11	Tigray Education Bureau	Birkti G/Micheal Garead	BA/Educational Psychology/MA Anthropology	**bitimami@yahoo.com,**
12	ESC	Fireweini G/egziabiher	**MA in Gender Studies , 2011 AAU**	*fireweinige@gmail.com,*
		Team 6: Federal Institutions in Addis Ababa		
1	AAU	Getachew Adugna	PhD, Curriculum and Instruction	**getish1958@yahoo.com**
2	ESC	Tesfamariam Shimekit	MA in Educational leadership-Bahir-Dar University	**tesfakit@gmail.com**;
3	AAU	Yohannes Workeaferahu	Msc Management in Economics Studies, Wageningen University Netherlands, 2005	yoh2003@gmail.com;
4	AAU (Parttimer)	Amin Negussie	MBA, AAU, 2012	aminezman@yahoo.com;
5	AAU	Meskerem Mitiku	MBA, AAU, 2010;Since 2012 PhD candidate in Tilburg University, Netherlands	Meskerem.mitiku@aau.edu.et;
6	AAU	Negash Mulatu Debalke	*Master of Science (MSc) Degree in Economics*, , 2011 AAU	*negash.mulatu@aau.edu.et ; negash2016@yahoo.com;*